# ኅብረተሰብ ሳይንስ

## 8ኛ ክፍል

## የተማሪ መጽሐፍ


**አዘጋጅ:-**

ወንዱ ተክለመድህን

**አርታኢ:-**

መኩሪያ ፈለቀ

**ገምጋሚዎች:-**

ዘላለም አላጋው

ዘሪሁን ጌታቸው

ይታገሱ አጥናፉ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

## ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ኘሮጀክት (GEQIP) አማካኝነት ነው። የኘሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ለGEQIP የዋለውን ገንዘብ ያገኘው በብድር/በእርዳታ ሲሆን ብድሩን/ እርዳታውን የሰጡት ዓለምአቀፍ የልማት ማህበራት (IDA)፣ ፋስት ትራክ ኢንሼትቭ ካታሊቲክ ፈንድ (FTI CF) እና ሌሎችም የልማት አጋሮች ማለት የፊንላንድ፣ የኢጣሊያ የልማት ማህበር፣ የኔዘርላንድና የታላቋ ብሪታኒያ የእርዳታ ድርጅት አለምአቀፍ የልማት ዋና ክፍል (DFID) ናቸው።

ሁሉንም በዝርዝር መጥቀስ የማይቻል በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ የተማሪ መጽሀፍና የመምህር መምሪያ እውን እንዲሆኑ ያልተቆጠበ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል። በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል።

© በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

*1ኛ እትም፣ 2003 ዓ.ም*

ISBN 978-99944-2-088-9

**የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 5613**
**ዱባይ፣**
**የተባበሩት የአረብ ኤሜሬት**

**ከኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 100767**
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**

ጋር በመተባበር ይህን መጽሐፍ ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅተው አትመው፣ አሰራጭተዋል።

ሁሉም የህትመት መብቶች ተከብረዋል።

የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የኮፒራይትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ 10ኛ አመት ቁጥር 55 አዲስ አበባ ጁላይ 19, 2004 ይከለክላል።

የስዕሎችን የኮፒ ራይት መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# ማውጫ

ገፅ

## ምዕራፍ አንድ፡- የምንኖርባት መሬት

1.1 አኅጉራት ....................................................................................1
1.2 የዓለም ሕዝቦች..................................................................................6
1.2.1 በዓለም የሚገኙ ሃይማኖቶች .................................................................. 15
1.3 የሕዝብ ሥርጭትና አኗኗር ...................................................................18
1.3.1 ሕዝብ ተበታትኖና ተጠጋግቶ የሚኖርባቸው ቦታዎችን ማነጻጸር ...............................18
1.3.2 ለዓለም ሕዝቦች ሥርጭት መለያየት ምክንያቶች ............................................. 23
1.3.3 የዓለም ሕዝቦች አኗኗር .................................................................... 25
1.3.4 የኢንዱስትሪ አብዮትና ያስከተለው ውጤት ........................................................ 27

ቁልፍ ቃላት ...................................................................................42
ማጠቃለያ ......................................................................................43
የክለሳ ጥያቄዎች ..............................................................................44
ፍተሻ ..........................................................................................46

## ምዕራፍ ሁለት፡- ገጸ ምድርን የሚለውጡ ኃይሎች

2.1 የመሬት ውጫዊ ኃይሎችና በሰው ልጅ አኗኗር ላይ
የሚያስከትሉት ለውጥ ...........................................................................47
2.2 የመሬት ገጽ ለዋጭ ውስጣዊ ኃይሎችና በሰው ልጅ አኗኗር ላይ
የሚያስከትሉት ለውጥ ........................................................................... 55
2.3 ከካርታ ላይ ርቀትና ስፋትን መለካት.............................................................61

ቁልፍ ቃላት ...................................................................................70
ማጠቃለያ ......................................................................................71
የክለሳ ጥያቄዎች ..............................................................................72
ፍተሻ .......................................................................................... 74

## ምዕራፍ ሦስት፡- ሥርዓተ ምኅዳርና የሰው ልጅ ጣልቃ ገብነት


3.1 የሰውና የተፈጥሮ ሀብት ግንኙነት ....... 75

3.2 የዓለም ሙቀት መጨመር መንሥኤና ውጤት ....... 83

ቁልፍ ቃላት ....... 91

ማጠቃለያ ....... 92

የክለሳ ጥያቄዎች ....... 93

ፍተሻ ....... 95


## ምዕራፍ አራት፡- ሕዝባዊ ጉዳዮች


4.1 ሕዝብ ነክ ጉዳዮች ....... 96

4.1.1 ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመዋጋት ዙሪያ የወጣቶች ሚና ....... 97

4.1.2 ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን መቆጣጠሪያ ስልቶች ....... 101

4.2 ሰብአዊ መብቶችና ደኅንነት ....... 106

4.3 የአጋርነት መርሐ ግብር ....... 114

ቁልፍ ቃላት ....... 121

ማጠቃለያ ....... 122

የክለሳ ጥያቄዎች ....... 123

ፍተሻ ....... 125

ምዕራፍ

አንድ

# የምንኖርባት መሬት

*ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጠቃላይ ውጤቶች*

**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- መገኛ ቦታዎችንና ዋና ዋና የዓለም መልክአ ምድሮችን እንዲሁም ዋና ዋና የዓለም ቋንቋዎችን ትገልጻላችሁ::
- ጥንታዊ ዋና ዋና ሥልጣኔዎችን ታደንቃላችሁ::
- ሕዝብ ተጠጋግቶና ተበታትኖ የሠፈረባቸው የዓለም ክፍሎችና ለልዩነቱ አስተዋጽኦ ያደረጉ ነገሮችን ትለያላችሁ::
- የኢንዱስትሪ አብዮት ያስከተለውን ውጤቶች ትዘረዝራላችሁ::
- የአፍሪካ ሕዝቦችን ፀረ ቅኝ አገዛዝ የትግል ታሪክን ትለያላችሁ::
- አዳዲስ ሐሳቦች እንዴት እንደተገኙና ምንነታቸውን ታስረዳላችሁ::

## 1.1 አኅጉራት


*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት፡-*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ**

- የሰባቱን አኅጉራት ካርታ ትሠራላችሁ::
- የአኅጉራትን አንጻራዊ መገኛ ትገልጻላችሁ::
- የዓለም አኅጉራትን ስፋት ታወዳድራላችሁ::
- የዓለም ከፍተኛና ዝቅተኛ ቦታዎችን ትለያላችሁ::
- የዓለም ታላላቅ ሐይቆችና ወንዞችን ትለያላችሁ::

**ቁልፍ ቃላት**

- አኅጉር
- ልሳነ ምድር
- ባሕረ ገብ መሬት




*ምሥል 1.1 አኅጉራት*

## ሀ. የአኅጉሮች አንጻራዊ መገኛ እና መጠን

ከመሬት ውጫዊ አካል ሃያ ዘጠኝ በመቶ የሚሆነው የተሸፈነው በአኅጉሮችና በደሴቶች ነው፡፡ ሰባ አንድ በመቶ የሚሆነው የመሬት ውጫዊ አካል ደግሞ የተሸፈነው በውኃ አካላት ነው፡፡

አኅጉሮች በጣም ትልቅ የመሬት ክፍሎች ናቸው፡፡ በዓለም ላይ ሰባት አኅጉሮች አሉ፡፡ እነርሱም፡- እስያ፣ አፍሪካ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ፣ አንታርክቲካ፣ አውሮፓ እና አውስትራሊያ ናቸው፡፡ በምስል 1.1 ላይ እንደምትመለከቱት አኅጉሮች በመጠናቸው ይለያያሉ፡፡ በመጠኑ በዓለም ትልቁ አኅጉር እስያ ነው፡፡ አንታርክቲካ፣ አውሮፓ እና አውስትራሊያ በአንድ ላይ ቢደመሩ እንኳን እስያን አያህሉም፡፡ እስያ በመጠኑ አንታርክቲካን በስድስት እጥፍ ይበልጣል፡፡

ከሰባቱ አኅጉራት አምስቱ እርስ በእርሳቸው የተያያዙ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል አንታርክቲካና አውስትራሊያ በውኃ የተከበቡ ናቸው፡፡ ሰሜን አሜሪካ እና ደቡብ አሜሪካ የፓናማ ልሣነ ምድር በተሰኘ ጠባብ የመሬት አካል ይገናኛሉ፡፡ አፍሪካም እንደዚሁ በስዊዝ ልሳነ ምድር ከእስያ ጋር ይገናኛል፡፡

### የአኅጉራት አንጻራዊ መገኛ

- **እስያ**

እስያ በምሥራቅ ከሰላማዊ ውቅያኖስ (Atlantic Ocean)፣ በደቡብ ከሕንድ ውቅያኖስ፣ በሰሜን ከአርክቲክ ውቅያኖስ፣ በምዕራብ ከአውሮፓ፣ በደቡብ ምዕራብ ከሜዲትራንያን ምሥራቃዊ ጫፍ፣ ከስዊዝ ልሳነ - ምድርና ከቀይ ባሕር ጋር ይዋሰናል፡፡

- **አፍሪካ**

አፍሪካ በደቡብ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ (Atlantic ocean)፣ በሰሜን ከአውሮፓ፣ በምሥራቅ ከእስያ (በሜዲትራንያን ምሥራቃዊ ጫፍ፣ በስዊዝ ልሳነ ምድር እና በቀይ ባሕር አማካይነት)፣ በምዕራብ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ ጋር ይዋሰናል፡፡

- **ሰሜን አሜሪካ**

ሰሜን አሜሪካ በምሥራቅ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ፣ በደቡብ ከደቡብ አሜሪካ (በፓናማ ልሳነ ምድር አማካይነት)፣ በሰሜን ከአርክቲክ ውቅያኖስ፣ በምዕራብ ከሰላማዊ ውቅያኖስ ጋር ይዋሰናል፡፡

- **ደቡብ አሜሪካ**

ደቡብ አሜሪካ በስተሰሜን ከሰሜን አሜሪካ (በፓናማ ልሳነ ምድር አማካይነት)፣ በስተ-ደቡብ ከአንታርቲክ ውቅያኖስ፣ በስተ-ምሥራቅ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ፣ እና በስተ-ምዕራብ ከሰላማዊ ውቅያኖስ ጋር ይዋሰናል፡፡

- **አንታርክቲክ**

አንታርክቲካ ዙሪያውን በአንታርክቲክ ውቅያኖስ የተከበበ አኅጉር ነው፡፡

- **አውሮፓ**

አውሮፓን በስተምሥራቅ እስያ፣ በስተምዕራብ አትላንቲክ ውቅያኖስ፣ በስተሰሜን አርክቲክ ውቅያኖስ፣ በስተ ደቡብ የሜዲትራንያን ባሕርና አፍሪካ ያዋስኑታል፡፡

- **አውስትራሊያ**

አውስትራሊያ በምሥራቅና በሰሜን ከሰላማዊ ውቅያኖስ፣ በምዕራብ ከሕንድ ውቅያኖስ እንደሁም በደቡብ ከአንታርክቲክ ውቅያኖስ ጋር ይዋሰናል፡፡

## ለ. የአኅጉሮች ዋና ዋና ገጽታዎች

**ሠንጠረዥ 1.1 የአኅጉሮች ዋና ዋና ገጽታዎች**

| አኅጉር | ጠቅላላ ስፋት በስኩዌር ኪሎ ሜትር | ጠቅላላ የመሬት ክፍል በመቶኛ | በጣም ከፍተኛ ተራራዎች (በሜትር) | በጣም ሰፋፊ ሐይቆች (በስኩዌር ኪሎ ሜትር) | ታላላቅ ወንዞች (በኪሎ ሜትር) |
|---|---|---|---|---|---|
| እስያ | 44,810,880 | 29.9 | የኤቨረስት ተራራ 8850 | ካስፒያን ባህር 371,083 | ያንግቲዝ 2461 |
| አፍሪካ | 30,350,000 | 20.2 | የኪሊማንጀሮ ተራራ 5895 | ቪክቶሪያ ሐይቅ 96,500 | ናይል 6695 |
| ሰሜን አሜሪካ | 24,367,875 | 16.3 | የማኪንለ ተራራ 6195 | ሱፐርየር ባህር 82,435 | ሚሲሲፒ 2303 |
| ደቡብ አሜሪካ | 17,831,606 | 11.9 | የሴሮ አኩንካዋ 6977 | ቲቲካካ ባህር 8,303 | አማዞን 2483 |
| አንታርክቲካ | 14,002,590 | 9.4 | የቪንሰን ማሲፍ 5141 | – | – |
| አውሮፓ | 9,935,233 | 6.6 | የኤልብረስ ተራራ 5643 | ላዶጋ ባህር 18,373 | ቮልጋ 1361 |
| አውስትራሊያ | 8,289,000 | 5.7 | የኩሲዩስከን 2228 | ታፓ ባህር 606 | ዳርሊንግ 105 |
| ዓለም | 149,568,790 | 100.0 | ኤቨረስት 8850 | ካስፒያን ባርሕ 371,088 | ናይል 6695 |

*ምንጭ፡-* ፓውል ኖርድ ኢንግሊሽ፡- ጂኦግራፊ ሕዝቦችና ቦታዎች በተለዋዋጩ ዓለም፤ ኤንቲሲ አሳታሚ ቡድን፣ አልናይስ (የተባበሩ የአሜሪካ ኢንግሎሽ ግዛቶች፣ 1995 እ.አ.አ)



ምሥል 1.2 የኤቨረስት ተራራ

## ውስን ጥናት

**በኤቨረስት ተራራ አጠገብ የሚኖር ቤተሰብ**

የኤቨረስት ተራራ ለመወጣት የማይቻል ተደርጎ ሲታሰብ አንዳንዶች ደግሞ የመጨረሻ ፈተና ሆኖባቸው ቆይቷል፡፡ የተራራው ከፍታ 8,850 ሜትር ሲሆን የሚገኘውም በሂማሊያ በቻይና ቲቤትና በኔፓል ድንበሮች አካባቢ ነው፡፡

የኤቨረስት ተራራን መውጣት በጣም አስቸጋሪ ብቻም ሳይሆን አደገኛም ነው፡፡ ተራራውን የሚወጡ ሰዎች የተራራ ከፍታ በሚያስከትላቸው አሉታዊ ተጽእኖዎች የተራራ በሽታ(mountain sickness) የተነሣ ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ከፍተኛሥፍራ ላይ ሰዎችም ይሁኑ እጽዋት እንዲሁም ሌሎች ፍጥረታት መኖር አይችሉም፡፡ ስለዚህም ወደ ተራራው ለሚወጡ ሰዎች ምግብ ማግኘት ያስቸግራል፡፡ በዚህ የተነሣ ወደ ተራራው የሚወጡ ሰዎች አስቀድመው ምግባቸውንና ሌሎች የሚያስፈልጉአቸውን ቁሳቁሶች ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ወደ ተራራው የሚወጡ ብዙ ሰዎች ምግባቸውንና ዕቃቸውን የሚሸከሙላቸው ሽርፓ(Sherpa) በመባል የሚታወቁትን በተራራው ግርጌ የሚኖሩትን ሰዎች ይቀጥራሉ፡፡

ሽርፓዎች ከዛሬ 300 ዓመታት በፊት በደቡብ ሂማሊያ አካባቢ ከምትገኘው ከቲቤት የፈለሱ ናቸው፡፡ ሽርፓ ማለት ብዙዎች እንደሚያስቡት ዕቃ ተሸካሚ ማለት ሳይሆን የአካባቢው ሰዎች ስያሜ ነው፡፡ ወደ ሂማሊያ በሚደረገው ጉዞና ወደ ኤቨረስት ተራራ ለመውጣት ሽርፓዎች በመንገድ መሪነት የሚያገለግሉ የአካባቢውን መልክአ ምድር ጠንቅቀው የሚያውቁ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ ሽርፓዎች የቡድሃ እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡

## ውስን ጥናት

**ጉብኝት በሙት ባሕር**

ሙት ባሕር ከባሕር ጠለል በታች 400 ሜትር ጥልቀት ያለው በታላቁ ስምጥ ሸለቆ ወለል ላይ የሚገኝ የዓለማችን ዝቅተኛ ሥፍራ ነው፡፡ የሙት ባሕር አካባቢ ዳርቻዎች፣ ብሔራዊ ፓርኮች፣ ጥብቅ ሥፍራዎች በጎብኚዎች መስብህነት የታወቁ ናቸው፡፡ የሚከተሉትን ሥፍራዎች ለምሳሌ እንመልከት፡፡

- የካሊያ ዳርቻ (Kalia beach): ውኃማ የመዝናኛ ሥፍራ ሲሆን የመዋኛ ገንዳዎች ያሉትና የውኃ ላይ ውድድሮችም ይካሄዱበታል፡፡
- ኩምራን ብሔራዊ ፓርክ (Qumran National Park): ጥንታዊ የመኖሪያ አካባቢ ነበር፡፡ በኩምራን ሸለቆ አካባቢ በሚገኙ ዋሻዎች የሙት ባሕር ጥቅሎች( the Dead Sea scrolls) በመባል የሚታወቀው ጥንታዊ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን የሚያሳይ የብራና ጥቅል ተገኝቷል፡፡ በአካባቢው ሆቴሎችና የስጦታ ዕቃ መሸጫ ሱቆች ይገኛሉ፡፡
- ማሳዳ ብሔራዊ ፓርክ (Masada National Park): በአካባቢው የቅሪት አካላት ቁፋሮ የሚካሄድበት ሥፍራ ነው፡፡ የሔሮድስ ተራራ፣ ሆቴሎችና የስጦታ ዕቃ መሸጫ ሱቆች በአካባቢው ይገኛሉ፡፡
- የማዕድን ዳርቻዎች (Mineral beach): በተፈጥሮ ማዕድን የበለጸገ የመዋኛ ሥፍራ፣ የታሸጉ ጭቃዎች( mud packs) መዝናኛዎች በአካባቢው ይገኛሉ፡፡
- አሻ የጎብኝዎች ማዕከል (Ahava visitors' center): በሙት ባሕር አካባቢ ከተገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች የተቀመሙ የመዋቢያና የመድኃኒት ምርቶች፣ የመረጃ ማዕከልና የስጦታ ዕቃ መሸጫ ሱቆች በአካባቢው ይገኛሉ፡፡
- ኢኑት ዙኪም (Einut Zukim or Ein Fesh'ha): ጥብቅ የተፈጥሮ አካባቢ፣ የመዋኛ ገንዳዎችና ምንጮች፣ የመታጠቢያ ዳርቻዎችና መዝናኛዎች በአካባቢው ይገኛሉ፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች 1.1

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- የአፍሪካን አንጻራዊ መገኛ ግለጹ፡፡
- ከሰሜን አሜሪካና ከአፍሪካ በቆዳ ስፋት የትኛው ይበልጣል?
- በቆዳ ስፋት ትልቁ አኅጉር የትኛው ነው?
- በከፍታው ከዓለም ትልቁ ተራራ ማነው? ከፍታው ስንት ሜትር ነው? የት ይገኛል?

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- የዓለም ካርታ ሠርታችሁ ሰባቱን አኅጉራት አመልክቱ፡፡
- ሰባቱን አኅጉራት በቆዳ ስፋታቸው መጠን ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ በቅደም ተከተል አስቀምጧቸው፡፡

# 1.2 የዓለም ሕዝቦች

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ**

- በዓለም ላይ የሚነገሩ ዋና ዋና ቋንቋዎችን ትገልጻላችሁ፡፡
- ዋና ዋና የዓለም ቋንቋዎችን መገኛን በካርታ ላይ ታመለክታላችሁ፡፡
- ጥንታዊ የዓለም ሥልጣኔዎች ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ትገልጻላችሁ፡፡
- የጥንት ሰዎች ለዓለም ያበረከቱትን ስልጣኔዎች አስተዋጽኦ ታደንቃላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ማንዳሪን
- ሳቲን
- ኪስዋሂሊ
- ፓትሪሺያኖች

## ◈ የዓለም ዋና ዋና ቋንቋዎች


ቋንቋ የሰው ልጅ ሐሳቡን በንግግር ወይም በምልክት ወይም በጽሑፍ የሚገልጽበት ዘዴ ነው፡፡ ቋንቋ በሰው ልጆች መካከል እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ የመገናኛ ዘዴ ነው፡፡ ለመግባባትና ሐሳብን ለመግለጽ ቋንቋ ጠቃሚ ነው፡፡

በዓለማችን 6000 የሚደርሱ ቋንቋዎች ይነገራሉ፡፡ ብዙዎቹ ቋንቋዎች የሚነገሩት አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ሕዝቦች ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ አንድ ሚሊዮን ወይም ከዚያ በላይ ቁጥር ባላቸው ሕዝቦች የሚነገሩ ከ200 በላይ ቋንቋዎች ይገኛሉ፡፡ ሃያ ሦስት የሚሆኑ ቋንቋዎች ደግሞ 50 ሚሊዮን እና ከዚያ በላይ ቁጥር ባላቸው ሕዝቦች ይነገራሉ፡፡ በዓለም ላይ አገልግሎት ከሚሰጡት ዋና ዋና ቋንቋዎች ማንዳሪን፣ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሣይኛ፣ ስፓኒሽ፣ ራሽያኛና አረብኛ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

1. **ማንዳሪን፡-** በቻይና በይፋ የሚነገር ቋንቋ ሲሆን በ600 ሚሊዮን ያህል ሕዝብ ይነገራል፡፡
2. **እንግሊዝኛ፡-** በዓለም ላይ በጣም በስፋት የሚነገር ቋንቋ ነው፡፡ በብዙ ሀገሮች የእንግሊዝኛ ቋንቋ በዋነኛ ቋንቋነት ወይም በሁለተኛ ደረጃ ቋንቋነት ያገለግላል፡፡ ዛሬ 400 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ የእንግሊዝኛ ቋንቋን በዋነኛ ቋንቋነት ይናገራል፡፡ አብዛኛዎቹ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በአውስትራሊያ፣ በካናዳ፣ በታላቋ ብሪታኒያ፣ በአየርላንድ፣ በኒውዚላንድ፣ በደቡብ አፍሪካ፣ እና በተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች ይገኛሉ፡፡ ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንግሊዞች አፍሪካን፣ አውስትራሊያን፣ ሕንድንና ሰሜን አሜሪካን በአሰሳ ካገኙአቸው በኋላ ቅኝ ግዛት ካደረጉዋቸው ጀምሮ የእንግሊዝኛ ቋንቋ በመላው ዓለም ሊስፋፋ ችሎአል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ዓለም አቀፋዊ ቋንቋ በመሆን ያገለግላል፡፡ የሥራ እና የዓለም አቀፍ ግንኙነት ቋንቋም በመሆን በመላው ዓለም በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡
3. **ፈረንሣይኛ፡-** በፈረንሣይ በስፋት የሚነገር ቋንቋ ነው፡፡ እንዲሁም በቤልጂየም፣ በካናዳ፣ በሀይቲ፣ በሉክሰምበርግ፣ በስዊዘርላንድና በተባበሩት መንግስታት በይፋ የሚነገር ቋንቋ ነው፡፡ ከ90 ሚሊዮን የሚበልጥ ሕዝብ ፈረንሣይኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋው ይጠቀምበታል፡፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሌሎች ሕዝቦች ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ቋንቋነት ይገለገሉበታል፡፡
4. **ስፓኒሽ፡-** በስፔን በስፋት የሚነገር ቋንቋ ነው፡፡ እንዲሁም በብዙ የደቡብ አሜሪካ ሀገሮች ስፓኒሽ በይፋ የሚነገር ቋንቋ ነው፡፡ በመላው ዓለም 297 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ የስፓኒሽ ቋንቋ ይናገራል፡፡

5. **ራሽያኛ፡-** በራሽያ በስፋት የሚነገር ቋንቋ ነው፡፡ 153 ሚሊዮን የሚገመት ሕዝብ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ይጠቀምበታል፡፡ ራሽያኛ በአውሮፓ በስፋት ከሚነገሩት ቋንቋዎች በሦስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት ከሚነገሩት ስድስት የሥራ ቋንቋዎች አንደኛው ነው፡፡

6. **አረብኛ፡-** በዓለም ላይ በስፋት ከሚነገሩ ቋንቋዎች አንዱ ነው፡፡ በመካከለኛው ምሥራቅ እና በሰሜን አፍሪካ በሚገኙ የአረብ ሀገሮች በይፋ የሚነገር ቋንቋ ነው፡፡ እነዚህ የአረብ ሀገሮች ግብፅ፣ ኢራቅ፣ ዮርዳኖስ፣ ሊባኖስ፣ ፍልስጤም፣ ሳውዲ አረቢያና ሶርያ ናቸው፡፡




*ምሥል 1.3 የቋንቋዎች ሥርጭትን የሚያሳይ የዓለም ካርታ*

## ውስን ጥናት

**ኦዲንጋ**

ኦዲንጋ የኩኩዮ ተወላጅ ሲሆን የሚኖረው በኬንያ ሞምባሣ ነው፡፡ ኦዲንጋ በቤት የኩኩዮ ቋንቋ ይናገራል፡፡ የተለያዩ ነገሮችን ለመግዛት ወደ አካባቢው ገበያ ሲሄድ ደግሞ የኪሲዋሂሊ ቋንቋ ይናገራል፡፡ ትምህርቱን የሚማረው ደግሞ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው፡፡ ኦዲንጋ አብረውት የሚማሩ ከዩጋንዳ፣ ከታንዛኒያ፣ ከሩዋንዳ እና ከኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ የመጡ ጥቂት ጓደኞች አሉት፡፡ ሁሉም የኪስዋሂሊ ቋንቋ ይናገራሉ፡፡ የኪስዋሂሊ ቋንቋ በብዙ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት በስፋት ይነገራል፡፡ ስለዚህም የቋንቋው ተናጋሪዎች በክልሉ በቀላሉ ለመንቀሳቀስና ለመግባባት ይችላሉ፡፡ ኦዲንጋም ከተለያዩ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ከመጡት ጓደኞቹ ጋር በቀላሉ ይግባባል፣ ይማራል እንዲሁም በጋራ ያጠናል፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች 1.2**

**ክንውን ሀ**

***በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- በዓለም በጣም ብዙ ተናጋሪ ያሉት ቋንቋ የትኛው ነው?
- አንድ ሚሊዮን ወይንም ከዚያ በላይ ተናጋሪዎች ያሉዋቸው ስንት ቋንቋዎች አሉ?
- ፈረንሳይኛ ብሔራዊ ቋንቋቸው የሆኑ ሀገሮችን ስም ጻፉ፡፡
- የደቡብ አሜሪካ ሀገሮች በይፋ የሚናገሩት ቋንቋ ምን ተብሎ ይጠራል?
- የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሚገለገልባቸውን ቋንቋዎች ስም ጻፉ፡፡
- የአረብኛ ቋንቋን በስፋት የሚጠቀሙ የመካከለኛ ምሥራቅ ሀገሮችን ስም ጻፉ፡፡

## ◈ ጥንታዊ የዓለም ሥልጣኔዎች

- በዓለም ጥንታዊ ሥልጣኔ የነበራቸው ጥቂት ሀገራት እነማን ናቸው?

### 1. ጥንታዊት ግሪክ

- ምዕራባዊ ሥልጣኔ የተጀመረው በየትኛው ሀገር ነው?

ምዕራባዊ ሥልጣኔ የተጀመረው ከ2500 ዓመታት በፊት በጥንታዊ ግሪክ ነበረ፡፡ ሥልጣኔው ያደገው በግሪክ ከተሞች ነበር፡፡ የጥንታዊ ግሪክ ከተሞች ራሳቸውን የቻሉ ነጻ መንግሥታት ነበሩዋቸው፡፡

የግሪክ ከተሞች በመጀመሪያ የነበራቸው አስተዳደር በጥቂት ኃያላን ሰዎች የሚመራ ነበረ፡፡ እ.አ.አ በስድስተኛው መቶ ዓመተ ዓለም አንዳንድ የግሪክ ከተሞች ለመጀመሪያ ጊዜ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን በሥራ ላይ አውለዋል፡፡ መላው የግሪክ ዜጎች፣ ከሴቶችና ከባርያዎች በስተቀር የመምረጥና የመመረጥ መብት ነበራቸው፡፡ እንዲሁም የፖለቲካና የዳኝነት ሥልጣን መያዝ ይችሉ ነበር፡፡ በሥልጣኔያቸው የታወቁት የግሪክ ከተሞች **አቴንስ** እና **እስፓርታ** ነበሩ፡፡

**አቴንስ** ሰፊ የቆዳ ሽፋንና ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር የነበራት ታላቅ የግሪክ ጥንታዊ ከተማ ነበረች፡፡ አቴንስ በጥንታዊ ግሪክ ዋነኛዋ የዲሞክራሲ ሥርዓት ማዕከል ነበረች፡፡ የአቴንስ ዲሞክራሲ ቀጥተኛ ደሞክራሲ እንጂ በውክልና የሚመራ ዲሞክራሲ አልነበረም፡፡ ይህም ማለት መላው የአቴንስ ከተማ ዜጎች በአንድ ላይ ተሰብስበው ከተወያዩ በኋላ ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ ይህንን የመሰለው ስብሰባ ሸንጎ በመባል ይታወቅ ነበር፡፡

በተጨማሪም አቴንስ የግሪክ የባሕል ማዕከል ነበረች፡፡ ፍልስፍና የተጀመረው በጥንታዊቷ ግሪክ ነበር፡፡ በጥንታዊ ግሪክ የነበሩ ሦስቱ ታዋቂ ፈላስፋዎች ሶቅራጥስ፣ አፍላጦንና አርስጣጣሊስ (Socrates, Plato, Aristotle) ይባላሉ፡፡ የተውኔት ጽሑፎችን ለመጀመሪያ ጊዜ የጻፉት ጥንታዊ ግሪኮች ናቸው፡፡ ጥንታዊውን የዓለም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የጻፈው ታዋቂው ግሪካዊ ሔሮዱቶስ «የታሪክ አባት» በመባል ይታወቃል፡፡ ጥንታዊ ግሪኮች በሒሣብ፣ በፊዚክስ፣ በሥነ ፈለግ፣ በጂኦግራፊ እና በሕክምና ሙያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ በሕክምና ሙያ የታወቀው ሒፖክራተስ «የሕክምና አባት» በመባል ይታወቃል፡፡

የጥንታዊ ግሪኮች የሥነ-ሕንፃ ጥበብ በአሁኑ ዘመን ለሚገነቡ ሕንጻዎች ሞዴል በመሆን ያገለግላል፡፡

ዘመናዊው የኦሎምፒክ ስፖርት ውድድር የተወሰደው ጥንታዊ ግሪኮች ኦሎምፒያ በተሰኘ ቦታ በየአራት ዓመቱ ያካሄዱት ከነበረው የስፖርት ወድድር ነው፡፡



ምሥል 1.4 የጥንታዊ ግሪክ ሥነ - ሕንፃ



ምሥል 1.5 የዲስከስ ወርዋሪ ሀውልት

## 2. ጥንታዊት ሮም

- **በዓለም ላይ የመጀመሪያውን ሕዝባዊ መንግሥት (ሪፐብሊክ) የመሠረቱት የትኞቹ ሕዝቦች ነበሩ?**

የመጀመሪያዎቹ ሮማውያን ላቲኖች ነበሩ፡፡ የሮም ሰዎች እ.ኤ.አ በ500 ዓ.ዓ. አካባቢ የሮማውያን ሪፐብሊክ (ሕዝባዊ መንግሥት) አቋቋሙ፡፡ የሪፐብሊኩ መሪዎች የሀገር ጉዳይ ጠባቂ (Consul) በመባል ይታወቁ ነበር፡፡ የሮም ሕዝቦች በሦስት ዋና ዋና መደቦች ይከፈሉ ነበር፡፡ እነርሱም:-

- መሳፍንቶች (ፓትሪሺያኖች)
- ባለመሬቶች (ኤኩቴስ)
- ተራው ሕዝብ (ፕሌቢያኖች) ናቸው፡፡

- መሳፍንቶች (ፓትሪሺያኖች) የሚባሉት በጣም ብዙ ሀብት የነበራቸው ሰዎች ናቸው፡፡
- ባለመሬቶች (ኤኩቴስ) የሚባሉት ሀብት የነበራቸው ነገር ግን መሳፍንቶች ያልሆኑ ናቸው፡፡
- ተራው ሕዝብ (ፕሌቢያኖች) የተባሉት ደሃ አርሶ አደሮች፣ የዕደ ጥበብ ሠራተኞች፣ አነስተኛ ነጋዴዎችና የቀን ሠራተኞች ነበሩ፡፡

እ.ኤ.አ በ270 ዓ.ዓ. አካባቢ ሮም ቀስ በቀስ እየተስፋፋች አብዛኛውን የኢጣሊያን ክፍል ለመቆጣጠር በቅታለች፡፡ በጥንት ዘመን የሮማውያን መንግሥት በመላው ዓለም በጣም የታወቀ ወታደራዊ መንግሥት ነበረ፡፡ የጥንታዊት ሮም ዝነኛ ወታደራዊ መሪ ጁልዮስ ቄሣር በመባል ይታወቃል፡፡

## ውስን ጥናት

### የጥንታዊት ሮም ሥልጣኔ

ሮማውያን እ.አ.አ በ509 ዓ.ዓ. የነበረውን ንጉሣዊ አገዛዝ አስወግደው በምትኩ ሕዝባዊ መንግሥት አቋቋሙ፡፡ ከዚያ በኋላ ሁሉም ዜጎች መሪዎቻቸውን በነጻ መምረጥ ችለዋል፡፡፡ የተመረጡት መሪዎችም የመረጣቸውን ሕዝብ በመወከል በሕዝቡ ስም ያስተዳድሩ ነበር፡፡ ይህ ሕዝባዊ መንግሥት በቆየባቸው 500 ዓመታት ሮም ከአንዲት አነስተኛ ከተማነት ተነሥታ በዓለም ላይ ኃያል መንግሥት ለመሆን በቅታለች፡፡

የሮም ሕዝባዊ መንግሥት በተመሠረተበት ወቅት አብዛኛዎቹ የሮም ኑዋሪዎች ፓትሪሽያን በተባሉ ጥቂት የመሬት ከበርቴዎች ተፅዕኖ ሥር ወድቀው ነበር፡፡ እርሶ አደሮች፣ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎችና አነስተኛ ነጋዴዎች የሚገኙበት የተራው ሕዝብ መደብ የማስተዳደር ሥልጣን አልነበረውም፡፡ በኅብረተሰቡ ዝቅተኛውን ሥፍራ ይዘው የሚገኙት ባሮች የዜግነት መብት አልነበራቸውም፡፡

እ.አ.አ በ27 ዓ.ዓ ላይ የሮማውያን ሕዝባዊ መንግሥት በሮማውያን ንጉሠ-ነገሥታዊ መንግሥት (Empire) ተለወጠ፡፡ አውግስጦስ ቄሣር የመጀመሪያው ንጉሠ-ነገሥት ነበር፡፡



ምሥል 1.6 ጥንታዊ ሮማዊ

ሮማውያን ለዓለም ሥልጣኔ የራሳቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ የሮማውያን ሕጎች ለብዙ የምዕራብ አውሮፓና የደቡብ አሜሪካ ሕጎች መሠረት ናቸው፡፡

ሮማውያን ሥነ-ሕንጻ ግንባታና በመንገድ ሥራ ከፍተኛ ሥልጣኔ ነበራቸው፡፡ አውሮፓውያን የላቲን ፊደላትን ያገኙት ከጥንታዊ ሮማውያን ነው፡፡ ለብዙ አውሮፓውያን ቋንቋዎች ዕድገት መሠረቱ የሮማውያን ላቲን ቋንቋ ነው፡፡

### 3. ጥንታዊት ቻይና

- በጥንታዊ ቻይና ታላቁ ግንብ የታነጸበት ምክንያት ምን ነበረ?

የጥንታዊት ቻይና ሥልጣኔ የተጀመረው በቢጫ ወንዝ ሸለቆ (Yellow River valley) ነበር፡፡ በጥንታዊት ቻይና የመጀመሪያው ሥርወ-መንግሥት የሻንግ ሥርወ መንግሥት ይባላል፡፡ የሻንግ ነገሥታት መግዛት የጀመሩት እ.አ.አ በ1700 ዓ.ዓ ገደማ ነበረ፡፡ በሻንግ ሥርወ መንግሥት ዘመን ቻይናውያን የአጻጻፍ ሥርዐት፣ የቀን መቁጠሪያ እና የተሻሻለ የነሐስ ሥራ ጥበብ ለዓለም አበርክተዋል፡፡ ጥንታዊ ቻይናውያን የራሳቸው የአጻጻፍ ዘዴ ነበራቸው፡፡ የጥንታዊ ቻይናዎች የአጻጻፍ ዘዴ ሎጐግራፊክ በመባል ይታወቃል፡፡ ሎጐግራፊክ ሥዕላዊ የአጻጻፍ ዘዴ ነበር፡፡ የጥንታዊ ቻይና የዕደ-ጥበበ ባለሙያዎች ጦርና ጩቤ የመሳሰሉትን መሣሪያዎች ከነሐስ ይሠሩ ነበረ፡፡



ምስል 1.7 ታላቁ የቻይና ግንብ

ከምዕራብ ቻይና የመጡ ቺን የተባሉ ሕዝቦች የሻንግ መሪዎችን ከሥልጣን አውርደው የራሳቸውን ሥርወ-መንግስት መሠረቱ። በቺን ዘመነ መንግሥት በቻይና ውስጥ የመሬት ከበርቴን ሥርዐት የሚደግፍ መንግሥት ተመሥርቶ ነበር። በቺን ዘመን ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገትና የንግድ እንቅስቃሴ በመፈጠሩ የከተሞች ዕድገት ታይተዋል። ቻይናውያን ከብረት ማዕድን የተሠራ ገንዘብ (ሣንቲም) በገበያ ላይ በመጠቀማቸው የንግዱ እንቅስቃሴ ሊስፋፋ ችሏል።

በቻይና የፍልስፍና ዕውቀት የተጀመረው በቺን ሥርወ መንግስት ዘመን ነበር። ታዋቂው የቻይና ፈላስፋ ኮንፊሺየስ በመባል ይታወቃል። የኰንፊሺየስ ፍልስፍና ኰንፊሺያኒዝም ይባላል። በመሠረቱ ኰንፋሺያኒዝም ፍልስፍና እንጂ ሃይማኖት አይደለም።

የጥንታዊ ቻይናውያን ሥልጣኔ ለዓለም ሕዝብ ከፍተኛ ጥቅም ነበረው። ለመጀመሪያ ጊዜ የድንጋይ ከሰል ጥቅም ላይ እንዲውል ያደረጉት ጥንታዊ ቻይናውያን ነበሩ። ልዩ ልዩ የሸክላ ዕቃዎች (ሣህኖች፣ ስኒዎች) እና የዕቃ መጫኛ ጋሪዎች በመጀመሪያ የተሠሩት በቻይናውያን ነው። የሐር ጨርቅ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሠራው በቻይና ሲሆን እ.ኤ.አ በ105 ዓ.ም አካባቢ ወረቀት ሠርተው ለዓለም አበርክተዋል። ቻይናን ከሞንጎላውያን ወረራ ለመከላከል እ.ኤ.አ በ200 ዓ.ዓ አካባቢ ሥራው የተጠናቀቀው ታላቁ የቻይና ግንብ ርዝመቱ ከ2400 ኪሎ ሜትሮች በላይ እንደሆነ ይገመታል።

ጥንታዊ የቻይና ነጋዴዎች ከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች እንዲሁም በቀይ ባሕርና በምሥራቅ አፍሪካ ባሕር ዳርቻ ከሚገኙ ሀገሮች ጋር የጠበቀ የንግድ ግንኙነቶች ነበራቸው። የሐር፣ ጨርቅና ልዩ ልዩ የሸክላ ዕቃዎች ዋነኛ ሸቀጦች ነበሩ። በምሥራቅ አፍሪካ ዳርቻ በቅሪተ አካላት ቁፋሮ የተገኙት ቻይና ሠራሽ የሸክላ ዕቃዎች በጥንታዊ ቻይና እና በምሥራቅ አፍሪካ መካከል የጠበቀ የንግድ ግንኙነት እንደነበረ ያስረዳሉ።

## ውስን ጥናት

**የቺን ሥርወ-መንግሥት**


ኢ.አ.አ በ195 ዓ.ዓ. አካባቢ ቻይና እርስ በርሳቸው በሚዋጉ ሰባት ግዛቶች የተከፋፈለች ሀገር ነበረች፡፡ በምዕራባዊ ቻይና ቺን የተባለው ሕዝብ መሪ የነበረው ሹር ሁዋንግ ዲን የተከፋፈሉትን ግዛቶች አንድ በማድረግ የመጀመሪያው የቻይና ንጉሠ-ነገሥት ለመሆን በቅቷል፡፡ ሹር ሁዋንግ ዲን ቻይናን በሰሜናዊ አቅጣጫ ከሚያጠቁ የሞንጎልያ ወራሪዎች ለመከላከል ከ2400 ኪሎ ሜትሮች በላይ ርዝመት ያለውን ታላቁ የቻይና ግንብ ገንብቷል፡፡ በተጨማሪም በመላው የቻይና ግዛት በጥቅም ላይ የዋለ የጋራ መገበያያ ገንዘብ እና የክብደት መለኪያ ሚዛን በሥራ ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡

### 4. ጥንታዊት ፐርሺያ

ጥንታዊት ፐርሺያ የነበረችበት ሥፍራ የዛሬዎቹን ከፊል ኢራንና ከፊል አፍጋኒስታንን ያጠቃልላል፡፡ ጥንታዊ ፐርሺያኖች ሀገራቸውን የአርያኖች ሀገር እያሉ ይጠሩ ነበር፡፡ ኢራን የሚለው ስም የተገኘው ከዚሁ አርያን ከሚለው የሕዝብ መጠሪያ ነው፡፡ ፐርሺያኖች የሚናገሩት ቋንቋ አርያን በመባል ይታወቃል፡፡

የጥንታዊት ፐርሺያ መሥራች ታላቁ ንጉሥ ሣይረስ ነበር፡፡ የፐርሺያ ነገሥታት ፈላጭ ቆራጭ ሥልጣን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ነገሥታቱ አሁራ ማዝዳ ተብሎ ለሚጠራው የፐርሺያኖች አምላክ ተጠሪ በመሆን ያገለግሉ ነበር፡፡ ጥንታዊ ፐርሺያኖች ገበሬዎች ነበሩ፡፡ ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ እና ልዩ ልዩ ቅጠላ ቅጠሎችን ለማምረት የሚያስችላቸውን የመስኖ ሥራ ይጠቀሙ ነበረ፡፡ የፐርሺያ ነጋዴዎች የተለያዩ ሸቀጦችን ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች በማምጣት በሜዲትራኒያን ባሕር አካባቢ ለሚገኙ ሀገሮች ያሠራጩ ነበረ፡፡ ዳሪክስ በመባል የሚታወቅ ከወርቅ የተሠራ ገንዘብ በመላው የፐርሺያ ግዛት አገልግሎት ይሰጥ ነበረ፡፡

የፐርሺያኖች ሃይማኖት መጠሪያ ዞሮአስትሪያኒዝም በመባል ይታወቃል፡፡ መሥራቹም ዞሮኦስተር የተባለ ነቢይ ነበረ፡፡




*ምስል 1.8 ፐርሺያ*

### 5. ጥንታዊ የኢንካ ሥልጣኔ

ኢንካ የደቡባዊ አሜሪካ ሕንድ ዝርያዎች ናቸው፡፡ የጥንታዊ ኢንካ ሕዝቦች በደቡብ አሜሪካ በጣም በሀብት የበለፀገ መንግሥት ነበራቸው፡፡

እ.ኤ.አ ከ1438 ዓ.ም. ጀምሮ የኢንካ መንግሥት በመስፋፋቱ፣ በደቡባዊ ፔሩ የምትገኘውንና ኩዝኮ በመባል የምትታወቀውን ዋና ከተማ ማዕከል ያደረገ በጣም ሰፊ ግዛት ያስተዳድር ነበረ፡፡ የኢንካ መንግሥት የዛሬዎቹን ኮሎምቢያን፣ ኢኳዶርን፣ ፔሩን፣ ቦሊቪያን፣ ቺሊንና አርጀንቲናን ያጠቃልል ነበረ፡፡ እ.አ.አ በ1532 ዓ.ም. የስፔን ወራሪ ኃይል የኢንካን መንግሥት አሸንፎ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎታል፡፡

የኢንካ ሰዎች በምህንድስና ጥበብና በተለያዩ የዕደ ጥበብ ሥራዎቻቸው ይታወቃሉ፡፡ እርስ በእርሳቸው የተጠላለፉ መንገዶችን ከመሥራታቸውም በላይ ግዙፍ በሆነው የሥነ ሕንፃ አሠራራቸው ይታወቃሉ፡፡ የኢንካ የዕደ-ጥበበ ባለሙያዎች የተዋቡ ቁሳቁሶችን ከወርቅ፣ ከብርና ከሌሎች ነገሮች ያዘጋጁ ነበረ፡፡ ውብ የሆነ ከጥጥና ከሱፍ ፀጉር የተሰሩ አልባሳትን ያዘጋጃሉ፡፡ ከዋና ዋናዎቹ የኢንካ እርሻ ውጤቶች መካከል በቆሎ፣ ጥጥና ድንች ወዘተ ይገኙባቸዋል፡፡

በኢንካ ኅብረተሰብ ቀሳውስት ዓይነተኛ ሚና ነበራቸው፡፡ የኢንካ ቄሶች የተለያዩ ዕፅዋትንና ተክሎችን በመጠቀም ሕሙማንን ይፈውሱ ነበረ፡፡ የኢንካ ሰዎች የተለያዩ አልባሳትን እንደ መገበያያ ገንዘብና እንደ ስጦታም ጭምር ይጠቀሙ ነበረ፡፡




*ምስል 1.9 የጥንቱ የኢንካ ሥልጣኔ*

## የክለሳ ጥያቄዎች 1.2

**ክንውን ለ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

1. **የሚከተሉትን ግለጹ**

| | | |
|---|---|---|
| - ሶቅራጥስ | - ላቲኖች | - የሻንግ ሥርወ መንግስት |
| - አፍላጦን | - ዞሮ አስተር | - የቺን ሥርወ መንግስት |
| - አርስጣጣሊስ | - ታላቁ ሣይረስ | - ኰንፉሺየስ |
| - ሔሮዱቶስ | - አሁራ ማዝዳ | - የአሜሪካ ሕንዶች |
| - ሒፖክራተስ | - አውጉስጦስ ቄሣር | |

2. **የሚከተሉትን ግለጹ**
   - ኮንፊሺያኒዝም
   - ዳሪክስ
   - ዞሮአስትሪያኒዝም

3. **የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**
   - የኢንካ መንግሥት የሚገኘው የት ነበረ?
   - በአሁኑ ዘመን የሚገኙ መንግሥታት እንደ ጥንታዊ ግሪኮች ቀጥተኛ ዲሞክራሲ የማይተገብሩት ለምንድን ነው?

- ጥንታዊ ቻይናውያን ለዓለም ካበረከቷቸው የፈጠራ ሥራዎች ሦስቱን ግለጹ፡፡
- የኢንካን ዋና ዋና ሥልጣኔዎችን ግለጹ፡፡
- የአቴናውያን መንግሥት ዲሞክራሲያዊ ገጽታዎች ምን ነበሩ?
- ቀጥተኛ ዲሞክራሲን ግለጹ፡፡
- ሔሮዱቶስ “የታሪክ አባት” የተባለው ለምን ነበረ?
- በጥንታዊ ግሪክ የታዩትንና ከዚህ በታች የሚኙትን የመንግሥት ዓይነቶች ግለጹ፡፡
  ሀ. የጥቂት ኃያላን ሰዎች አገዛዝ
  ለ. ዲሞክራሲ
- ሁለት ጥንታዊ የግሪክ ከተሞችን ስም ጻፉ፡፡
- ፓትሪሺያኖች እና ፕሌቢያኖች እነማን ነበሩ?
- የሀገር ጉዳይ ጠባቂዎች (consuls) ምን ነበሩ?
- ሮማውያን ለዘመናዊው ሥልጣኔ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ምን ነበረ?
- በሻንግ ዘመነ-መንግስት ከተሠሩት የፈጠራ ሥራዎች መካከል ሦስቱን ግለጹ፡፡
- ከጥንታዊት ቻይና የፈጠራ ስራዎች መካከል አምስቱን ጻፉ፡፡

## 1.2.1 በዓለም የሚገኙ ሃይማኖቶች

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ**

- የዓለም ዋና ዋና ሃይማኖቶችን ሥርጭት ትገልጻላችሁ፡፡
- የሌሎች ሃይማኖቶችን እኩልነት ትገልጻላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- **ኦሪት (ቶራ)**
- **ሒጅራ**
- **ዓ.ዓ (ዓመተ ዓለም)**

### ◈ የዓለም ዋና ዋና ሃይማኖቶች

በዓለም ላይ የሚገኙ ሃይማኖቶች የይሁዲ፣ የሒንዱይዝም፣ የቡዲሂዝም፣ የሺንቶይዝም፣ የእስልምና እና የክርስትና ሃይማኖቶች ናቸው፡፡

1. **ይሁዲ (Judaism)፦** ይህ ሃይማኖት የአይሁድ ወይም የእስራኤላውያን ሃይማኖት ነው፡፡ በዓለም ላይ በጣም ጥንታዊ ሃይማኖት ነው፡፡ የይሁዲ ሃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ አምላክ ማመንን ያስተማረ ሃይማኖት ነው፡፡ የይሁዲ ሃይማኖት ትምህርት የሚመነጨው ኦሪት (ቶራ) በመባል ከሚታወቁት በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚገኙት የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት ውስጥ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች የይሁዲ እምነት ተከታዮች ይገኛሉ፡፡

2. **ሒንዱይዝም፡-** በሕንድ የሚገኝ ሃይማኖት ነው፡፡ በዓለም ላይ ከሚገኙት አንጋፋ ሃይማኖቶች አንዱ ሒንዱይዝም ነው፡፡ ሒንዱይዝም የሃይማኖት መመሪያ የሚሆን መጽሐፍ የለውም፡፡ የሰው ነፍስ እንደማይሞትና የሰው አካል ሲሞት ነፍስ እንደገና እንደሚፈጠር ያስተምራል፡፡ ይህ ቀጣይ ዳግም ልደት ሂደት (Reincarnation) ወይንም እንደገና መፈጠር በመባል ይታወቃል፡፡



*ምስል 1.10 ሲቫ በመባል የሚታወቀው የሒንዱ የጭፈራ (ዳንስ) አምላክ*

3. **ቡዲሂዝም፡-** የተመሠረተው እ.ኤ.አ በ500 ዓ.ዓ አካባቢ ሕንድ ውስጥ ሲዳሃርታ ጉታማ በተባለ ሰው ነበር፡፡ ተከታዮቹ ቡድሀ ብለው ይጠሩት ነበረ፡፡ ትርጓሜውም “ብሩሁ” ማለት ነው፡፡ ቡድሀ ብዙ አማልክት ማምለክን ይቃወም ነበረ፡፡ ቡዲሂዝም ከሕንድ ውጭ በይበልጥ የተስፋፋው በቻይና፣ በጃፓን፣ በኮሪያ፣ በካምቦዲያ፣ በላኦስ፣ በማይናማር፣ በታይላንድ፣ እና በቬትናም ነው፡፡ በተጨማሪ በርካታ የቡዲሂዝም ተከታዮች በቲቤት፣ በኔፓል፣ በስሪላንካ እና በሞንጉሊያ ይገኛሉ፡፡




*ምሥል 1.11 የቡዲይዝም ምልክት*

4. **ሺንቶይዝም፡-** ይህ ሃይማኖት በጃፓን የሚገኝ አንጋፋ ሃይማኖት ነው፡፡ ሺንቶ የሚለው የጃፓንኛ ቃል ትርጓሜ “የአማልክት መንገድ” ማለት ነው፡፡ ሺንቶይዝም በብዙ አማልክቶች ያምናል፡፡ "ከሞት በኋላ ሕይወት" የሚሰኘውን እምነት አይቀበልም፡፡ በሺንቶይዝም እምነት መሠረት የጃፓን ንጉሣዊ ቤተሰብ የመጣው ከፀሐይ አምላክ ነው፡፡
5. **እስልምና፡-** የተመሠረተው በነቢዩ መሐመድ ትምህርት ላይ ነው፡፡ ነቢዩ መሐመድ የተወለዱት እ.አ.አ በ570 ዓ.ም. በመካ ከተማ ነው፡፡ ነቢዩ መሐመድ የእስልምናን ሃይማኖት ያስተማሩት በአንድ አምላክ በአላህ ብቻ በማመን ነው፡፡

የመካን ከተማ ይቆጣጠር የነበረው ኩረይሽ የተባለው ነገድ አባላት የነቢዩ መሐመድን ትምህርት በመቃወም እ.አ.አ በ622 ዓ.ም. ነቢዩ መሐመድን ለመግደል ሲሞክሩ መሐመድ መካን ለቀው ወደ መዲና ከተማ ተጉዘዋል፡፡ ይህ ነቢዩ መሐመድ ከመካ ወደ መዲና ያደረጉት ጉዞ ሒጅራ በመባል ይታወቃል፡፡

የእስልምና የዘመን አቆጣጠር የሚጀምረው ከሒጅራ ነው፡፡

የእስልምና ሃይማኖት በመካከለኛው ምሥራቅ፣ ሰሜናዊ አፍሪካ እና በእስያ ተስፋፍቷል፡፡ ከክርስትና ሃይማኖት ቀጥሎ በዓለም ላይ ብዙ ተከታዮች ያሉት ሃይማኖት እስልምና ነው፡፡

### 6. ክርስትና፡-

የክርስትና ሃይማኖት የተመሠረተው በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ላይ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ በመካከለኛው ምሥራቅ በምትገኘው በምድረ እሥራኤል በቤተልሔም ከተማ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ አምላክ ማመንን አስተምሯል፡፡

**በክርስትና ሃይማኖት የዘመን አቆጣጠር የሚጀምረው ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በመነሣት ሲሆን አቆጣጠሩም ዓመተ ምሕረት ይባላል፡፡**

### ማስታወሻ

ማንኛውም ሰው የሃይማኖት ነፃነት አለው፡፡ የ1987 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት፣ አንቀጽ 27 ማንኛውም ሰው የማሰብ የሕሊና እና የሃይማኖት ነፃነት እንዳለው ያረጋግጣል፡፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነቱን ለብቻ የመቀበል መብት እንዳለውና ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተባበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብት እንዳለው ያረጋግጣል፡፡

አንድ ዜጋ የራሱ እምነት ስራሱ የሚያረካውን ያህል ሌላውም ዜጋ በራሱ እምነት የሚረካ መሆኑን አውቆና ተቀብሎ ጣልቃ አለመግባት፣ አለማንቋሸሽና እኩል እንደሆነ መመልከት ይጠበቅበታል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች 1.2.1

***በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

***1. የሚከተሉትን ቦታዎች ግለጹ፡፡***

- እስራኤል
- ሕንድ
- ጃፓን
- መካ
- ፍልስጤም
- መዲና

***2. የሚከተሉትን ግለጹ፡፡***

- ቶራ
- እንደገና መፈጠር
- ቡድሀ
- ሒጅራ
- ዓመተ ምሕረት

***3. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡***

- የሒንዱይዝም ሃይማኖት መሠረታዊ ትምህርት ምንድን ነው?
- ሺንቶ የሚለውን ቃል አብራሩ፡፡

# 1.3 የሕዝብ ሥርጭትና አኗኗር

## 1.3.1 ሕዝብ ተበታትኖና ተጠጋግቶ የሚኖርባቸው ቦታዎችን ማነጻጸር

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ**

- ሕዝብ በጣም ተጠጋግቶና ተበታትኖ የሚኖርባቸውን የዓለም አካባቢዎች ትለያላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- የተበታተነ የሕዝብ ሥርጭት
- የተጠጋጋ የሕዝብ ሥርጭት
- ሞቃት በረሃ
- ቀዝቃዛ በረሃ

- በተበታተነና በተጠጋጋ የሕዝብ ሥርጭት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

### የተበታተነ የሕዝብ ስርጭት ያላቸው አካባቢዎች

ለኑሮ አመቺ ያልሆነ የአየር ንብረት ያላቸው አካባቢዎች ሕዝብ በብዛት ያልሠፈረባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡ እነዚህ አካባቢዎች ቀዝቃዛ እና ሞቃት በረሃዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡

### ሞቃት በረሃዎች (Hot deserts)

ሞቃት በረሃዎች፡- የውኃ እጥረት የሚታይባቸው በጣም ሞቃትና ደረቅ አካባቢዎች ናቸው፡፡ ዓመታዊ የዝናብ መጠናቸው ከ250 ሚሊ ሜትር በታች ሲሆን አማካይ ዓመታዊ ሙቀታቸው ደግሞ ከ16°.6 ሲልሽየስ (30° ፋራናይት) ይሆናል፡፡ አብዛኛዎቹ ሞቃት በረሃዎች የሚገኙት የአኅጉሮች ምዕራባዊ ጠረፍ አካባቢ ከምድር ወገብ ከ15° - 30° ሰሜን ወይም ደቡብ ኬክሮስ ነው፡፡ ሞቃት በረሃዎች የሚባሉት

- የሰሜን አፍሪካው፡- ሰሐራ በረሃ
- የመካከለኛ እስያው፡- ጐቢ በረሃ
- የደቡብ እስያው (ሕንድ)፡- ታር በረሃ
- የመካከለኛው አውስትራሊያው ታላቁ የአውስትራሊያ በረሃ
- የደቡብ አሜሪካው፡- አታካማ በረሃ
- የመካከለኛ ምሥራቁ፡- አረቢያን በረሃ
- የተባበሩት አሜሪካ ግዛቶች ምዕራዊ ክፍል ኮሎራዶ በረሃ ናቸው፡፡




*ምሥል 1.12 ሞቃት በረሃዎች*

### ቀዝቃዛ በረሃዎች

ቀዝቃዛ በረሃዎች በሰሜን ንፍቀ ክበብ ብቻ የሚገኙ ሲሆን በሰሜን አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ እስያና የአርክቲክ ውቅያኖስ አዋሳኝ ዝቅተኛ ቦታዎችን ይሸፍናሉ፡፡ በቀዝቃዛ በረሃዎች ለስድስት ወራት ያህል አማካይ ወርኃዊ ሙቀት ከ6° ሴልሸየስ በታች ነው፡፡ የአካባቢው ቀዝቃዛ አየር ብዙ ርጥበት የመሸከም አቅም ስለሌለው የአካባቢው ዝናብ አነስተኛ ነው፡፡ ስለዚህም ቀዝቃዛ በረሃዎች አብዛኛውን ጊዜ በበረዶ የተሸፈኑ በጣም ቀዝቃዛና ዛፍ አልባ አካባቢዎች ናቸው፡፡ ቱንድራ በሚል ስምም ይጠራሉ፡፡

### ጥቅጥቅ ያለ የሕዝብ ክምችት ያላቸው አካባቢዎች

ጥቅጥቅ ያለ የሕዝብ ክምችት ያላቸው አካባቢዎች የሚባሉት በአነስተኛ ቦታ ከአንድ ስኩዌር ካሬሜትር ባልበለጠ ሥፍራ በጣም ብዙ ሕዝብ ሠፍሮ የሚገኝባቸው ቦታዎች ናቸው፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑት


- በአፍሪካ የናይል ሸለቆ
- በእስያ ሕንድና ቻይና ናቸው፡፡

### የናይል ሸለቆ

በአፍሪካ የናይል ሸለቆ በተለይ በደለል የተሞላው የናይል ወንዝ ዳርና ዳር ያለው ለጥ ያለ ሜዳ (Nile delta) ከፍተኛ የሕዝብ ክምችት የሚገኝበት አካባቢ ነው፡፡ ይኸ የአፍሪካ ክፍል በአንድ ስኩዌር ኪሎሜትር ውስጥ እስከ 600 ሰው የሚኖርበት አካባቢ ነው፡፡ ዘጠና አምስት በመቶ የሚደርሰው የግብጽ ሕዝብ የሚኖረው ሃያ ኪሎ ሜትር በሚሆነው በወንዙ ዳርቻ አካባቢ ነው፡፡ ሕዝቡ በባሕላዊና ዘመናዊ የመስኖ ዘዴ እየተጠቀመ የተለያዩ ሰብሎችን እያመረተ ኑሮውን ይገፋል፡፡

## የቻይና፣ የሕንድ፣ የፓኪስታን እና የጃፓን አካባቢ

በዓለም ውስጥ ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት ያለው በእስያ በተለይ በምሥራቅ ቻይና ነው፡፡ በቻይና የሕዝብ ጥግግት የሚታየው በያንግቲዝ ወንዝ ላይ ባሉ ሜዳዎች እና በማንቹርያ ሜዳዎች አካባቢ ነው፡፡ የቻይና አጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር 1.3 ቢሊዮን ገደማ ነው፡፡ ይኸም ማለት በዓለም ከሚገኝ ሕዝብ ከአምስት ሰው አንዱ ቻይናዊ ነው ማለት ነው፡፡ የጃፓን ሕዝብ ቁጥር 126,475,664 ሲሆን የሕዝብ ጥግግቱም 539 ሕዝብ በአንድ ስኩዌር ኪሎ ሜትር ነው፡፡ ሌላው የተጠጋጋ የሕዝብ ጥግግት የሚገኘው በሕንድና ምሥራቅ ፓኪስታን አካባቢ ነው፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት የሚገኘው በጋንጀስ ወንዝ አካባቢ ነው፡፡ ሕዝቡ በመስኖ አማካኝነት ከፍተኛ ሩዝ ያመርታል፡፡




*ምሥል 1.13 የዓለም የሕዝብ ስርጭት ካርታ*

## ውስን ጥናት

### የኢንዊት ወይም ኢስኪሞ ቤተሰብ

ኢንዊቶች ወይም ኢስኪሞዎች የሚኖሩት የአርክቲክ አዋሳኝ ዝቅተኛ ቦታዎችን ይዞ በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮፓና በእስያ አካባቢዎች ነው። አካባቢው ቱንድራ በመባል ይታወቃል።
የቱንድራ አካባቢ የአየር ንብረትን ማወቅ ሕዝቦች በዓለም ዙሪያ ለምን በኩል ደረጃ እንዳል ሠፈሩ ወይም እንዳልተሰራጩ ለመረዳት ያስችለናል። የቱንድራ አካባቢ የአየር ንብረት ለሰው ልጆች ኑሮ አመቺ አይደለም። ሙቀቱ ዝቅተኛ (በጣም ቀዝቃዛ) የዝናብ መጠኑም አነስተኛ ነው። አፈሩም ቢሆን ዓመቱን ሙሉ በበረዶ የተሸፈነ ነው። በአጠቃላይ አካባቢው ለእርሻ ሥራ የማይስማማ ደን አልባ አካባቢ ነው። ስለዚህም የኑዋሪዎች ቁጥር አነስተኛ ነው።

በአካባቢው ሕይወት በጣም አስቸጋሪ ነው። በጋው በጣም ረዥም፣ ጨለማና ቀዝቃዛ ነው። የሙቀት መጠኑ ከ $-40^{\circ}$ ፋራናይት ($-20^{\circ}$ ሴሊሸስ) ወይንም ከዚያ በታች ሊሆን ይችላል። ወደ አካባቢው መሄድ ከባድ ነው። መንገድ ወይንም ባቡር በአካባቢው ባለመኖሩ የሕዝቡ ግንኙነት ውስን ነው። አንዳንድ ጊዜ ምግብና ሌሎች ሸቀጦችን ለማመላለስ የሚያገለግሉ ጀልባዎችም የባሕሩ ውኃ ወደ በረዶነት ስለሚለጠጥ ሊቆሙ ይችላሉ። በዚህ የተነሣ የምግብና የሸቀጦች ዋጋ ውድ ነው። ስለዚህም የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ የተመሠረተው በአደንና አሳ ማጥመድ ስራ ላይ ነው።

ኢንዊቶች በካናዳና አላስካ ኤስኪሞስ በመባል ሲታወቁ በሳይቤሪያ (ሰሜን ሩስያ) አካባቢ ደግሞ ቶንጉሲስ፣ ቹኩቺ ወ.ዘ.ተ በሚሉ መጠሪያዎች ይታወቃሉ። ኢንዊቶች ኑሮአቸው የተመሠረተው በአደንና አሳ በማጥመድ ስራ ነው። የአደኗቸውን እንስሳት ቆዳ በመሸጥ በምትኩ ለአደን የሚራዷቸውን ዘመናዊ መሣሪያዎች ይገዛሉ። የኤስኪሞዎች አሠፋፈር በጣም የተበታተነ ነው። ቤታቸውንም የሚሠሩት በግግር በረዶ ሲሆን "ኢግሉ" በሚል ስም ይጠራል። በበጋ ወራት ከሲልና ከካረቡ (የሰሜን አሜሪካ የደጋ አጋዘን) ቆዳ በሚሠሩ ድንኳኖች ወይም በሸራ ድንኳኖች ውስጥ ይኖራሉ።

ከቀዝቃዛው የአርክቲክ ውቅያኖስ ውስጥ ሰላሞን፣ ኮድ እና አስናባሪ የሚባሉትን የአሣ ዓይነቶች ያጠምዳሉ። ከመሬት ላይ በበጋ ወራት የደጋ አጋዘን ሲያድኑ በክረምት ወራት ደግሞ ዋልታዊ ጥንቸል (Hare) ያድናሉ። ይሁን እንጂ ተወዳጅ ምግባቸው የሲል፣ የካረቡ፣ የደጋ አጋዘን ሥጋ እና የምርስ (walrus) ጉበት ናቸው። ኤስኪሞዎች በልብስነት የሚጠቀሙት የካሪቡ ቆዳና የዋልታ ድብ ለስለሳ ፀጉር ነው።

በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው ኤስኪሞዎች ኑሮአቸው ተለውጧል። በከተሞችና አነስተኛ መንደሮች መኖር ጀምረዋል። አለባበሳቸውም ዘመናዊ ሆኖአል። ዘመናዊ ቤትም ውስጥ ይኖራሉ። የምግብ ሸቀጣቸውንም ከምግብ መሸጫ መደብሮች ይገዛሉ። በበረዶ ላይ የሚንሸራተቱ ጋሪዎችን ትተው በሞተር ጀልባ መጓዝ ጀምረዋል። በአሁኑ ጊዜ አብዛኞዎቹ ኤስኪሞዎች በተለያዩ መስኮች ተቀጥረው ደመወዝ የሚከፈላቸው ሠራተኞች ሆነዋል።



ምሥል 1.14 ኤስኪሞ

## ውስን ጥናት

### በሙምባይ የሚኖር ቤተሰብ

ሙምባይ ቀድሞ ቦምቤ በመባል የምትታወቅ የሕንድ አንድ ከተማ ናት፡፡ ከጠቅላላ ነዋሪዋ መካከል ሃምሣ አራት ነጥብ አምስት በመቶ የሚሆነው የሚኖረው በወዳደቁና ችምችም ባሉ ቤቶችና ንጽሕና በጎደለው አካባቢ ተፋፍገው በተሠሩ ቤቶች ነው፡፡

በሕንድ ትላልቅና ዘመናዊ ከተሞች ያረጁና የተጎሳቆሉ መንደሮች (slums areas) ሃምሣ አራት በመቶ ይሆናሉ፡፡ ይሁን እንጂ የሙምባይን ያህል የሕዝብ ጥግግት ያለው መንደር የለም፡፡ ስለዚህም በሙምባይ የመኖሪያ ቤቶችና የአካባቢ ጽዳት ጉዳይ አሳሳቢ ችግር ነው፡፡

የሙምባይ ከተማ ነዋሪ ከገጠሩ ሕዝብ የበለጠ የኑሮ ጫና አለበት፡፡ በሙምባይ ጥቂት የወደብና የፋብሪካ ሠራተኞች ቢኖሩም የተቀረው ሕዝብ ግን የዕለት ተዕለት ኑሮውን ለማሸነፍ በተለያየ የሥራ መስክ ተሠማርቶ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ የእጅ ሥራ ባለሞያዎች ከብረት፣ ከዝሆን ጥርስ፣ ከቆዳና ከሐር የተሠሩ ምርቶችን ለገበያ ያቀርባሉ፡፡ ይሁን እንጂ ገቢያቸው ለኑሮአቸው የሚበቃ አይደለም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ እባብ በማላመድና በማሰልጠን (Snake charmers) እባቡ በሙዚቃ እየተመራ ከወዲያ ወዲህ በመንቀሳቀስ ትርኢት እንዲያሳይ በማድረግ ከአላፊ አግዳሚው ገንዘብ ይሰበሰባሉ፡፡ በሙምባይ ከተማ ሰፋፊ መንገዶችና ዘመናዊ ሱቆች የመኖራቸውን ያህል በጣም ጠባብ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ከደሳሳ ቤቶች ጋር ይገኛሉ፡፡ የእጅ ባለሙያዎች የጥበብ ሥራዎች የሚሸጡባቸው አነስተኛ ሱቆችም በስፋት የሚገኙት በእነዚህ አካባቢዎች ነው፡፡



ምስል 1.15 የሙምባይ ከተማ

## የክለሳ ጥያቄዎች 1.3.1

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች?***

- የሕዝብ ሥርጭት ምን ማለት ነው?
- በሕዝብ ሥርጭትና በሕዝብ ጥግግት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
- በተበታተነና በተጠጋጋ የሕዝብ ጥግግት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
- በዓለም ዙሪያ የተበታተነና የተጠጋጋ የሕዝብ ጥግግት ያላቸው ቦታዎችን ዘርዝሩ፡፡

***ለ. የቡድን ሥራ***

ተማሪዎች ሁለት ቡድኖችን በመመስረት አንደኛው ቡድን በዓለም ዙሪያ የተበታተነ የሕዝብ ጥግግት ያላቸውን ቦታዎች በተመለከተ፣ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ የተጠጋጋ የሕዝብ ጥግግት ያላቸውን ቦታዎች በተመለከተ መረጃ አሰባስቡ፡፡ በመቀጠል የተሰበሰበውን መረጃ በየተራ አቅርባችሁ ተወያዩበት፡፡

***ሐ. የግል ሥራ፡-***

- የዓለም ካርታ በመሥራት ሕዝብ ተበታትኖና ተጠጋግቶ የሚኖርባቸውን ቦታዎች አመልክቱ፡፡

## 1.3.2 ለዓለም ሕዝቦች ሥርጭት መለያየት ምክንያቶች

***ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት***

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ**

- ➢ የዓለም የሕዝብ ሥርጭት የተለያየበትን ምክንያት ታብራራላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- **ማኅበራዊ ምክንያት**
- **ተፈጥሮአዊ ምክንያት**

በዓለም ላይ የሕዝብ ስርጭት ከቦታ ወደ ቦታ የተለያየ ነው፡፡ የሕዝብ ስርጭት ልዩነትን የሚያስከትሉ ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ◈ ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች

**ሀ. የአየር ንብረት**

ሕዝብ በአንድ ቦታ ተጠጋግቶ የሚሠፍረው በአካባቢው መካከለኛ ሙቀት፣ አስተማማኝና በቂ የዝናብ መጠን ሲኖርና ለኑሮው ምቹ ሁኔታ ሲፈጠርለት ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ አካባቢ በጣም ቀዝቃዛ ወይም በጣም ደረቅ ከሆነ ለኑሮ አመቺ ስለማይሆን ብዙ ሕዝብ አይሠፍርበትም፡፡

### ለ. የመሬት መልክአምድራዊ አቀማመጥ ሁኔታ

የመሬት መልክአምድራዊ አቀማመጥ የሕዝብ ስርጭቱን ሊያበረታታ ወይንም ሊያደክም ይችላል፡፡ ከወጣ ገባ አካባቢዎች ይልቅ ሜዳማ አካባቢዎች የሕዝብ በብዛት መከማቸትን ይፈጥራሉ፡፡

### ሐ. የለም አፈርና የእፅዋት መኖር

ሕዝብ በአንድ አካባቢ በከፍተኛ ጥግግት ለመሠፈር የአፈሩ ለምነትና የአካባቢው በእፅዋት መሸፈን የጐላ ሚና አላቸው፡፡ በተቃራኒው በአረንጓዴ ተክሎች ያልተሸፈነ እና ለም አፈር የሌለበት ቦታ ብዙውን ጊዜ ለመኖሪያ አካባቢነት አይመረጥም፡፡

## ◈ ማኅበራዊ ምክንያቶች

ምጣኔ ሀብታዊ፣ የቴክኖሎጂ የእድገት ደረጃ፣ ማኅበራዊና ፓለቲካዊ አደረጃጀቶች የባህል ልዩነቶችን ያስከትላሉ፡፡ ስለዚህም ማኅበራዊ ምክንያቶች በሕዝብ ስርጭት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡፡ ጦርነትና የእርስ በእርስ ግጭትም የሕዝብ ሥርጭትን ይወስናል፡፡ የተሻሻሉ የመገናኛ አውታሮች ያሏቸው ሥፍራዎችና የባሕር ዳርቻዎች ብዙ ሕዝብ የሚሠፍርባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡ በተመሳሳይ የማዕድን ሀብት በቁፋሮ የሚወጣባቸው አካባቢዎችም ሕዝብ በብዛት የሚሠፍርባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች 1.3.2

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች:-***

- *የሕዝብ ሥርጭትን የሚወስኑ ዋና ዋና ተፈጥሮአዊና ማኅበራዊ ምክንያቶች ምን ምንድናቸው?*
- *ተፈጥሮአዊ ወይም ማኅበራዊ ምክንያቶች በተናጠል የሕዝብ ሥርጭትን ሊወስኑ የማይችሉበትን ምክንያት አስረዱ፡፡*

***ለ. የቡድን ውይይት***

- *ግማሽ የሚያህለው የዓለም ሕዝብ አምስት በመቶ በሚሆነው በመሬት የቆዳ ስፋት ላይ ብቻ እንደሠፈረ ይገመታል፡፡ በተቃራኒው ሃምሣ ሰባት በመቶ የሚሆነው የመሬት የቆዳ ስፋት የያዘው አምስት በመቶ የሚሆነውን የዓለም ሕዝብ ነው፡፡ ይኽ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን ተወያዩ፡፡*
- *የተጠጋጋ እና የተበታተነ የሕዝብ አሠፋፈር ያለባቸው ሥፍራዎች በተፈጥሮአዊ አካባቢ ሁኔታም ሆነ በምጣኔ ሀብት ዕድገት ተቃራኒ ገጽታ ይታይባቸዋል፡፡ ይህንን በተመለከተ ተወያዩበት፡፡*

***ሐ. የሚሠሩ ተግባራት***

- *የኢትዮጵያ ካርታ ሠርታችሁ የተጠጋጋና የተበታተነ የሕዝብ ሥርጭት ያለባቸውን ቦታዎች አመልክቱ*

## 1.3.3 የዓለም ሕዝቦች አኗኗር

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ**

- በዓለም ላይ የሚገኙትን የተለያዩ የአኗኗር ዘይቤዎች ታደንቃላችሁ፡፡
- አኗኗራችሁን ከሌሎች ሕዝቦች አኗኗር ጋር ታነጻጽራላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- በግብርና ላይ የተመሠረተ አኗኗር
- በኢንዱስትሪ ላይ የተመሠረተ አኗኗር
- በንግድና በአገልግሎት ሰጭነት ላይ የተመሠረተ አኗኗር

- የሕዝቦች አኗኗር ስንል ምን ማለታችን ነው?
- ዋና ዋና የዓለም ሕዝብ የአኗኗር ዘይቤዎችን ዘርዝሩ፡፡

መልክአ ምድር፣ የአየር ንብረት፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ የምጣኔ ሀብት ዕድገት፣ የቴክኖሎጂ ደረጃና የማኅበረሰብ የዕድገት ደረጃ በሕዝቦች የአኗኗር ዘይቤ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አላቸው፡፡ ቀጥሎ በዓለማችን የሚታዩ ዋና ዋና የአኗኗር ዘይቤዎችን እንመለከታለን፡፡

### ◈ በግብርና ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ

አብዛኛው የዓለም ሕዝብ በተለያየ የአኗኗር ዘይቤ የሚተዳደር ቢሆንም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በግብርና ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በከተማ ወይም በኢንዱስትሪ ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ ያላቸው ሕዝቦች ምግባቸውን የሚያገኙት ከግብርና ነው፡፡ በሰው ልጅ ታሪክ ለምግብና ለኢንዱስትሪ ጥሬ ሀብት የሆኑ ምርቶች የሚገኙት አኗኗራቸውን በግብርና ላይ መሠረት ካደረጉ ሕዝቦች ነው፡፡ ከዓለማችን ግማሽ የሚያህለው ሕዝብ የአኗኗር ዘይቤው የተመሠረተው በግብርና ላይ ነው፡፡ በአፍሪካና በእስያ ደግሞ ከሰማንያ በመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝብ ኑሮው የተመሠረተው በግብርና ላይ ነው፡፡ በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ ደግሞ በግብርና የሚተዳደረው ሕዝብ ከሁለት በመቶ አይበልጥም፡፡ በዓለማችን በግብርና ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ የተጀመረው ከሺህ ዓመታት በፊት ነው፡፡

ግብርና በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የተለያየ ምርት፣ የአመራረት ዘይቤና የአኗኗር መሠረት አድርጎ የሚካሄድ በመሆኑ ተፈጥሮአዊውን አካባቢና የመሬት ገጽታን በከፍተኛ ሁኔታ በመለወጥ ላይ ይገኛል፡፡ የግብርና ሥራ እርሻና የከብት እርባታ ተብሎ ይከፈላል፡፡ በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የሚኖረው አብዛኛው ሕዝብ የሚተዳደረው በእርሻ ላይ ሲሆን የተወሰነው ሕዝብ የሚኖረው ደግሞ በከብት እርባታ ነው፡፡ የሐሩር ሞቃታማ አካባቢ ዝቅተኛ ሥፍራዎች ለከብት እርባታ አመቺ ሲሆኑ አምባ ምድሮችና ከፍተኛ ሥፍራዎች ደግሞ ለእርሻ ሥራ ተስማሚ በመሆናቸው የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ የተመሠረተው በእርሻ ላይ ነው፡፡

በግብርና ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ ያላቸው ሕዝቦች ምርታቸው ከእጅ ወደ አፍ ነው፡፡ የአኗኗር ዘይቤያቸው በቀጥታ በተፈጥሮ አካባቢ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በአየር ንብረት ለውጥና በተለያዩ ሰው ሠራሽና

ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ሳቢያ የተለያዩ ፈታኝ ሁኔታዎች እያጋጠማቸው ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የግብርና ምርቶች ገበያ ዋጋ ዝቅተኛ በመሆኑ በኢንዱስትሪ የበለጸጉ ሀገራት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የበኩላቸውን ተጽእኖ እያሳደሩ ይገኛሉ፡፡ በግብርና ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ ያላቸው ሕዝቦች አኗኗራቸው፣ አለባበሳቸውና አሠራራቸው በሌሎች ዘርፎች ከሚኖሩት ሕዝቦች የተለየ ነው፡፡

### ◈ በኢንዱስትሪ ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ

ጥሬ ዕቃዎችን ወደ አለቀላቸው የፍጆታ ሸቀጥነት የመቀየር ሥራ እንዲሁም በጣም ውስብስብና የረቀቁ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን የተለያዩ ክፍሎች የመገጣጠም ሥራ የፋብሪካ ወይም የኡንዱስትሪ ሥራ ይባላል፡፡ በዓለም በሰሜን አሜሪካ፣ በምዕራብ አውሮፓና በሩቅ ምሥራቅ እስያ የሚኖረው አብዛኛው ሕዝብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ አኗኗሩ የተመሠረተው በኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ ላይ ነው፡፡ ደረጃውና ብዛቱ ዝቅተኛ ቢሆንም በሌላው የዓለም ክፍልም በኢንዱስትሪ ላይ በተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ የሚኖር ሕዝብ አለ፡፡

አኗኗራቸው በኢንዱስትሪ ላይ የተመሠረተ ሕዝቦች በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች በማምረትና በመሸጥ ወይንም ተቀጥረው በሚያገኙት ገቢ ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን የፍጆታ ዕቃዎች ያሟላሉ፡፡ ስለዚህም በግብርና ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ ካላቸው ሕዝቦች ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ እንዲሁም ለምግብ ፍጆታ የሚውሉ የግብርና ውጤቶችን በንግድ ልውውጥ ያገኛሉ፡፡ ይህም በኢንዱስትሪ ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ ያላቸው ሕዝቦች በግብርና ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ ካላቸው ሕዝቦች ጋር ያላቸውን ትስስርና መደጋገፍ ያሳያል፡፡

### ◈ በንግድና በሌሎች የአገልግሎት ዘርፎች ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ

ንግድ በሰዎች ወይንም በሀገራት መካከል የሚደረግ የምርት ልውውጥ ነው፡፡ የንግድ እንቅስቃሴ ፍላጎትንና አቅርቦትን መሠረት አድርጎ የሚከናወን ሂደት በመሆኑ በገዢና በሻጭ መካከል ትስስር ይፈጥራል፡፡ የመጓጓዣ አገልግሎት ደግሞ የምርት ልውውጡን በማሳደግ የተሳካ የንግድ ሂደት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ በገጠርና በከተማ እንዲሁም በበለጸጉና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት በንግድ ልውውጥ ሂደት የተለያዩ አገልግሎቶችን ለምሳሌ የተሽከርካሪ አቅርቦት፣ የመጫንና የማራገፍ፣ ምርትን የመቀበልና የማሠራጨት፣ የምግብና የመኝታ አገልግሎት፣ የጥገና አገልግሎትና የመሳሰሉትን በመስጠት በሚያገኙት ገቢ ኑሯቸውን የመሠረቱ በርካታ ሕዝቦች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሕዝቦች በኢንዱስትሪ ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ ካላቸው ሕዝቦችና በግብርና ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ ካላቸው ሕዝቦች ጋር ጥብቅ ትስስርና መደጋገፍ አላቸው፡፡ ይህም የዓለም ሕዝብ አኗኗር ምን ያህል የተሳሰረና የሚደጋገፍ መሆኑንና የአንዱ መኖር ለሌላው መኖር አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች 1.3.3**

*ሀ. በእውቀት ላይ  የተመሠረቱ ጥያቄዎች፡-*

- በዓለም በስፋት የሚታየው የአኗኗር ዘይቤ የተመሠረተው በምን ላይ ነው?
- በምዕራብ አውሮፓና በሰሜን አሜሪካ በስፋት የሚታየው የአኗኗር ዘይቤ ምን ይባላል?
- በግብርና እና በኢንዱስትሪ ላይ በተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ መካከል ያለውን ቁርኝት አስረዱ፡፡

***ለ. የቡድን ውይይት***

ተማሪዎች ሦስት ቡድን አቋቁሙ፡፡ እያንዳንዱ ቡድን የመኖሪያ አካባቢውን በመጐብኘት የሕዝቡን የአኗኗር ዘይቤ ያቅርብ፡፡ ከዚያም የቡድን ተጠሪዎች የጥናቱን ውጤት ለክፍል ተማሪዎች እያቀረቡ የጋራ ውይይት ይደረግበት፡፡ በመጨረሻም በውይይቱ ላይ የተነሡትን ቁም ነገሮች በቅደም ተከተል በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

***ሐ. የግል ሥራ***

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ሕዝቦች የአኗኗር ዘይቤ የተመሠረተው በምን ላይ ነው? ለምን በዚህ የአኗኗር ዘይቤ እንደሚተዳደሩ ዋና ዋና ምክንያቶችን ዘርዝራችሁ ጻፉ፡፡

***መ. የሚሠሩ ተግባራት***

- የዓለም ካርታን በመሥራት በግብርና እንዲሁም በኢንዱስትሪ ላይ የተመሠረተ የአኗኗር ዘይቤ ያላቸውን አካባቢዎች አመልክቱ፡፡

## 1.3.4 የኢንዱስትሪ አብዮትና ያስከተለው ውጤት

***ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት:-***

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ**

- ብሔርተኝነትና ቅኝ አገዛዝ ለኢንዱስትሪ አብዮት መፈጠር የነበራቸውን አስተዋጽኦ ታደንቃላችሁ፡፡
- የኢንዱስትሪ አብዮት የት እንደተጀመረ ትለያላችሁ፡፡
- የአፍሪካን ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል ታስረዳላችሁ፡፡
- የአፍሪካውያንን ስኬታማ ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግልን በምሳሌ ትገልጻላችሁ፡፡
- የአንደኛና የሁለተኛ የዓለም ጦርነቶች ውጤት ታስረዳላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- **አብዮት**
- **የእንፋሎት ኃይል**
- **ብሔርተኝነት**
- **ብዙኃንነት**
- **ነጻነት**

### 1.የኢንዱስትሪ አብዮት አጀማመር

- የኢንዱስትሪ አብዮት ምንድን ነው?

የኢንዱስትሪ አብዮት በማምረት ሂደት ላይ የተደረገ መሠረታዊ ለውጥ ነው፡፡ በእጅ ከማምረት ይልቅ በማሽን ማምረት የተጀመረበት ሒደት ነው፡፡ እንዲሁም በመኖሪያ ቤት ከማምረት ይልቅ በፋብሪካ ውስጥ ማምረት የተጀመረበት ወቅት ነው፡፡

የኢንዱስትሪ አብዮት የተጀመረው በ18ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በእንግሊዝ ሀገር ነው፡፡ በዚያ ሀገር ሊጀመር የቻለበት ምክንያት በቂ የድንጋይ ከሰል እና የብረት ማዕድን ክምችት ስለነበረ ነው፡፡

## የኢንዱስትሪ አብዮት ደረጃዎች


የኢንዱስትሪ አብዮት በሁለት ደረጃዎች ይከፈላል፡፡ የመጀመሪያው ደረጃ እ.አ.አ ከ1750ዎቹ እስከ 1870ዎቹ ዓ.ም ሲዘልቅ፣ ሁለተኛው ደረጃ ደግሞ እ.አ.አ በ1870ዎቹ ዓ.ም ተጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ ቀጥሏል፡፡

## የኢንዱስትሪ አብዮት የመጀመሪያው ደረጃ

- **የኢንዱስትሪ አብዮት በተጀመረበት ወቅት ዋነኛው የኃይል ምንጭ ምን ነበረ?**

በመጀመሪያው ደረጃ ወቅት በእጅ የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ለመተካት የሚያስችሉ አዳዲስ ማሽኖች ተሠርተዋል፡፡ በዚህ ወቅት ዋናው የኃይል ምንጭ የእንፋሎት ኃይል ነበረ፡፡ እንፋሎት የሚገኘው ውኃን በከሰል በማፍላት ነው፡፡

የአዳዲስ ማሽኖች መሠራት የተለያዩ ቁሳቁሶችን በተሻለ መንገድ ለማምረት አስችሏል፡፡ እ.ኤ.አ በ1764 ዓ.ም. ጀምስ ሐርግሬቭስ የተባለ ሰው ስፒኒንግ ጄኒ በመባል የሚታወቀውን የፈትል መሣሪያ ሠርቷል፡፡ ይህ መሣሪያ በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የሚካሄደውን የሽመና ሥራ በከፍተኛ ሁኔታ ሊያፋጥነው ችሏል፡፡ እ.ኤ.አ በ1760 ዎቹ ዓ.ም. ደግሞ ጀምስ ዋት በእንፋሎት ኃይል የሚንቀሳቀስ ሞተር ሠርቷል፡፡ በእንፋሎት ኃይል የሚንቀሳቀስ የመጀመሪያው ሞተር ታቅዶ የተሠራው ከከሰል ማዕድን ጉድጓድ ውስጥ ውኃ እንዲመጥ ተደርጎ ነበረ፡፡ የድንጋይ ከሰል በእንፋሎት ለሚሠራው ሞተር ኃይል ሰጪ ከመሆኑም በላይ ብረትን ለማቅለጥም ይጠቅማል፡፡ ብረት ደግሞ የተለያዩ ማሽኖችንና ቁሳቁሶችን መሥሪያ ዓይነተኛው ጥሬ ዕቃ ከመሆኑም በላይ ድልድዮችንና መርከቦችን ለመሥሪያ ያገለግላል፡፡ በእንፋሎት ኃይል የሚንቀሳቀሱ ባቡሮችና ጀልባዎች በመሠራታቸው የመጓጓዣ ዘዴ ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል፡፡ የመጀመሪያው ባቡር የተሽከረከረው በእንግሊዝ ሀገር እ.አ.አ በ1825 ዓ.ም በስቶክተን እና በዳርሊንግተን ከተሞች መካከል በተዘረጋው የባቡር ሀዲድ ላይ ነበረ፡፡



*ምሥል 1.16 ጥሬ ጥጥ ወደ ክር ተቀይሮ ለልብስ መሥሪያ ሲዘጋጅ*

### የኢንዱስትሪ አብዮት ሁለተኛው ደረጃ

በኢንዱስትሪ አብዮት በሁለተኛው ደረጃ ዋናው የኃይል ምንጭ ከእንፋሎት ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ ነዳጅ እና አቶሚክ ኃይል ተቀይሯል። ሚካኤል ፋራዳይ የተባለ እንግሊዛዊ ዲናሞ በመባል የሚታወቅ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት የሚችል መሣሪያ ሠርቷል። ይህ መሣሪያ በተለያዩ ፋብሪካዎች በእንፋሎት ኃይል የሚንቀሳቀሰውን ሞተር ተክቷል።

የመገናኛ ዘዴዎችም ታላቅ መሻሻል ታይቶባቸዋል። ለምሳሌ እ.አ.አ በ1876 ዓ.ም. አሌክሳንደር ግራሀም ቤል ስልክ ሠርቷል። እ.ኤ.አ በ1899 ዓ.ም. ደግሞ ገሊልሞ ማርኮኒ ሬዲዮ ሠርቷል።

### 2. የኢንዱስትሪ አብዮት ውጤቶች

የኢንዱስትሪ አብዮት ሁለት ዋና ዋና ውጤቶች አሉት። ***የመጀመሪያ*** ውጤት በኅብረተሰቡ የአኗኗር ሁኔታ ላይ የታየው ለውጥ ነው። ይኸውም በምጣኔ ሀብት፣ በማኅበራዊ እና በፖለቲካ ዘርፎች የተፈጠረ ለውጥ ነው።

**ሀ. ምጣኔ ሀብታዊ ለውጥ፤** አዳዲስ ማሽኖች ተሠርተው ጥቅም ላይ በመዋላቸው የሰውን ልጅ ድካም ቀንሰዋል። ይህም ከፍተኛ መጠን ያላቸውን ሸቀጦች በዝቅተኛ ወጪና በቀላል ዘዴ ለማምረት አስችሏል። ኢንዱስትሪዎች ዋነኛዎቹ የምርት ማዕከላት እንዲሆኑ አስችሏል። የመገናኛና የመጓጓዣ ዘዴዎችም እየተሻሻሉ መጥተዋል።

**ለ. ማኅበራዊ ለውጥ፤** የማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት መስፋፋት ለከተሞች ማደግ ምክንያት ሆኖአል። በርካታ ሰዎች በከተሞች በተስፋፉት ፋብሪካዎችና የንግድ ድርጅቶች ተቀጥረው ለመሥራት ከገጠር ወደ ከተሞች ፈልሰዋል። ይህም ቀስ በቀስ በከተሞች የሚኖረው የሕዝብ ቁጥር እንዲጨምር አስተዋጽኦ አድርጓል። እያደገ የመጣው የከተማ ሕዝብ ብዛት ለሁለት መሠረታዊ መደቦች መፈጠር ምክንያት ሆኗል። እነርሱም

- **የባለሀብቱ (capitalist) መደብ፡-** የተለያዩ ፋብሪካዎች ባለቤቶችና ሀብታም ነጋዴዎችን የያዘ መደብ ነው።
- **የሠራተኛ መደብ፡-** በየፋብሪካው ተቀጥረው የሚሠሩ ላብ አደሮችን የያዘ መደብ ነው።

  የባለሀብቱ መደብ አባላት ተጨማሪ ትርፍ ለማግኘት በማሰብ ሴቶችንና ሕጻናትን በጣም ዝቅተኛ በሆነ ክፍያ ያሠሩዋቸው ነበረ። የሠራተኛው መደብ አባላት የሚገኙበት አስከፊ የኑሮና የሥራ ሁኔታ፣ በጣም ዝቅተኛ ክፍያ እንዲሁም ለረጅም ሰዓት መሥራታቸው ለመብታቸው እንዲታገሉ አስገድዷቸዋል። ትግላቸውንም በተቀነባበረ ሁኔታ የሚመሩ የሠራተኛ ማኅበራት አቋቁመዋል።

**ሐ. ፖለቲካዊ ለውጥ፡-** የባለሀብቱ መደብ አባላት በፖለቲካው መስክ ወሳኝ ሚና መጫወት በመቻላቸው የፖለቲካ ሥልጣኑን በእጃቸው አስገብተዋል።

የኢንዱስትሪ አብዮት ያስከተለው ***ሁለተኛው*** ውጤት እ.አ.አ በ19ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ የተጀመረውን የአውሮፓውያን ቅኝ አገዛዝ ነው። አውሮፓውያን ሌሎች ሀገራትን በቅኝ ግዛት ለመያዝ የተነሡት በሚከተሉት ምክንያቶች ነበር።

ሀ) ለኢንዱስትሪዎቻቸው ጥሬ ዕቃ ለማግኘት

ለ) ለኢንዱስትሪዎቻቸው ምርት ገበያ ለማግኘት

ሐ) በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን ሕዝባቸውን ለማሥፈር በቂ ቦታ ለማግኘት ነበር።



**እ.ኤ.አ በ1914 ዓ.ም. ሰባት የአውሮፓ ሀገሮች 115 በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮችን በቅኝ አገዛዝ ሥር አውለው ነበር።**

### 3. የአዲስ አስተሳሰቦች መታየት

የኢንዱስትሪ አብዮት እ.አ.አ በ19ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን የሕዝቦች የብሔርተኝነት ስሜት ወይም የሀገር ፍቅር ስሜት እንዲፈጠር አስችሏል፡፡ የአንድ ሀገር ሕዝብ ብሔርተኝነት የሚገለጸው ተመሳሳይ በሆነ ሀገራዊ ዝንባሌ፣ ለአንድነት በመቆምና፣ ከባዕድ አገዛዝ ነጻ ሆኖ ለመገኘት ቁርጠኝነት በማሳየት ነው፡፡ በተጨማሪም በትውልድ ሀገር የኩራት ስሜት በማሳየትና የሀገርን ብልፅግናና ዕድገት በመመኘት ይገለጻል፡፡

በአጠቃላይ በኢንዱስትሪ በበለፀጉ ሀገሮች የተስፋፉት ሌሎች አዳዲስ አስተሳሰቦች ማለትም ነጻ አስተሳሰብ (ሊበራሊዝም) ዲሞክራሲና የመድብለ ፓርቲ ሥርዐት መኖር (pluralism) ናቸው፡፡

- **ሀ. ነጻ አስተሳሰብ (Liberalism):-** በመባል የሚታወቀውን ሐሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያራመደው ጆን ሎቴዋርት ነው፡፡ ነጻ አስተሳሰብ (liberalism) ማለት በንግግር ነጻነት፣ ሒስ በማድረግ፣ በሃይማኖት ነጻነትና መንግሥት በሕዝብ ቁጥጥር ሥር በመዋሉ ማመን ነው፡፡
- **ለ. ዲሞክራሲ:-** የተጀመረው በጥንታዊ ግሪክ ነበረ፡፡ በግሪክ ቋንቋ “ዲሞስ” ማለት ሕዝብ ማለት ሲሆን “ክራሲያ” ደግሞ መንግሥት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ዲሞክራሲ ማለት በሕዝብ የተቋቋመ መንግሥት ማለት ነው፡፡ እ.ኤ.አ ከ1860 እስከ 1865 ዓ.ም. የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንት የነበሩት አብርሃም ሊንከልን ዲሞክራሲን ሲገልጹ፡፡ “የሕዝብ፣ በሕዝብ እና ለሕዝብ የተቋቋመ መንግሥት” ብለውታል፡፡
- **ሐ. የመድብለ - ፓርቲ ሥርዐት መኖር (Pluralism):-** የካፒታሊስት ሥርዓት - ማኅበር የዲሞክራሲ ዋነኛ ገፅታ ነው፡፡ ፕሉራሊዝም ሲገለጽ የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት፣ ሃይማኖት ወይንም ዘር ያላቸው ሰዎች በአንድ በተወሰነ ሕብረተሰብ ውስጥ በአንድነት ሲኖሩ ነው፡፡ ፕሉራሊዝም በፖለቲካ አስተሳሰብ ውስጥ የመድብለ ፓርቲ ፖለቲካ ሥርዐት መኖር ማለት ነው፡፡

## ◈ አንደኛውና ሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች

አንደኛው የዓለም ጦርነት የተካሄደው እ.ኤ.አ ከ1914 - 1918ዓ.ም. ነበር፡፡ ለጦርነቱ መቀስቀስ የተለያዩ ምክንያቶች ነበሩ፡፡

- **አንደኛው የዓለም ጦርነት ለምን ተጀመረ?**

### ለአንደኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስ መሠረታዊ ምክንያቶች

#### ሀ. በኢምፔሪያሊስት ኀይሎች መካከል የነበረ ፉክክር

ለአንደኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስ ከሚጠቀሱት መሠረታዊ ምክንያቶች አንዱ በአውሮፓ ሀገሮች መካከል የነበረው ምጣኔሀብታዊና የፖለቲካ ፉክክር ነበረ፡፡ ለሀገሮቹ መፎካከርና ግጭት መነሻ የነበረው ጥሬ ዕቃ፣ ገበያ እና ግዛት ለማግኘት የሚደረገው እሽቅድምድም ነበር፡፡ በመጨረሻም ፉክክሩ ያመራው ወደ ግጭት ነበረ፡፡

#### ለ. የጦር ኃይል ግንባታ

በ20ኛው ምዕተ - ዓመት መጀመሪያ ላይ ኃያላን የአውሮፓ ሀገሮች ከፍተኛ የጦር ኃይል ግንባታ ፉክክር ጀምረው ነበረ፡፡ የሠራዊቶቻቸውን መጠን መጨመር ብቻ ሳይሆን ለጦርነት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ሁሉ ያደራጁ ነበረ፡፡ እ.አ.አ በ1906 ዓ.ም የእንግሊዝ መንግሥት ተወዳዳሪ የማይገኝላቸውን የጦር መርከቦች ሠርቶ አወጣ፡፡ ከሦስት ዓመታት በኋላ የጀርመን መንግሥት ተመሳሳይ መርከቦች ሠራ፡፡

### ሐ. የጦር ቃል ኪዳን ሀገሮች

እ.ኤ.አ በ1879 ዓ.ም. ጀርመንና ኦስትሪያ- ሀንጋሪ፡ “የሁለትዮሽ ቃል-ኪዳን ሀገሮች” (Dual Alliance) በመባል የሚታወቀውን የወዳጅነት ውል ተፈራረሙ፡፡ ከሦስት ዓመታት በኋላ ኢጣሊያ “የሁለትዮሽ ቃል ኪዳን ሀገሮችን” ስትቀላቀል “የሦስቱ ወዳጅ ሀገሮች” (Triple Alliance) በመባል የሚታወቅ እጅግ የተጠናከረ የጦር ኃይሎች ጉራ ተመሠረተ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ስያሜያቸው “ማዕከላዊ ኃይሎች” (Central Power) ተብሏል፡፡ እ.ኤ.አ በ1907 ዓ.ም. እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ሩሲያ “የሦስትዮሽ” ሕብረት (Triple Entente) የተባለውን ቡድን አቋቋሙ፡፡ በዚህ የተነሣ አውሮፓ በሁለት ወታደራዊ የጦር-ሠፈሮች ተከፈለች፡፡ እ.ኤ.አ በ1915 ዓ.ም. ኢጣሊያ “ከሦስትዮሽ ቃል-ኪዳን ሀገሮች” ወጥታ “የሦስትዮች” ሕብረት ተቀላቀለች፡፡ “የሦስቱ ወዳጅ ሀገሮች” “ኃያላን የወዳጅ ሀገሮች” ተብለው ተሰይመዋል፡፡

### መ. ብሔረተኝነት

ፈረንሳይ ቀደም ሲል በጀርመን የተወሰዱባትን ግዛቶች ለማስመለስ ታደርግ የነበረው እንቅስቃሴ በአውሮፓ ለነበረው ውጥረት ተጨማሪ ምክንያት ነበር፡፡ ሌላው የውጥረት መነሻ ደግሞ በደቡብ ምሥራቅ አውሮፓ በባልካን አካባቢ የነበረው የብሔረተኛነት እንቅስቃሴ ነበረ፡፡ በዚህ አካባቢ የሚኖሩት ሕዝቦች ከኦቶማን ቱርኮች አገዛዝ ነጻ ለመውጣት ያደርጉ የነበረው ትግል ለመጀመሪያው የዓለም ጦርት መቀስቀስ አንዱ ምክንያት ነበር፡፡

**ውስን ጥናት**

**የአንደኛው የዓለም ጦርነት መጀመር**

*ለአንደኛው የዓለም ጦርነት መጀመር ሰበብ የሆነው የኦስትሪያው አልጋ-ወራሽ አርክዱክ ፍራንዝ ፈርዲናንድ እና ባለቤቱ እ.ኤ.አ. ሰኔ 28 ቀን 1914 ዓ.ም. በቦስኒያ ዋና ከተማ በሳሪያቮ በመገደላቸው ነበር፡፡ ገዳዩ ጋብሪሎ ፕሪንቺፕ የተባለ የሰርቢያ ብሔረተኛ ነበረ፡፡ ግድያው የሰርቢያ መንግሥት ኀላፊነት መሆኑን ኦስትሪያ–ሀንጋሪ አሳወቀች፡፡ በማስከተልም ኦስትሪያ ሀንጋሪ በሰርቢያ ላይ ጦርነት አወጀች፡፡ በዚህ ወቅት ሩሲያ ከሰርቢያ ጐን ቆመች፡፡ ጀርመን በበኩሏ ኦስትሪያ - ሀንጋሪን በመደገፍ በሩሲያና በፈረንሳይ ላይ ጦርነት አወጀች፡ በመጨረሻም እንግሊዝ በጀርመን ላይ ጦርነት በማወጇ የአንደኛው የዓለም ጦርነት ተጀመረ፡፡*

## የጦርነቱ ሒደት

- የአንደኛው የዓለም ጦርነት እንዴት ተካሔደ?

የአንደኛው የዓለም ጦርነት የተካሄደው በተለያዩ ሥፍራዎች ነው፡፡ በአውሮፓ ውስጥ ጦርነቱ የተካሄደው በሁለት የጦር ግንባር ነበር፡፡ ግንባሮቹም፤

- የምዕራብ ግንባር እና
- የምሥራቅ ግንባር በመባል ይታወቃሉ፡፡

የማዕከላዊ ኃይሎች አቀማመጥ አማካይ ሥፍራ ላይ ነበረ። በምዕራብ የእንግሊዝና የፈረንሳይ የጦር ኃይሎች በምሥራቅ ደግሞ ሩሲያዎች በተጠንቀቅ ቆመዋል። ጀርመኖች የውጊያ ዕቅድ ሲያዘጋጁ በመጀመሪያ በምዕራብ ግንባር በፈረንሳይ ላይ ድንገተኛ የማጥቃት እርምጃ በመውሰድ ድል ከተቀዳጁ በኋላ ተዋጊ ኃይላቸውን ወደ ምሥራቅ በማዞር ሩሲያን ለመውጋት ነበረ። ነገር ግን ይህ ዕቅዳቸው አልሠራም። በምዕራብ በኩል የሚዋጋውን ጦር ቀንሰው ወደ ምሥራቅ ለማዝመት ተገደው ነበረ። ስለዚህ የጀርመን የጦር ኃይል በአንድ ጊዜ በሁለት የተለያዩ ግንባሮች ለመዋጋት ተገዶ ነበረ።

እ.አ.አ በ1917 ዓ.ም. ሰሜን አሜሪካ የቃል-ኪዳን ኃይሎችን ስትቀላቀል የጦርነቱ የኃይል ሚዛን ተለወጠ። በመጨረሻም እ.ኤ.አ ኅዳር ወር 1918 ዓ.ም. የማዕከላዊ ኃይሎች በጦርነቱ ተሸነፉ።

### የአንደኛው የዓለም ጦርነት ያስከተሳቸው ውጤቶች

የአንደኛው የዓለም ጦርነት በቃል-ኪዳን ኃይሎች ድል አድራጊነት ተጠናቋል። ወታደሮችንና ሲቪሎችን ጨምሮ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሞተዋል። ለጦርነቱ ከ337 ቢሊዮን ዶላር በላይ ወጥቷል። ከዚህም በላይ በርካታ ኢንዱስትሪዎች፣ ድልድዮችና መሠረተ ልማቶች በሙሉ ወድመዋል። ብዙ ቤተሰቦች ተፈናቅለዋል። በፖለቲካ መስክ አሜሪካና ሶቪየት ኅብረት በዓለም ላይ ግንባር ቀደም ኃይሎች ለመሆን ችለዋል።



*ምሥል 1.17 በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ወታደሮች በአውሮፓ ለውጊያ በተቆፈረ ጉድባ ውስጥ*

**የክለሳ ጥያቄዎች 1.3.4**

**ክንውን ሀ**

*ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ*

- በኢንዱስትሪ በበለፀጉ የአውሮፓ ሀገሮች መካከል የነበረው ምጣኔሀብታዊ እና ፖለቲካዊ ፉክክር መነሻ ምን ነበር?
- በሦስትዮሽ ቃል ኪዳን ሀገሮችና በሦስትዮሽ ወዳጅ ሀገሮች መካከል የነበረውን ልዩነት ምን ነበር?
- የአንደኛው የዓለም ጦርነት ለመጀመር ሰበብ የነበረውን ምክንያት ግለጹ።

- ወታደራዊ የኃይል ሚዛን የቀየረውንና በመጨረሻም የማዕከላዊ ኃይሎችን ሽንፈት ያስከተለውን ሁኔታ አብራሩ፡፡
- የኢንዱስትሪ አብዮት ለምን በእንግሊዝ ሀገር ተጀመረ?
- በመጀመሪያው ደረጃ በኢንዱስትሪው አብዮት ወቅት ዋነኛው የኃይል ምንጭ ምን ነበረ?
- የእንፋሎት ሞተር ለኢንዱስትሪ አብዮት የነበረው ጠቀሜታ ምን ነበረ?
- የኢንዱስትሪ አብዮት ያስከተላቸው ለውጦች ምን ምን ነበሩ?

**ለ. የሚከተሉትን አብራሩ**

- የእንፋሎት ኃይል
- የፈትል መሣሪያ
- የካፒታሊስት መደብ
- የሠራተኛ ማኅበር
- የሠራተኛ መደብ

**ሐ. የሚሠሩ ተግባራት**

ማጣቀሻ መጻሕፍትን በመጠቀም ቀጥሎ በተጻፉት ሰዎች ላይ አጭር ጽሑፍ አዘጋጁ

- ሚካኤል ፋራዳይ
- ጀምስ ሐርግሪቭስ
- ጀምስ ዋት
- አሌክሳንደር ግራሐም ቤል
- ጉሊልሞ ማርኮኒ

## ሁለተኛው የዓለም ጦርነት (እ.ኤ.አ 1939 — 1945ዓ.ም.)

- ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንዴት ተጀመረ?

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተካሄደው የቃል ኪዳን ኃይሎች (Allied Powers) እና አክሲስ ኃይሎች (Axis Powers) በተባሉ ሁለት ወታደራዊ ጉራዎች መካከል ነበረ፡፡

**የቃል ኪዳን ኃይሎች የሚባሉት ፈረንሣይ፣ እንግሊዝ፣ ሩሲያና አሜሪካ ሲሆኑ የአክሲስ ኃይሎች ደግሞ ጀርመን ጃፓንና ኢጣሊያ ነበሩ፡፡**

## የጦርነቱ መነሻ ምክንያቶች

የጦርነቱ መነሻ ምክንያት የናዚና የፋሺስት ኃይሎች መነሣት ነበር፡፡ ይህም የተፈጠረው በጀርመን የናዚ ፓርቲ፣ በኢጣሊያን የፋሺስት ፓርቲ እንዲሁም በጃፓን አምባገነኖች ሥልጣን በመያዛቸው ነበር፡፡

እ.ኤ.አ ከ1933 ዓ.ም. ጀምሮ ጀርመን በናዚ ፓርቲ ሥር ገብታ ነበረ፡፡ ናዚ የሚለው ምኅፃረ ቃል በሙሉ ቃል ሲጻፍ "ብሔራዊ ሶሻሊስት የጀርመን ሠራተኞች ፓርቲ" ማለት ነው፡፡ የናዚ ፓርቲ መሪ አዶልፍ ሒትለር ይባላል፡፡

**ናዚዎች የጀርመን ሕዝብ ዘር ከሁሉም የሰው ዘር በላይ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ስለዚህም ዓለምን መግዛት አለብን ይላሉ፡፡ ጀርመኖች ያካሔዱት ወረራ በአውሮፓ ውስጥ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንዲጀመር ምክንያት ሆኗል፡፡ ኢጣሊያም በሙሶሊኒ በሚመራው የፋሽስት ፓርቲ ቁጥጥር ገብታ ነበረ፡፡ ኢጣሊያኖች በአፍሪካ አንድ ግዙፍ የኢጣሊያ ግዛት ለማቋቋም ጽኑ ፍላጎት ነበራቸው፡፡**

**ውስን ጥናት**

**የሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመር**

እ.ኤ.አ በ1931 ዓ.ም. ጃፓን በሰሜናዊ ቻይና የሚገኘውን ማንቹሪያ በመባል የሚታወቀውን ክፍለ ሀገር ስትወር እ.ኤ.አ በ1935 ዓ.ም. ደግሞ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ተወረረች፡፡ በመጨረሻም እ.ኤ.አ መስከረም 3 ቀን 1939 ዓ.ም. ጀርመን ፖላንድን ወረረች፡፡ እ.ኤ.አ መስከረም 3 ቀን 1939 ዓ.ም. እንግሊዝና ፈረንሳይ በጀርመን ላይ ጦርነት ሲያውጁ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአውሮፓ በይፋ ተጀመረ፡፡

## የጦርነቱ ሒደት

- የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ውጊያ እንዴት ተካሔደ?

በምዕራብ ግንባር የጀርመን ጦር ግስጋሴ ፈጣን ነበረ፡፡ እ.ኤ.አ በ1940 ዓ.ም. ጀርመኖች ፈረንሳይን ወረሩ፡፡ ፈረንሳይም የጀርመንን ጥቃት መቋቋም ባለመቻሏ እጅ ሰጠች፡፡

አዶልፍ ሒትለር በፈረንሳይ ላይ ባገኘው ድል በመበረታታት በብሪታኒያ ላይ የአውሮፕላን ጥቃት ሰነዘረ፡፡ ነገር ግን የብሪታኒያ ጦርነት እንደተገመተው ቀላል አልነበረም፡፡ የብሪታኒያ ጠንካራ የአየር ኃይል የጀርመኖችን ወረራ ለመቀልበስ ችሏል፡፡

እ.ኤ.አ በታኅሣሥ 1941 ዓ.ም. ጃፓን በሰላማዊ(Pacific) ደሴት ሐዋይ ላይ በሚገኘውና ፐርል ሀርበር በተሰኘው የአሜሪካ የባሕር ኃይል ጦር ሠፈር ላይ ጥቃት በመሠንዘሯ አሜሪካ በጃፓን ላይ ጦርነት አውጃለች፡፡ እ.ኤ.አ በ1943 ዓ.ም እና በ1945 ዓ.ም መካከል የጦርነቱ የኃይል ሚዛን ወደ ቃል ኪዳን ኃይሎች እያደላ መጣ፡፡ የቃል ኪዳን ኃይሎች በእስያና በአውሮፓ በአክሲስ ኃይሎች ላይ በአየርና በባሕር ከፍተኛ የማጥቃት እርምጃ ወስደዋል፡፡



*ምስል 1.18 በስተግራ ሠላምታ የሰጠው ቤኒቶ ሙሶሊኒ እና በስተ ቀኝ አዶልፍ ሒትለር*

እ.ኤ.አ በ1944 ዓ.ም. ቤኒቶ ሙሶሎኒ ከሥልጣኑ ከተወገደ በኋላ የቃል-ኪዳን ኃይሎች አብዛኛውን የኢጣሊያን ግዛት መቆጣጠር ችለዋል፡፡ በዚያው ዓመተ ምሕረት ፈረንሳይ ነፃነቷን አግኝታለች፡፡ ሩሲያም በበኩሏ የጀርመንን ዋና ከተማ በርሊንን ተቆጣጠረች፡፡ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 30 ቀን 1945 ዓ.ም. አዶልፍ ሒትለር ራሱን በራሱ አጠፋ፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ ጀርመን እጇን ስትሰጥ በአውሮፓ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተፈጸመ፡፡ ይህንን ተከትሎ በሩቅ ምሥራቅ ጃፓንም ተሸንፋለች፡፡

እ.ኤ.አ ነሐሴ 6 እና 9 ቀን 1945 ዓ.ም. አሜሪካ ሒሮሺማ እና ናጋሣኪ በተባሉት የጃፓን ከተሞች ላይ የአቶሚክ ቦንብ ጣለች፡፡ ይህ ሁኔታ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት በእስያ መጠናቀቁን አበሠረ፡፡

## ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ያስከተላቸው ውጤቶች

- ጦርነት የሚያስከትላቸው ዋና ዋና ውጤቶች ምንድናቸው?

የቃል - ኪዳን ኃይሎች ጦርነቱን በድል ሲያጠናቅቁ የአክሲስ ኃይሎች ሽንፈትን ተከናንበዋል፡፡ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ ከፍተኛ ውድመት አስከትሏል፡፡ 50 ሚሊዮን ወታደሮች በግዳጅ ላይ እንደሞቱ ይገመታል፡፡ ብዙ ከተሞች፣ ኢንዱስትሪዎች፣ መንገዶች፣ ሐዲዶች፣ እና ድልድዮች ሙሉ በሙሉ ተደምስሰዋል፡፡ ይህ የንብረት ውድመት ሲተመን ከሁለት ሺህ ቢሊዮን ዶላር በላይ እንደነበር ይገመታል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች 1.3.4

**ክንውን ለ**

**በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች**

***ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

- እ.ኤ.አ በ1941 ዓ.ም. አሜሪካ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተሳተፈችው ለምን ነበረ?
- የአንደኛው የዓለም ጦርነት በዋናነት የተካሄደው አውሮፓ ውስጥ ሆኖ እያለ ለምን የዓለም ጦርነት ተብሎ ሊጠራ ቻለ?
- የአንደኛውና የሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች በሰው ሕይወትና በንብረት ያስከተሉትን ውድመት ዘርዝሩ፡፡
- የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ለምን ተጀመረ?
- የሁለተኛው የዓለም ጦርነትን ሂደት ግለጹ
- በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የቃል-ኪዳን ኃይሎች አሸናፊ የሆኑበትን ምክንያት ግለጹ፡፡
- ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመር ምክንያት የሆኑትን ሦስቱን ወታደራዊ መንግስታት ስም ጻፉ፡፡

***ለ. የሚከተሉትን ግለጹ፡፡***

- የጦር ቃል ኪዳን ሀገሮች
- ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች
- የጦር ኃይል ግንባታ
- የሦስትዮሽ ቃል ኪዳን
- የፋሽስት ፓርቲ
- የሁለትዮሽ ቃል ኪዳን
- የቃል ኪዳን ኃይሎች
- የናዚ ፓርቲ

***ሐ. የሚሠሩ ተግባራት***

1. በአውሮፓ ካርታ ላይ የሚከተሉትን ሥፍራዎች አመልክቱ፡፡
   - ኦስትሪያ
   - የባልካን አካባቢ
   - ሳራዬቮ
   - ሀንጋሪ
   - ሰርቢያ
   - ፖላንድ
   - ቦስኒያ
   - በርሊን
2. የሚከተሉትን ለዩ
   - ፍራንዝ ፈርዲናንድ
   - ጋቭሬሎ ፕሪንቺፕ
   - የአክሲስ ኃይሎች
   - አዶልፍ ሒትለር
   - ቤኒቶ ሙሶሎኒ

## ቅኝ አገዛዝ እንዳይስፋፋ አፍሪካውያን ያደረጉት መከላከል

- አፍሪካውያን ቅኝ አገዛዝ እንዳይስፋፋ ለመከላከል ያደረጉት ጥረት ምን ነበረ?

ተማሪዎች! ባለፈው ክፍለ ትምህርት ውስጥ የኢንዱስትሪ አብዮት ካስከተላቸው ውጤቶች አንደኛው ዝቅተኛ ዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሀገሮች በቅኝ አገዛዝ ሥር መውደቃቸው እንደነበረ ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ በ19ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ውስጥ የአፍሪካ ሕዝቦች የቅኝ አገዛዝ መስፋፋትን እንዴት እንደተከላከሉ ትማራላችሁ፡፡ ይህ የፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል እስከ 1914 ዓ.ም. ድረስ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮች ተካሂዷል፡፡

### 1. የአሻንቲ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል

- ቀድሞ ጎልድ ኮስት በመባል የሚታወቀው የትኛው የምዕራብ አፍሪካ ሀገር ነው?

የአሻንቲ ሕዝብ (አሣንቲ) መኖሪያ በዛሬዋ ጋና የሚገኝ በጣም ሰፊ ግዛት ነበረ፡፡ የአሻንቲ ሕዝብ መሪዎች አሳንትሔኔ በመባል የማዕረግ ስም ይጠሩ ነበር፡፡

እ.ኤ.አ በ1874 ዓ.ም. እንግሊዞች በምዕራብ አፍሪካ በአትላንቲክ ውቅያኖስ ዳርቻ የሚገኘውን ቀጭን መሬት ያዙ፡፡ በዚሁ ዓመት እንግሊዞች ወደ አሻንቲ ግዛት እየተስፋፉ ነበረ፡፡ ነገር ግን የአሻንቲ ሕዝብ ሀገሩን ከእንግሊዝ ተስፋፊዎች ለመከላከል ቢሞክርም እ.ኤ.አ በ1896 ዓ.ም. በወራሪዎቹ ተሸንፎ ግዛቱን ተቀምቷል፡፡ እ.ኤ.አ በ1900 ዓ.ም. የአሻንቲ ሕዝብ ለነጻነቱ ከእንግሊዞች ጋር ለሁለተኛ ጊዜ በጀግንነት ተዋግቶ ተሸንፎአል፡፡ በዚያኑ ዓመት እንግሊዞች የዛሬዋ ጋና የምትገኝበትን አካባቢ በሙሉ በቅኝ አገዛዛቸው ሥር ካስገቡ በኋላ ጐልድ ኮስት(Gold coast) ብለው ሠይመውታል፡፡

### 2. ሳሞሪ ቱሬ

- ሳሞሪ ቱሬ ማን ነው?

እ.ኤ.አ በ1870ዎቹ ዓ.ም ሳሞሪ ቱሬ በምዕራብ አፍሪካ ሠፊ ግዛት መስርቶ ነበረ፡፡ የሳሞሪ ቱሬ ግዛት የዛሬዎቹን የምስራቅ ሴኔጋልን ክፍል የደቡብ ምሥራቅ ማሊ እና ጊኒን አካባቢዎች ያጠቃልል ነበረ፡፡ በዚሁ ወቅት ፈረንሳዮች በምዕራብ አፍሪካ ቅኝ ግዛት በማስፋፋት ላይ ይገኙ ነበረ፡፡ ነገር ግን እ.ኤ.አ በ1886/7 ዓ.ም ሳሞሪ ቱሬ ከፈረንሳዮች ጋር ስምምነት ቢያደርግም ፈረንሳዮች ስምምነቱን አፍርሰው ግዛቱን በኃይል ለመንጠቅ በመሞከራቸው ሳሞሪ ቱሬ በቆራጥነት ተዋግቷል፡፡



*ምስል 1.19 ሣሞሪ ቱሬ*

ሳሞሪ ቱሬ በምዕራብ አፍሪካ ባሕር ዳርቻ ከሚገኙት ከተሞች ጋር በነበረው የንግድ ግንኙነት አማካኝነት በቂ የጦር መሣሪያ ያገኝ ነበረ፡፡ በዚህም ተጠቅሞ ከፈረንሣዮች ጋር ለሰባት ዓመታት በጀግንነት ተዋግቷል፡፡ ሆኖም በእንግሊዝ እና በፈረንሳይ ሤራ የጦር መሣሪያ አቅርቦቱ ስለተቋረጠበት ሳሞሪ ቱሬ ሊዳከም ቻለ፡፡ በመጨረሻም እ.ኤ.አ በ1898 ዓ.ም. ሳሞሪ ቱሬ በፈረንሳዮች ተይዞ ወደ ጋቦን ተወስዶ ታሠረ፡፡ ከሁለት ዓመታት የእሥር ቆይታ በኋላ ሳሞሪ ቱሬ በተወለደ በሰባ ዓመቱ ዓረፈ፡፡


### 3. የማጂ ማጂ አመጽ

የማጂ ማጂ አመጽ የተቀሰቀሰው እ.ኤ.አ በ1905 ዓ.ም የጀርመን ቅኝ ግዛት በነበረችው **በታንጋኒካ** ነበረ፡፡ አመጹ የተጀመረው ቅኝ ገዢዎች የአካባቢውን ሕዝብ በጥጥ እርሻ ላይ እንዲሠራ በማስገደዳቸው ነበረ፡፡ ነገር ግን

ሕዝቡ ለቅኝ ገዢዎች ከመታዘዝ ይልቅ በአመጽ እምቢታውን ለመግለጽ ሞከረ፡፡ እንደ ሰደድ እሳት የተቀጣጠለው የአርሶ አደሮች አመጽ የማጂ ማጂ አመጽ በመባል ይታወቃል፡፡ "ማጂ" የሚለው የሰዋሂሊ ቋንቋ ቃል ትርጉሙ ውኃ ማለት ነው፡፡ የአመጹ መሪዎች ሕዝቡ ለአመጽ ሲነሣ የማጂ ውኃ ሰውነቱ ላይ ከተረጨ የጀርመን ጥይት እንደማይገለው አሳምነውት ነበር፡፡ የአመጹ ተካፋዮች ይህንን አምነው በመቀበል ትግላቸውን እ.ኤ.አ እስከ 1907 ዓ.ም. ድረስ ቀጠሉ፡፡ ነገር ግን በመጨረሻ አመጹ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ሥር በመዋሉ ጀርመኖች አስከፊ የሆነ ቅኝ አገዛዛቸውን አስፋፍተዋል፡፡

### 4. የአድዋ ጦርነት

- የአድዋ ጦርነት የተካሄደው በማንና በማን መካከል ነበር?
- የአድዋ ጦርነት መነሻው ምን ነበር?



*ምስል 1.20 የአድዋ ጦርነት*

እ.ኢ.ት.አ ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም የውጫሌ ውል በኢጣሊያ እና በዳግማዊ አጼ ምኒሊክ መካከል ተፈረመ፡፡ ውሉ በአማርኛና በኢጣሊያንኛ ቋንቋዎች የተዘጋጁ ሃያ አንቀጾች ነበሩት፡፡ ነገር ግን በኢጣሊያ ቋንቋ የተዘጋጀው ቅጂ ላይ የተጻፈው ስምምነት በአማርኛው ቅጂ ላይ የሌለ ግዴታዎችን አስገብቶ ነበር፡፡

አንቀጽ ሦስት በኢጣሊያ ተይዞ በነበረው መረብ ምላሽ (በዛሬዋ ኤርትራ) እና በተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል መካከል ያለውን ድንበር የሚያካልል አንቀጽ ነው፡፡ ጣሊያኖች በዚህ አንቀጽ ሦስት ባለመርካታቸው "**ተጨማሪ ስምምነት**" (Additional Convention) በተሰኘ ሌላ ውል የአጼ ምኒልክ የክብር መልክተኛ ከነበሩት ከራስ መኰንን ጋር ተፈራርመዋል፡፡ ይህ ተጨማሪ ውል ጣሊያኖች ግዛታቸውን እስከ መረብ ወንዝ ድረስ እንዲያስፋፉ ይፈቅድላቸዋል፡፡ ስለዚህም ከመረብ ወንዝ በስተ ሰሜን የሚገኘውን አካባቢ ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠሩ በኋላ እ.ኢ.ት.አ ታኅሣሥ 23 ቀን 1882 ዓ.ም. ይህንን ቅኝ ግዛታቸውን **ኤርትራ** ብለው ሠይመውታል፡፡


በአማርኛው ቅጂ የተጻፈው የአንቀጽ 17 ስምምነት **ኢትዮጵያ ከአውሮፓ መንግሥታት ጋር የውጭ ግንኙነት ለማድረግ የጣሊያንን መንግሥት እገዛ መጠቀም ትችላለች** በማለት ሲገልጽ በጣሊያንኛው ቅጅ የተጻፈው ደግሞ **የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ማንኛውንም የውጭ ግንኙነት በኢጣሊያ መንግሥት በኩል ማድረግ አለባቸው** ይላል፡፡ በጣሊያንኛ ቅጂ የተጻፈው ውል ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ጥብቅ ግዛት እንደሆነች የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በዚህ የተነሣ ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ጥብቅ ግዛት መሆኗን ኢጣሊያ ለአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት ወዲያውኑ አሳውቃለች፡፡

ነገር ግን እ.ኢ.ት.አ በ1888 ዓ.ም. ዳግማዊ አጼ ምኒልክ የውጫሌውን ውል በሙሉ ውድቅ ማድረጋቸውን ለዋና ዋና የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታትና ለራሱ ለኢጣሊያ መንግሥትም አሳወቁ፡፡ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ የሀገራቸውን ነጻነትና ክብር ከማዋረድ ጦርነትን መረጡ፡፡

እ.ኢ.ት.አ ጥቅምት 2 ቀን 1888ዓ.ም. ከወራሪው የኢጣሊያ ጦር ጋር ለመፋለም የክተት አዋጅ በመጥራት 100,000 ሠራዊት እየመሩ ወደ ሰሜናዊ ኢትዮጵያ ዘመቱ፡፡

እ.ኢ.ት.አ ኅዳር 28 ቀን 1888 ዓ.ም. ግንባር ቀደሙ የኢትዮጵያ ሠራዊት አምባላጌ ተራራ ላይ መሽጎ የነበረውን የጣልያንን ሠራዊት ድባቅ መታ፡፡

እ.ኢ.ት.አ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. የመጨረሻው ወሳኝ ጦርነት አድዋ ላይ ተደረገ፡፡ የአድዋ ጦርነት አንድ ሙሉ ቀን የተካሄደ እና ደም ያፋሰሰ ጦርነት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ተዋጊዎች በከፍተኛ ወኔና ጀግንነት ከጠላት ሠራዊት ጋር ተፋልመዋል፡፡ በጦርነቱ የኢጣሊያ ሠራዊት ሙሉ በሙሉ ተሸንፏል፡፡ ኢትዮጵያውያን የአድዋ ጦርነት ባለድል ሆነዋል፡፡ ከጠቅላላው ሃያ ሺህ የኢጣሊያ ሠራዊት አንድ ሦስተኛ የሚሆነው በጦርነቱ ላይ ሲደመሰስ ሁለት ሺህ ወታደሮች ተማርከው አንድ ሺህ አምስት መቶ የሚሆኑት ደግሞ ቁስለኛ ሆነዋል፡፡ በኢትዮጵያውያን በኩል ከአንድ መቶ ሺህ ሠራዊት ውስጥ ሰባት ሺህ ያህል ተሰውቷል፡፡ የአድዋ ጦርነት የተጠናቀቀው በኢትዮጵያውያን ድል አድራጊነት ነው፡፡ ጣልያኖች የትግራይን መሬት ሙሉ በሙሉ ለቅቀው ከወጡ በኋላ በቅኝ ግዛታቸው ኤርትራ ውስጥ ተወስነው ተቀመጡ፡፡ የአድዋ ድል ኢጣሊያ የቀረውን የኢትዮጵያን ክፍል በቅኝ ግዛቷ ሥር ለማስገባት የነበራትን ዕቅድ ውድቅ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያውያን ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የታጠቀውን የኢጣሊያ ሠራዊት ድል በማድረጋቸው አፍሪካውያን ወንድሞቻቸው ለነጻነት የሚያደርጉት ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል የበለጠ እንዲጠናከር አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡




ምሥል 1.21 በቅኝ አገዛዝ ሥር የነበሩ የአፍሪካ ሀገራት

## የአፍሪካውያን ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል

- **የቅኝ አገዛዝን መስፋፋት በመቃወምና የቅኝ አገዛዝን አስተዳደር በመታገል መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?**

የቅኝ አገዛዝን በመቃወም የተደረገው የአፍሪካውያን ትግል እያደገ የመጣው ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነው፡፡ ቅኝ አገዛዝን ለማስወገድ አፍሪካውያን የተለያዩ የትግል ስልቶችን ተጠቅመዋል፡፡ በኬንያ የወጣት ኩኩዩ ማኅበር በግብጽ የዋፍዲስት ፓርቲ፣ በቱኒዝያ የኔዎ- ዳትሱር ፓርቲና በደቡባዊ አፍሪካ የአፍሪካ ብሔራዊ ሸንጎ (ANC) ፓርቲ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል ለማድረግ ተቋቁመዋል፡፡

### 1. ኩኩዩ

ኩኩዩ በኬንያ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ካላቸው ሕዝቦች መካከል አንደኛው ነው፡፡ የኩኩዩ የወጣት ማኅበር የተቋቋመው በከተሞች በሚኖሩና የነጮች ንብረት በሆኑት የእርሻ መሬቶች ላይ ተቀጥረው በሚሠሩ አፍሪካውያን ነው፡፡ የእንግሊዝ ሠፋሪዎች በኬንያ የኩኩዩ ሕዝብ ንብረት የነበረውን ለም መሬት በኃይል ነጥቀው በመውሰዳቸው በኩኩዩ ሕዝብና በቅኝ ገዢዋ እንግሊዝ መካከል ጠላትነት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡


እ.ኤ.አ በ1921 ዓ.ም. የእንግሊዝ ባለመሬቶች በእርሻ ሥራ የተሠማሩትን የአፍሪካውያን ክፍያ በአንድ ሦስተኛ እንዲቀንስ ማድረጋቸው የኩኩዩ ወጣት ማኅበር እንዲመሠረት ምክንያት ሆኗል፡፡

ሐሪ ቱኩ የተባለው ወጣት የስልክ ሠራተኛ የማኅበሩ መሪ ነበረ፡፡ የማኅበሩ ዓላማ የአፍሪካውያንን መብት ማስከበርና የእንግሊዞችን ቅኝ አገዛዝ መታገል ነበረ፡፡ የማኅበሩ ትልቁ ጥያቄ የእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች ከሕዝቡ በኃይል ነጥቀው የወሰዱትን ለም መሬት ማስመለስ ነበረ፡፡ ነገር ግን የእንግሊዝ ቅኝ ገዢዎች በማኅበሩ አባላት ላይ በጣም አስከፊ እርምጃ ወሰዱ፡፡ እ.ኤ.አ በ1922 ዓ.ም. የማኅበሩ መሪ ሐሪ ቱኩ ታሠረ፡፡

### 2. የአፍሪካ ብሔራዊ ሸንጎ (African National Congress- ANC)

- **ለሠላሣ ዓመታት ያህል በእሥር ቤት ያሳለፉ የአፍሪካ ብሔራዊ ሸንጎ መሪ ማን ነበሩ?**

የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ቀድሞ ያደገው ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ይልቅ በደቡብ አፍሪካ ነበረ፡፡ ይህ ሁኔታ ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል ለመምራትና ለማስተባበር የሚችል የፖለቲካ ፓርቲ በደቡብ አፍሪካ ለማቋቋም አስችሏል፡፡




*ምስል 1.22 ኔልሰን ማንዴላ*

**ቅኝ ገዢዎች በደቡብ አፍሪካ የዘር መድልዎ መፈጸም፣ ጥቂቶች ብዙኃኑን በበላይነት መግዛት እንዲሁም ጥቁሮች በነጮች እንዲበዘበዙ የሚያስገድድ ሥርዓት መሥርተው ነበር።**

የአፍሪካ ብሔራዊ ሸንጎ (A.N.C) የተመሠረተው እ.ኤ.አ በ1912 ዓ.ም. ነበር። ይህ ሸንጎ በአፍሪካ በመጀመሪያ የተመሠረተ የፖለቲካ ፓርቲ ነው። የፓርቲው አባላት በደቡብ አፍሪካ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የመጡ አፍሪካውያን ናቸው። የፓርቲው ራዕይና ግብ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለሥራ የመጡ የሌሴቶና የስዋዚላንድ ዜጎችን አስተሳሰብ ኤ.ኤን.ሲ. ሊለውጥ ችሏል። እነዚህ ሠራተኞች ሀገራቸው ሲመለሱ ለዲሞክራሲያዊ መብቶችና ለነጻነት ተደራጅቶ የመታገልን ልምድ አስፋፍተዋል።

## 3. ዋፍድ

ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ግብጻውያን በእንግሊዞች ላይ ያነጣጠረ ጠንካራ ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ተቃውሞና ትግል ጀመሩ። ይህ የትግል ሂደት ዋፍድ ለተባለ ብሔረተኛ ፓርቲ መመሥረት ምክንያት ሆኗል። ዋፍድ የሚለው ቃል ትርጓሜው መልዕክተኞች ማለት ነው። ፓርቲው ለግብጽ ፍፁማዊ ነጻነት መታገል ጀመረ። ከፓርቲው መሪዎች አንዱ ዛግሉል ፓሻ በመባል ይታወቃል። በቨርሴይልስ ከተማ በሚካሄደው ስብሰባ የግብጽን የነጻነት ጥያቄ ለማቅረብ ዛግሉል ፓሻ ከመልዕክተኞች ጋር ተጉዞ ነበረ። ነገር ግን እንግሊዞች ዛግሉል ፓሻን ሜዲትራኒያን ባሕር ላይ ወደምትገኘው የማልታ ደሴት በግዞት ወስደውታል።

እ.ኤ.አ በ1922 ዓ.ም. የግብጽ የነጻነት ጥያቄ ምላሽ ቢያገኝም የእንግሊዝ ወታደሮች እስከ 1956 ዓ.ም. ድረስ የግብጽን ምድር ለቀው አልወጡም። እ.ኤ.አ በ1923 ዓ.ም. የተመሠረተው የዋፍድ ፓርቲ ለግብጽ ነጻነት የተጀመረውንም ትግል አጠናክሮ ቀጥሏል።

## 4. ኒዎ ዳትሱር

ኒዎ ዳትሱር እ.ኤ.አ በ1934 ዓ.ም. በሐቢብ ቡርጊባ ቱኒዚያን ከፈረንሳይ ቅኝ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት የተመሠረተ ፓርቲ ነው። ዳትሱር ማለት የሕገ-መንግሥት ፓርቲ ማለት ነው። እ.ኤ.አ በ1956 ዓ.ም. ቱኒዚያ ነጻነቷን ስትቀዳጅ ሐቢብ ቡርጊባ የመጀመሪያው የሀገሪቷ ፕሬዚዳንት ሆነዋል።

**የክለሳ ጥያቄዎች 1.3.4**

**ክንውን ሐ**

**ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች**

*1. የሚከተሉትን ለዩ።*

- አሻንቲ
- ጉልድ ኮስት
- አሳንትሔኒ
- ሳሞራ ቱሬ
- ማጂ ማጂ
- ዛግሉል ፓሻ
- ሐቢብ ቡርጊባ
- ኩኩዩ
- ዳግማዊ ምኒሊክ
- የአድዋ ጦርነት
- የአፍሪካ ብሔራዊ ሸንጎ
- አንደኛው የዓለም ጦርነት
- ዋፍድ
- ራስ መኮንን
- ሐሪ ቱኩ
- ሰዋሂሊ
- የውጫሌ ውል
- አንቀጽ ሦስት
- አንቀጽ አሥራ ሰባት
- መረብ ምላሽ
- ኒዎ ዳትሱር

2. የሚከተሉትን ግለጹ፡፡

- ቅኝ ግዛት
- በብዙኃኑ ላይ የጥቂቶች የበላይነት
- ጥብቅ ግዛት

3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

- አሻንቲዎች በጀግንነት የተዋጉት ከማን ጋር ነበረ?
- ሳሞራ ቱሬ ለትግል የተነሣበት ምክንያት ምን ነበረ?
- የማጂ ማጂ አመጽ የተነሣበትን ምክንያት ግለጹ፡፡
- ለውጫሌ ውል መፍረስ ምክንያት የነበሩ የትኞቹ አንቀጾች ናቸው? ውጤታቸውስ ምን ነበረ?
- በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል በአፍሪካ የታዩትን ፀረ-ቀኝ አገዛዝ የትግል ዘዴዎች አብራሩ፡፡
- በኬንያ ኩኩዩ የወጣት ማኅበርን ለትግል ያነሳሣው ምን ነበረ?

ለ. የሚሠሩ ተግባራት

- የሚከተሉትን ቦታዎች በአፍሪካ/በኢትዮጵያ ካርታ ላይ አመልክቱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| - ጋና | - ውጫሌ | - ቱኒዝያ |
| - ሴኔጋል | - አድዋ | - ደቡብ አፍሪካ |
| - ማሊ | - ኤርትራ | - ስዋዚላንድ |
| - ጊኒ | - መረብ ወንዝ | - ግብጽ |
| - ታንዛንያ | - ኬንያ | - ሌሶቶ |

## ቁልፍ ቃላት

- ላቲን፡- የጥንታዊ ሮማውያን ቋንቋ
- ልሳነ ምድር፡- ሁለት ትላልቅ የመሬት ክፍሎችን የሚያገናኝ ጠባብ መሬት
- ሒጅራ፡- እ.አ.አ በ622 ዓ.ም ነቢዩ መሐመድ ከመካ ወደ መዲና ያደረጉት ስደት
- ማንዳሪን፡- የቻይናውያን ቋንቋ
- ባሕረ ሰላጤ፡- አንዳንድ ጊዜ የባሕር ወሽመጥ ወይንም የባሕር ሰርጥ ተብሎ ይጠራል፡፡ ጠበብ ብሎ ሁለት ሰፋፊ የመሬት አካላትን የሚያገናኝ የመሬት ክፍል ሆኖ በሁለት ጎኑ በውሃ የተከበበ ነው፡፡
- ብሔረተኝነት፡- ለትውልድ ሀገር ያለ ጠንካራ ስሜት
- ብዙኃንነት፡- የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ ላይ መኖር፡፡
- አብዮት፡- ፍፁም የሆነ ለውጥ
- አንጻራዊ መገኛ፡- የአንድን አካባቢ መገኛ ዙሪያውን ከሚገኙ ቋሚ ምልክቶች አንጻር የሚገልጽ አመላካች ነው፡፡
- አኗኗር፡- ሕዝቦች ዕለታዊ ኑሮአቸውን ለመምራት የሚያደርጉት ምጣኔ ሀብታዊ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ መገለጫ ነው፡፡
- ኦሪት (ቶራ)፡- የሙሴ ሕግና ሥርዓት የተጻፈበት የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል፡፡
- ኪስዋሂሊ፡- በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት የሚነገር ቋንቋ
- ክፍለ አኅጉር፡- በዓለማችን ከሚገኙ አኅጉራት መካከል የተወሰነ ሥፍራ የያዘ አኅጉር ወይንም የአንድ መልከአ ምድራዊ ክልልን ወይን ፖለቲካዊ ክልልን ያሳያል፡፡
- ዓ.ዓ (ዓመተ ዓለም)፡- ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው ዘመን አቆጣጠር፡፡
- የተበታተነ የሕዝብ ሥርጭት፡- ሕዝቦች ተራርቀውና ተበታትነው መኖራቸውን ያመለክታል፡፡
- የተጠጋጋ የሕዝብ ሥርጭት፡- ሕዝቦች በውስን ሥፍራ በጣም ተቀራርበው በከፍተኛ ቁጥር መኖራቸውን ያሳያል፡፡
- የእንፋሎት ኃይል፡- ውኃን በማፍላት የሚገኝ ኃይል
- ፓትሪሺያኖች፡- በጥንታዊ ሮማውያን መሳፍንቶች

## ማጠቃለያ

- ከመሬት ውጪያዊ አካል ሃያ ዘጠኝ በመቶ የሚሆነው በአኅጉሮችና በደሴቶች የተሸፈነ ነው፡፡
- በዓለም ላይ ሰባት አኅጉሮች አሉ፡፡ እነርሱም እስያ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ አፍሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ አውስትራሊያ እና አንታርክቲካ ናቸው፡፡
- በጣም ሞቃትና በጣም ቀዝቃዛ የሆኑት አካባቢዎች የተበታተነ የሕዝብ ሥርጭት አላቸው፡፡
- የተጠጋጋ የሕዝብ ሥርጭት ያላቸው አካባቢዎች ከአንድ ስኩዌር ሜትር በማይበልጥ ቦታ በጣም ብዙ ሕዝብ የሠፈረባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡
- የሕዝብ ሥርጭትን የሚወስኑት ተፈጥሮአዊና ማኅበራዊ ምክንያቶች ናቸው፡፡
- የዓለም ሕዝብ አኗኗር በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በንግድና በአገልግሎት ዘርፎች የተመሠረተ ነው፡፡
- በዓለም በጣም ብዙ ተናጋሪ ያላቸው ቋንቋዎች ይገኛሉ፡፡ ማንዳሪን፣ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ አረብኛ እና ስፓኒሽ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ዓለም አቀፍ መግባቢያ ናቸው፡፡ የስፓኒሽ ቋንቋ በደቡብ እና በማዕከላዊ አሜሪካ በስፋት ይነገራል፡፡
- ከጥንታዊ የዓለም ሥልጣኔዎች የግሪክ፣ የሮም፣ የቻይና፣ የፐርሺያና የኢንካ ሥልጣኔዎች እጅግ በጣም አስደናቂ ቅርሶች አሏቸው፡፡
- ከዓለማችን ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ክርስትና፣ እስልምና፣ ይሁዲ፣ ቡዲሂዝም፣ ሒንዱይዝምና ሺንቶይዝም ብዙ ተከታዮች አሏቸው፡፡
- በዓለም ላይ የሕዝቦች ሥርጭት ያልተመጣጠነ ነው፡፡ ለምሳሌ ሕንድ፣ ቻይና እና የናይል ሸለቆ በጣም የተጠጋጋ ሕዝብ የሚኖርባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል እጅግ በጣም ቀዝቃዛ እና በጣም ሞቃት በረሃዎች የተበታተነ የሕዝብ ጥግግት አላቸው፡፡ የሕዝብ ሥርጭትን በዋናነት የሚቆጣጠሩት መልክአ-ምድራዊ አቀማመጥና ማኅበራዊ ምክንያቶች ናቸው፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች የተለያየ የአኗኗር ዘይቤ አላቸው፡፡
- የኢንዱስትሪ አብዮት የተጀመረው በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ነው፡፡ የኢንዱስትሪ አብዮት ምንም እንኳን መልካም ውጤት ቢያመጣም ቅኝ አገዛዝን፣ የአንደኛውንና የሁለተኛውን የዓለም ጦርነቶች አስከትሏል፡፡ በሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ደረጃ ወቅት አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገሮች በቅኝ አገዛዝ ሥር ወድቀዋል፡፡ የአፍሪካውያን ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ከመሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ ዋፍዲስትና ኒዎ ዳትሱር በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡

# የምዕራፍ አንድ
# የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች «እውነት» ወይም «ሐሰት» በማለት መልሱ፡፡**

1. በተጓዳኝ መስመሮችና በሜሪዲያኖች የሚገለፀው የቦታዎች መገኛ አንፃራዊ መገኛ ነው፡፡
2. የተበታተነ የሕዝብ ስርጭት ያላቸው አካባቢዎች ጥሩ ምሳሌ የአርክቲክ አካባቢ ነው፡፡
3. ፓለቲካዊ አደረጃጀቶችና ምጣኔ ሀብታዊ የዕድገት ደረጃ የሕዝብ ስርጭት ዋነኛ ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ናቸው፡፡
4. ጥሬ ዕቃዎችን ወደ ያለቀላቸው የፍጆታ ሸቀጥነት የመለወጥ ሥራ የፋብሪካ ወይም የኢንዱስትሪ ሥራ ይባላል፡፡
5. የመሬት ሰፊው አካል በውሃ የተሸፈነ ነው፡፡

**ለ. አዛምዱ**

***በ "ሀ" ረድፍ የተዘረዘሩትን በ "ለ" ረድፍ ከቀረቡት ጋር አዛምዱ፡፡***

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ዳግማዊ ምኒልክ | ሀ) በጀርመን ላይ የተካሄደውን አመጽ የመራ |
| 2. ሳሞራ ቱሬ | ለ) በእንግሊዝ ላይ የተካሄደውን አመጽ የመራ |
| 3. ሐቢብ ቡርጊባ | ሐ) በጣሊያን ላይ የተካሄደውን ጦርነት የመሩ |
| 4. ጋብሬሎ ፕሪንቺፕ | መ) በፈረንሳይ ላይ የተካሄደውን አመጽ የመራ |
| 5. ቤኒቶ ሞሶሎኒ | ሠ) የናዚ ፓርቲ መሪ |
| 6. አዶልፍ ሂትለር | ረ) የፋሽስት ፓርቲ መሪ |
| | ሰ) የቱኒዚያ አመጽ መሪ |
| | ሸ) የግብጽ አመጽ መሪ |
| | ቀ) በስፔን የተካሄደ አመጽ የመራ |
| | በ) የአውስትሪያን ልዑል የገደለ |

**ሐ.ምርጫ**

***ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች ምረጡ፡፡***

1. የሕዝብ ክምችት ከፍተኛ በሆነባቸው አካባቢዎች አጣዳፊና ዋነኛ ችግር ያልሆነው፡፡
   ሀ. የምግብ ሰብል እጥረት
   ለ. የመኖሪያ ቤትና የእርሻ ቦታ እጥረት
   ሐ. የአካባቢ ንጽሕና ጉድለት
   መ. የሃይማኖት ግጭት
2. በዓለም ትልቁ አኅጉር
   ሀ. አፍሪካ
   ለ. ሰሜን አሜሪካ
   ሐ. ደቡብ አሜሪካ
   መ. እስያ

3. ኢንዊቶች የሚኖሩት በ __________ ነው፡፡
   ሀ. ሩቅ ምሥራቅ ሀገሮች
   ለ. በአንታርክቲክ አካባቢ
   ሐ. ሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮፓና እስያ አካባቢዎች
   መ. በደቡባዊ አፍሪካ
4. ከሚከተሉት አንዱ የሕዝብ ሥርጭትን የሚወስን ተፈጥሮአዊ ምክንያት አይደለም፡፡
   ሀ. የምጣኔ ሀብታዊ የዕድገት ደረጃ
   ለ. የአየር ንብረት
   ሐ. የአፈርና የእፅዋት ሀብት
   መ. የመሬት አቀማመጥ
5. በዓለም ዝቅተኛ ሥፍራ የሚገኝበት አካባቢ ______________ ይባላል፡፡
   ሀ. የኮባር ረባዳማ አካባቢ
   ለ. ሙት ባሕር
   ሐ. የጋንጀስ ሸለቆ
   መ. የአልኳታር ረባዳማ አካባቢ
6. ከሚከተሉት አንዱ እጅግ በጣም የተበታተነ የሕዝብ ሥርጭት ያለው አካባቢ ነው፡፡
   ሀ. የናይል ሸለቆ
   ለ. ጃፓንና ሕንድ
   ሐ. የሐሩር በረሃማ አካባቢዎች
   መ. ቻይናና ባንግላዴሽ
7. በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ የተመሠረተው ______________ ነው፡፡
   ሀ. በኢንዱስትሪ
   ለ. በእርሻ
   ሐ. በቱሪዝም
   መ. በንግድ
8. በአፍሪካ የመጀመሪያው የፖለቲካ ፓርቲ የተቋቋመው በ__________ነው፡፡
   ሀ. ኬንያ
   ለ. ደቡብ አፍሪካ
   ሐ. ቱኒዚያ
   መ. ግብጽ

**መ. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተገቢ ቃላት ወይም ሐረጋት ሙሉ፡፡**

1. በታንጋኒካ በቅኝ ገዢዎች ላይ የተነሣው አመጽ ____________ ይባላል፡፡
2. በጀርመን የናዚ ፓርቲ መሪ የነበረው ________ ይባላል፡፡
3. በአፍሪካ ትልቁና ሞቃታማው በረሃ________________ ነው፡፡
4. የሕዝቦችን የአኗኗር ሁኔታ የሚወስኑት ___________፣___________ ናቸው፡፡
5. ከምሥራቅ እስያ በከፍተኛ የሕዝብ ክምችት የሚታወቁት ሀገሮች ___________እና _______________ ናቸው፡፡

**ሠ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡**

1. የጥንታዊ ቻይና ሥልጣኔ ለዓለም ያበረከተውን አስተዋጽኦ ዘርዝሩ፡፡
2. በአማርኛና በኢጣሊያ ቋንቋዎች በተዘጋጁት የውጫሌ ውል ቅጂዎች መካከል የነበረውን ልዩነት ግለጹ፡፡
3. በቀዝቃዛው በረሃ አካባቢ የሕዝቦች ዋነኛ መተዳደሪያ ምንና ምን ናቸው?
4. የኢንዱስትሪ አብዮት ያስከተለውን ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ዘርዝሩ፡፡

## ፍተሻ

*የምታውቋቸውን ክንውኖች በመለየት በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ይህንን (✓) ምልክት አኑሩ፡፡*

1. የሰባቱን አኅጉራት ካርታ እሠራለሁ፡፡ ☐
2. የአኅጉራትን አንጻራዊ መገኛ እገልጻለሁ፡፡ ☐
3. የዓለም አኅጉራት ቆዳ ስፋት አወዳድራለሁ፡፡ ☐
4. የዓለም ከፍተኛና ዝቅተኛ ቦታዎችን እለያለሁ፡፡ ☐
5. የዓለም ታላላቅ ሐይቆችና ወንዞችን እለያለሁ፡፡ ☐
6. በዓለም የሚነገሩ ዋና ዋና ቋንቋዎችን እገልጻለሁ፡፡ ☐
7. ዋና ዋና የዓለም ቋንቋዎች መገኛን በካርታ ላይ አመለክታለሁ፡፡ ☐
8. ጥንታዊ የዓለም ሥልጣኔዎች ያበረከቱትን አስተዋጽኦ እገልጻለሁ፡፡ ☐
9. ጥንታዊ የዓለም ስልጣኔዎች ያበረከቱትን አስተዋጽኦ አደንቃላሁ፡፡ ☐
10. የዓለም ዋና ዋና ሃይማኖቶችን ሥርጭት እገልጻላሁ፡፡ ☐
11. የሌሎች ሃይማኖቶችን እኩልነት እገልጻለሁ፡፡ ☐
12. ሕዝብ በጣም ተጠጋግቶና ተበታትኖ የሚኖርባቸውን የዓለም አካባቢዎች እለያለሁ፡፡ ☐
13. የዓለም የሕዝብ ሥርጭት የተለያየበትን ምክንያት እለያላሁ፡፡ ☐
14. በዓለም ላይ የሚገኙትን የተለያዩ የአኗኗር ዘይቤዎች አደንቃለሁ፡፡ ☐
15. አኗኗራችንን ከሌሎች ሕዝቦች አኗኗር ጋር አነጻጽራለሁ፡፡ ☐
16. የእስልምና ይማኖት አመጣጥን መጥቀስ እችላለሁ፡፡ ☐
17. የክርስትና ሃይማኖት አነሳስና ዕድገትን በአጭሩ ማስቀመጥ እችላለሁ፡፡ ☐
18. በዓለም ላይ ከፍተኛ (የተጠጋጋ) እና ዝቅተኛ (የተበታተነ) የሕዝብ ክምችት ያላቸውን ቦታዎች መለየት እችላለሁ፡፡ ☐

**ምዕራፍ ሁለት**

# ገጸ ምድርን የሚለውጡ ኃይሎች

*ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጠቃላይ ውጤቶች*

**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-**

- የመሬትን ገጽ የሚለውጡ ኃይሎችንና የሚያስከትሉትን ተጽእኖዎች ትገልጻላችሁ፡፡
- በካርታ ላይ ርቀትንና ስፋትን ትለካላችሁ፡፡

## 2.1 የመሬት ውጫዊ ኃይሎችና በሰው ልጅ አኗኗር ላይ የሚያስከትሉት ለውጥ

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት:-*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ**

- የመሬት ገጽታን የሚለውጡ ውጪያዊ ኃይሎችን ትገልጻላችሁ፡፡
- ሸርሸራና ደለል በመሬት ገጽ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ ትለያላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ሸርሸራ
- ክምችት
- ደለል

### ◈ የመሬት ወለል ገጽታን የሚለውጡ ውጪያዊ ኃይሎች

- የመሬት ወለል ገጽታን የሚለውጡ ውጪያዊ ኃይሎችን ዘርዝሩ፡፡
- በግጥግጦሽ፣ ፍርፈራ፣ ሸርሸራና ክምችት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት አብራሩ፡፡

ሸርሸራና ክምችት የመሬትን ገጽ የሚያስተካክሉ ወይንም የሚለውጡ ውጪያዊ ኃይሎች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ግጥግጦሽ (Denudation) እና የድንጋይ ፍርፈራም (weathering) የመሬትን ገጽ ከመለወጥ አንጻር ጉልህ ተጽእኖ አላቸው፡፡

## ውጪያዊ ኃይሎች ሦስት ዓይነት ሂደቶችን ያከናውናሉ፡፡

### ግጥግጦሽ (Denudation)

ይህ እንቅስቃሴ የመሬትን ወለል ዝቅ የማድረግ ወይንም የማስተካከል እንቅስቃሴ ነው፡፡ የግጥግጦሽ እንቅስቃሴ ፍርፈራንና ሽርሽራን ያጠቃልላል፡፡ ፍርፈራ አለቶችን ቀስ በቀስ የመሰባበርና ወደ ትናንሽ አካላት የመቀየር ሂደት ነው፡፡ ፍርፈራ በሁለት ይከፈላል፡፡

### 1. የአለቶች መሰባበር (Physical weathering)

የአለቶች መሰባበር አንዳንድ ጊዜ ሜካኒካዊ ፍርፈራ ይባላል፡፡ የአለቶች መሰባበር ማለት ተፈጥሮአዊ አለቶችን ወደ ደቃቅ አካልነት የመቀየር እንቅስቃሴ ነው፡፡ አለቶች ለሙቀትና ለቅዝቃዜ ሲጋለጡ መሰነጣጠቅና መሰባበር ይጀምራሉ፡፡ የዛፍ ሥሮች በአለቶች ስንጥቅ ጠልቀው በመግባት ስንጥቆቹን የበለጠ ያሰፏቸዋል፡፡ ቀዝቃዛ የአየር ንብረት ባለበት አካባቢ በስንጥቆቹ መካከል ውኃ ይገባል፡፡ ውኃው በቅዝቃዜ ምክንያት ወደ በረዶነት ስለሚቀየር አለቶቹን በማሳበጥ፣ በመሰነጣጠቅ፣ በመሰባበር ወደ ደቃቅ አካልነት ይለውጣቸዋል፡፡

### 2. ኬሚካላዊ ፍርፈራ (Chemical weathering)

ኬሚካላዊ ፍርፈራ የአለቶችን ይዘት የሚለውጡ በርካታ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል፡፡ እነዚህ እንቅስቃሴዎች ጎልተው የሚታዩት ሙቀትና እርጥብ በአለበት ሥፍራ ነው፡፡ ቀዝቃዛና ደረቅ የአየር ንብረት በሚፈራረቅባቸው አካባቢዎች እንቅስቃሴዎቹ በጣም አዝጋሚዎች ናቸው፡፡ ከእንቅስቃሴዎቹ በጣም የተለመደው **ውክሰዳ** (Oxidation) ነው፡፡ የመዳብና የብረት ዝገት የውክሰዳ ውጤት ነው፡፡ ውክሰዳ ማለት የኦክስጂንና የማዕድናት መዋሐድ ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል በዝናብ ውስጥ የሚገኙ ደካማ አሲዶች እንደ ኖራ ድንጋይ ያሉትን አለቶች ያሟሟል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ወይም ሂደት **ክሰላ**(Carbonation) ይባላል፡፡

> ውኃ ከካርቦንዳይኦክሳይድ ጋር ሲደባለቅ →ካርቦኒክ አሲድ→የኖራ ድንጋይ በሟሟትና በመሸርሸር ዋሻ ይፈጥራል፡፡ ለምሳሌ የሶፍ ዑመር ዋሻ ባሌ ዞን ውስጥ የሚገኘው በወይብ ወንዝ አማካይነት የተፈጠረ ዋሻ ነው፡፡

የዝናብ ውኃ መሬት ውስጥ እየሰረገ የሚፈጥራቸው የመሬት ውስጥ ወንዞችም ከመሬት ሥር የሚገኘውን የኖራ ድንጋይ በማሟሟት በሂደት የመሬት ውስጥ መተላለፊያዎችንና ዋሻዎችን ይፈጥራሉ፡፡ ዋሻዎቹም በተራቸው **ስርግርጌ** (Stalactite)፣ **ጉልት ካልሲት** (Stalagmite)፣ ዓምዶች (Pillars) የመሳሰሉትን አካላት ይፈጥራሉ፡፡ (ምስል 2.1 ን ተመልከቱ)፡፡

- **ስርግርጌ (Stalactite)፡-** የሚባሉት ከዋሻዎቹ ጣራ ላይ ቁልቁል የሚንጠለጠሉ የኖራ ድንጋይ አካላት ናቸው፡፡
- **ጉልት ካልሲት (Stalagmites)፡-** የሚባሉት ከዋሻዎቹ ወለል በመጀመር ቀስ በቀስ ወደላይ እየተቆለሉ ሄደው በመጨረሻም የኖራ ድንጋይ ዓምድ የሚፈጥሩ አካላት ናቸው፡፡
- **ዓምዶች (Pillars)፡-** እነዚህ ደግሞ ዋሻዎቹ ውስጥ ስርግርጌ እና ጉልት ካልሲቶች ሲገናኙ የሚፈጥሯቸው የኖራ ድንጋይ ምሰሶዎች ናቸው፡፡

## 2. ሸርሸራ (Erosion)

- ሸርሸራ ምንድን ነው?
- የሸርሸራ ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
- በትምህርት ቤታችሁ ወይም በመኖሪያ አካባቢያችሁ በቅርብ ጊዜ ስላያችሁት የተሸረሸረ መሬት ሁኔታ ግለጹ፡፡
- ስለ ሸርሸራ ምክንያቶች አስተያየት ስጡ፤ የተሸረሸረው አፈርም ወዴት እንደሚሄድ ግለፁ፡፡



ምሥል 2.1 ስርግርጌ እና ጉልት ካልሲት

የተሰባበሩ አለቶች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በፍሰተ ገጽ (running Water)፣ በበረዶ፣ በንፋስና በውቅያስኖስ ሞገድ ተጠርገው ወይም ታጥበው የሚወሰዱበት ሂደት ሽርሸራ ይባላል፡፡ ውኃ በመሬት ወለል ላይ የጎርፍ መውረጃ ቦዮችን ይፈጥራል፡፡ ቦዮቹ ጥልቀትና ስፋት እያገኙ ሲሄዱ ከተራ ጎርፍ መውረጃነት አልፈው ትላልቅ ወንዞች ይሆናሉ፡፡

በንፋስ ኃይል እየተወሰደ በሌላ ቦታ የሚከማች **የደቃቅ አሸዋ ክምችት(Loess)** ሌላኛው የሸርሸራ ውጤት ነው፡፡ በንፋስ ኃይል እየተገፋ የተወሰደው አሸዋ ብዙ ርቀት ተጉዞ በሌላ ቦታ አዲስ አፈር ወይንም አዲስ የአሸዋ ክምችት ይፈጥራል፡፡ ለምሳሌ በቅርቡ ከሰሐራ በረሃ በንፋስ ሞገድየተወሰደ አሸዋ የአትላንቲክ ውቅያኖስን አቋርጦ በደቡብ አሜሪካ አማዞን ተፋሰስ ውስጥ አዲስ ለም አፈር መፍጠሩ በምርምር ተደርሶበታል፡፡ በተጨማሪ በየዓመቱ ከጎቢ በረሃ (Mongolia) በንፋስ ኃይል ግፊት ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ የሚወስደው አፈር ሰሜናዊ የቻይና ሜዳማ አካባቢዎች ሲደርስ ለእርሻ ሥራ ምቹና ጤናማ ተፋሰስ ይፈጥራል፡፡ ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ከተራራ ላይ በዝግታ የሚንሸራተት ግግር በረዶ (Glaciers) በካናዳ፣ በምዕራብ አውሮፓ እና በሩስያ መሬቱን ሲያርስና ገጸምድሩን (Land Scape) ሲለውጥ ቆይቷል፡፡ በዚህ የተነሣ በአካባቢው ስስ አፈር የያዘ ገጸምድር ተፈጥሯል፡፡ የአካባቢውን ሥርዓተ-መትርብ (Drainage System) አዛብቷል፡፡

በባሕር ጠረፋማ አካባቢዎች ደግሞ ቀላይ ሞገድና፣ ማዕበላዊ ሞገድ የመሳሰሉት አዳዲስ ገጸምድሮችን ከመፍጠራቸውም በላይ የሰውን ልጅ የአኗኗር ሥርዓት የተለያየ ያደርጋሉ፡፡


- የሸርሸራን ምንነት ለመረዳት ከዚህ በታች የቀረቡትን ምስሎች በደንብ ማጤን ያስፈልጋል፡፡




ምሥል 2.2 የቦይ ሸርሸራ (Gulley Erosion)



ምሥል 2.3 ወጥነት ያለው የሠፊ አካባቢ ሸርሸራ (Sheet Erosion)



*ምሥል 2.4 የንፋስ ሸርሸራ*





*ምሥል 2.5 የበረዶ ክምችት ሸርሸራ*

## 3. ክምችት (Deposition)

- ክምችት ምንድን ነው?
- በሸርሸራና በክምችት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?


ክምችት የፍርፈራና የሸርሸራ የመጨረሻ ውጤት ነው፡፡ የተሰባበሩ አለቶች፣ አሸዋና አፈር በውኃ፣ በንፋስ፣ በበረዶ፣ በውቅያኖስ ሞገድ እና በስበት ኃይል ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ተጓጉዘው በአንድ ቦታ ላይ በተለያዩ መንገዶች ይከማቻሉ፡፡ ለምሳሌ የስበት ኃይል ቅጽበታዊ የሆነ ግዝፈተ-ጉዞት (Mass Movement) ያስከትላል፡፡ በዚህ ጊዜ የመሬት መንሸራተት (Land Slide) እና የጭቃ ጎርፍ (Mud flow) ይፈጠራል፡፡ ጅረቶችና ወንዞች ዝቅተኛ ቦታ ላይ ሲደርሱ የተሸከሙትን አሸዋና ለም አፈር ያከማቻሉ፡፡ (ምስል 2.6 ተመልከቱ) የጅረቶችና የወንዞች የውኃ ብዛት መጠን፣ የፍሰት ፍጥነት ሲቀንስ የተሸከሙትን ዝቃጭ ረጅም ርቀት ማጓጓዝ ስለማይችሉ በየትኛውም ሥፍራ ያከማቹታል፡፡ አዲስ የተከማቸው አፈር በወንዞቹ መውረጃ ቦይ፣ ሜዳማ የባሕር ዳርቻዎች፣ በኮረብታና ተራራዎች ግርጌ አካባቢ ሰተቶ ደለል (Alluvial Plains) ይፈጥራል፡፡ ትላልቅ ወንዞች ለምሳሌ እንደ ናይል፣ ሚሲሲፒ እና አማዞን የመሳሰሉት ባሉበት ቦታ ደግሞ ሰፊ ደለል(Delta) ይሠራሉ፡፡ አንዳንዴም ባሕር ውስጥ ርቀት ተጉዘው ይከማቻሉ፡፡




*ምሥል 2.6 ሸርሸራና ክምችት የመሬትን ቅርጽ ይለውጣሉ፡፡*


## ◈ የሸርሸራ ውጤቶች

ከየብስ ክፍል አስራ አንድ በመቶ የሚሆነው ለእርሻ ሥራ ተስማሚ ነው፡፡ በየብስ ላይ አንድ ሳንቲ ሜትር ውፍረት ያለው አፈር ለማግኘት ከአንድ መቶ እስከ አራት መቶ ዓመታት ይወስዳል፡፡ ለእርሻ ሥራ አመቺ የሚሆን አፈር ለማግኘትና የአፈሩ ጥልቀት በሚፈልገው ደረጃ ለመድረስ ከ30 እስከ 120 ዓመታት ይፈጃል፡፡ ይሁን እንጂ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ ሲከማች የቆየውን ይህን እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነውን ሀብት የሰው ልጅ ያለአግባብ ያባክነዋል፡፡ ሸርሸራ የከፋና ፈጣን የሚሆነው በተለይ ዝናብ ወቅትን ጠብቆ የማይመጣና አስተማማኝ ሳይሆን ሲቀር ነው፡፡ የእጽዋት ሽፋን መመንጠር፣ ልማዳዊ አስተራረስ፣ የእርከን ያለመኖር የዝናብን ውኃ የማስቀረት (ከመፍሰስ የማዳን) አቅም ይቀንሳል፡፡ ወደ መሬት የሚሰርገው የውኃ መጠን በእጅጉ እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ ስለዚህም አፈሩ ለንፋስ ሸርሸራ ይጋለጣል፡፡




*ምሥል 2.7 የአፈር ሸርሸራና ውጤቶቹ*

ሸርሸራ ምድረ- በዳነትን ያስከትላል። ምድረ-በዳነት ደግሞ በረሃማነት ማለት ነው። በረሃማነት ጎልቶ የሚታየው ከፊል በረሃማነት ባላቸውና የዝናብ መጠናቸው አስተማማኝ ባልሆኑ አካባቢዎች ነው።




| በጣም አስከፊ አደጋ ውስጥ ያሉ ሐገሮች | በአስከፊ አደጋ ውስጥ ያለው የሰዎች ብዛት ከየሀገሮቹ የሕዝብ ብዛት በመቶኛ |
|---|---|
| ኢትዮጵያ | 18% |
| ሱዳን | 23% |
| ቻድ | 30% |
| ኔጄር | 42% |
| ሱማሊያ | 26% |

*ምሥል 2.8 የምድረ-በዳነት አደጋ የሚያሰጋቸው አካባቢዎች*



*ምስል 2.9 የደን ምንጠራ የበረሃማነት መስፋፋትን ያስከትላል፡፡*

## ውስን ጥናት

በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አርባ በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ አካባቢ የቆዳ ስፋት በደኖች የተሸፈነ ነበር፡፡ አሁን ግን ደን የለበሰው የኢትዮጵያ የቆዳ ስፋት ከሁለት በመቶ አይበልጥም፡፡ የሸለቆ ተፋሰሶቿ እንዲሁም የተራራ ተዳፋቶቿ ሰፋፊና ለም የእርሻ ቦታዎች ነበሩ፡፡ ተራሮች በሙሉ በደን የተሸፈኑ ነበሩ፡፡ ብዙ ጅረቶችና ወንዞች ለመስኖ የሚያገለግል ከፍተኛ የውኃ ክምችት ነበራቸው፡፡

የሣር ሜዳዎች ዓመቱን ሙሉ በቂ የውኃ መጠን ነበራቸው፡፡ የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመምጣቱ የደኖች ለእርሻ ቦታ፣ ለመኖሪያ ቤት ግንባታና ለምግብ ማብሰያ ያለማንም ከልካይ ተመነጠሩ፡፡ አብዛኛው አካባቢ የደን ሽፋን በማጣት አቧራ የሚነፍስበት እርቃኑን የቀረ ባዶ ሜዳ ሆነ፡፡ ከተራራዎች ያለማቋረጥ ይፈሱ የነበሩት ምንጮች ቀስ በቀስ እየቀነሱ ደረቁ፡፡ የዝናብ መጠኑ ከመቀነሱ ሌላ የክረምቱ መግቢያ እየዘገየ መውጫው ደግሞ እየፈጠነ በመምጣቱ ድርቅና ረኃብ በየጊዜው በተደጋጋሚ የሚመጣ ክስተት ሆነ፡፡ በዚህ የተነሣ የአካባቢው ሰዎች ከአካባቢያቸውና ከቀዬያቸው ተፈናቀሉ፡፡ መሥራትና ማምረት የሚችሉ እጆች ለምግብ እርዳታ ተዘረጉ፡፡ ይህ ሁሉ ችግር የተፈጠረው የደን ሽፋን በወደመበት አካባቢ አፈሩ በከፍተኛ ሁኔታ ለሸርሸራ በመጋለጡ ነው፡፡ ስለዚህ የአካባቢያችንን ደኅንነት ለመጠበቅ የንፋስ ሸርሸራ መከላከያ ዛፎች መትከል፣ የግጦሽ ሣር ለማግኘት የመስኖ ውኃ መጠቀም፣ ድነናና ዳግም ድነና ማካሄድ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

## ◈ የክምችት ውጤቶች

- **የክምችት ውጤቶች ምን ምንድን ናቸው?**

ሸርሸራ በሰው ልጆች ሕይወት ወይንም የአኗኗር ሥርዓት ላይ የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ተመልክተናል፡፡ በመቀጠል ክምችት በሰው ልጆች ሕይወት ወይም አኗኗር ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ እንመለከታለን፡፡
ሱዳንና ግብጽን በመሳሰሉ ሀገሮች የወንዝ ሸርሸራ ከከፍተኛ ቦታዎች ጠራርጎ የሚወሰደው ለም አፈር በወንዞች ዳርቻ እየተከማቸ በዚያ ያለውን ምድረ በዳ ለእርሻ ምቹ አካባቢ አድርጓል፡፡ በአንዳንድ የደቡብ ምሥራቅ እስያ ሀገራት ደግሞ በኃይለኛው ሠገር ዝናብ (Monsoon rain) የተነሣ የሚመጣውን የዝናብ ውኃ በተራራማ አካባቢዎች የሚገኙ ዛፎች ሊከላከሉት እንዲሁም ሥሮቻቸው የጎርፉን ፍጥነት ማዘግየት ስለማይችሉ ውኃው ቀልቀል እየተምዘገዘገ በመውረድ የመሬት መንሸራተት (Land Slide) ያስከትላል፡፡ በዚህም በመንደሮች፣ በሰዎችና በእንስሳት፣ በእርሻ ማሳዎችና በመንገዶች ላይ ከፍተኛ አደጋ ይከሰታል፡፡ ወንዞች በደለል ከመሞላታቸውም በላይ ተደጋጋሚና አስከፊ የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ ይከሰታል፡፡

**ስምሳሌ:-** በባንግላዴሽ ከሂማሊያ ተራራዎች የሚነሡ ወንዞች ከደን አልባ አካባቢዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ መጠኑ እየጨመረ የሚሄድ ደለል ይዘው በመምጣት በወንዞቹ ታችኛው ክፍል (lower Course) ላይ ያከማቻሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የወንዞቹ የደለል ክምችት እየጨመረ ሲሄድ የወንዞቹ መውረጃ ቦዮች ሙሉ በሙሉ ስለሚዘጉ የጐርፍ መጥለቅለቅ አደጋን ያስከትላሉ፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች 2.1**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- የመሬት ወለል ገጽ ለዋጭ ኃይል ስንል ምን ማለታችን ነው?
- የሚከተሉትን ቃላት ትርጉም ስጡ፡፡ ግጥግጦሽ፣ ፍርፈራ፣ ስርግርጌ፣ ጉልት ካልሲት፣ ምሰሶዎች(ዓምዶች)
- የፍርፈራ ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
- ውክስዳና ክሰላ ያላቸው ግንኙነት ምንድን ነው?
- የሸርሸራንና የክምችትን ምንነት እንዲሁም ውጤታቸውን አስረዱ፡፡

***ለ. የቡድን ሥራ***

- በአካባቢያችሁ የሚታየውን የሸርሸራ ችግር አብራሩ፡፡
- የሸርሸራ ችግርን ለመፍታት መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ዘርዝሩ፡፡

***ሐ. የሚሠሩ ተግባራት***

- በአካባቢያችሁ ከሸርሸራ ጋር በተያያዘ የተመለከታችኋቸውን ሁኔታዎች መዝግቡ፡፡
- የመዘገባችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማቅረብ ተወያዩበት፡፡

## 2.2 የመሬት ገጽ ለዋጭ ውስጣዊ ኃይሎችና በሰው ልጅ አኗኗር ላይ የሚያስከትሉት ለውጥ

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- የመሬት ገጽታን የሚለውጡ ውስጣዊ ኃይሎችን ትገልጻላችሁ::
- የመሬት ገጽታ የሚለውጡ ውስጣዊ ኃይሎች በመሬት ገጽ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ ታስረዳላችሁ::

**ቁልፍ ቃላት**

- ቅልብሽ
- ዝንፈት
- ገሞራ ሕጽም
- ገሞራ ትፍ
- ምቅማጥ ተራራ
- የመሬት መንቀጥቀጥ
- ንቅ-ገሞራ
- ገሞራዊነት

### ◈ የመሬት ገጽታ ለዋጭ ውስጣዊ ኃይሎች


- የመሬትን ገጽ ለዋጭ ውስጣዊ ኃይሎች ምንድን ናቸው?

የመሬት ገጽ ለዋጭ ውስጣዊ ኃይሎች አንዳንድ ጊዜ ውስጠ - መሬት ለውጥ (Endogenic forces) ተብለው ይጠራሉ:: የውስጣዊ ኃይሎች የጉልበት መነሻ ውስጣዊ የመሬት አካል ነው:: ውስጣዊ ኃይሎች በቅርፊተ መሬት ላይ የተለያዩ መልክአ ምድሮችን ይገነባሉ:: የመሬት ገጽ ለዋጭ ውስጣዊ ኃይሎች ቅልብሽ፣ ዝንፈት፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም ርዕደ ምድር እና ገሞራዊነት በመባል ይታወቃሉ:: የቅርፊተ መሬት ገጽ (outer crust) ከተለያዩ አለቶች የተገነባ ነው:: የአለቶች ንብርብር የሚፈጥረው ጫና በቅርፊተ መሬት ላይ እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ያደርጋል:: ይህ እንቅስቃሴ አለቶች በተለያየ አቅጣጫ እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ በመሬት ገጽ ላይ የተለያየ የመልክአ ምድር ዓይነት እንዲታይ ያደርጋል::


#### ሀ. ቅልብሽ (Folding)

ከመሬት ውስጥ የሚመነጨው ኃይል በውጪኛው ቅርፊተ - መሬት ላይ የሚገኙትን አለቶች እንዲቀለበሱና እንዲዛነፉ ሲያደርግ በመሬት ገጽ ላይ የተቀለበሱና የተዛነፉ የተለያዩ የመሬት ቅርጾች ይፈጠራሉ::

በቅርፊተ - መሬት የውስጠኛው ክፍል ሁለት ስፍሃኖች (Plates) በተቃራኒ አቅጣጫ አንዱ ወደሌላው ሲንቀሳቀስ ይጋጫሉ:: ግጭታቸው ደግሞ በመሬት ገጽ ላይ መቀልበስን ያስከትላል:: ቅልብሽ በመሬት ገጽ ላይ ተራሮች እንዲፈጠሩ ያደርጋል:: ለምሳሌ በሰሜን ምዕራብ አፍሪካ- አትላስ፣ በደቡብ ምዕራብ አፍሪካ ደግሞ ኬፕ ሬንጅ የተራራ ሰንሰለት፣ በአውሮፓ- የአልፕስ የተራራ ሰንሰለት፣ በሰሜን አሜሪካ-የሮኪ ተራራ፣ በእስያ የሂማሊያ፣ በደቡብ አሜሪካ የኤንደስ ተራራ የተፈጠሩት በቅልብሽ ነው:: (ምስል 2.10ን እና ምስል 2.11ን ተመልከቱ)::




ምሥል 2.10 ማቀልበሸና ማዝነፍ




ምሥል 2.11 የቅልብሽ ዓይነቶች

## ሰ. ዝንፈት (Faulting)


- ዝንፈት ምንድነው?
- የዝንፈት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
- በዝንፈት ምክንያት የተፈጠሩ ጥቂት የመሬት ገጾችን ጥቀሱ፡፡

ዝንፈት የሚከሰተው የመሬት ንጥነጣዊ እንቅስቃሴ በሚፈጥረው ግፊት የተነሣ አለቶች ከተለያየ አቅጣጫ ወደ አንድ አቅጣጫ ሲገፉ፣ አንዱ በሌላው ላይ ሲጫን ወይም አንዱ ከሌላው ሥር ገብቶ ሲገኝ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ አለቶች በሌላ አለቶች ላይ ወደጎን ይንሸራተታሉ፡፡

ዝንፈት ለምቅማጥ ተራሮች(Block mountain)፣ ለስምጥ ሸለቆና ለአምባ ምድር መፈጠር ምክንያት ነው፡፡ ምቅማጥ ተራሮች የሚፈጠሩት በአብዛኛው በሁለት ትይዩ ስንጥቆች መካከል ያለው መሬት ወደ ላይ ተገፍቶ በሚመጣበት ጊዜ ነው፡፡

የዝንፈቶች አቀማመጥ እና የኃይሉ **አማቂ ኃይል** ወደ ላይ እንዲነሣ የተገደደው የቅርፊተ መሬት አካል ምቅማጥ ተራሮች **(Block Mountains)** ተብሎ ሲጠራ ወደ ታች በመስመጥ ዝቅ የሚለው የቅርፊተ - መሬት አካል ደግሞ ስምጥ ሸለቆ (Rift valley) ይፈጥራል፡፡ ከስምጥ ሸለቆው ግራና ቀኝ የሚገኙ ያልሰመጡ የመሬት ክፍሎች ደግሞ አምባ ምድር ይፈጥራሉ፡፡ ታላቁ የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆና የኢትዮጵያ አምባ ምድሮች የተፈጠሩት በዚህ መንገድ ነው፡፡

የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ የዓለም ትልቁ ስምጥ ሸለቆ አካል ነው፡፡ ይህ ሸለቆ ርዝመቱ ከሶርያ እስከ ሞዛምቢክ ይደርሳል፡፡ የኢትዮጵያ ሰምጥ ሸለቆ የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ አካል ሲሆን በውስጡ ንቅ እሳተ ገሞራዎች፣ በርካታ ሐይቆች፣ ፍልውሃዎች፣ ፍልቅልቆች(Fumarols) እና ፍል ጉነቶች (geysers) ወ.ዘ.ተ. ይገኛሉ፡፡





*ምሥል 2.12 ታላቁ የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ*


## ሐ. ገሞራዊነት (Volcanism)

ገሞራዊነት የጠጣርነት፣ የፈሳሽነት ወይንም የጋዝነት (የአየርነት) ባሕርይ ያላቸው የማዕከለ መሬት አለቶች ወደ ቅርፊተ - መሬት እንዲገቡ የሚገደዱበትን ወይንም በቀጥታ ወደ መሬት ወለል ተገፍትረው የሚወጡበትን ሂደት በሙሉ ያመላክታል፡፡ ምንም እንኳ በማዕከለ መሬት አለቶች ከፍተኛ ሙቀት ያላቸው ቢሆንም ቅርፊተ - መሬት በሚያሳድርባቸው ከፍተኛ ግፊት ምክንያት በከፊል ጠጣርነት መልክ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ በቅልብሽና

በዝንፈት መፈጠር ሂደት ወይንም በመሬት ስፋሃኖች (Plates) ድንበር አካባቢ የመሬት የአግድም እንቅስቃሴ (Horizonal earth movement) ሲኖር በማዕከለ መሬት ላይ የተጫነው የግፊት መጠን ይቀንስና በከፊል ጠጣርነት መልክ የነበሩት የማዕከለ መሬት አለቶች ሙሉ በሙሉ በመቅለጥ ወደ ቅርፊተ - መሬት ደካማ አካባቢዎች ወይንም በቀጥታ ወደ መሬት ወለል ይወጣሉ። መሬት ወለል ላይም ከደረሱ በኋላ በመቀዝቀዝ እንደገና ወደ ጠጣር አለትነት ይቀየራሉ። የቀለጠው አለት መሬት ውስጥ ሲሆን ገሞራ ሕጽም (Magma) ሲባል መሬት ወለል ላይ የደረሰው ደግሞ ገሞራ - ትፍ (Lava) ይባላል።




*ምሥል 2.13 የውጪያዊና የውስጣዊ ገሞራዊነት ባሕርያት*




## ውስን ጥናት

### እሳተ ገሞራ

የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ በሕይወትና በንብረት ላይ ከፍተኛ ውድመት ያስከትላል። በዓለማችን በተለያዩ ዘመናት አሳዛኝና አሰቃቂ ጉዳት ያደረሱ ፍንዳታዎች ተከስተዋል። ለምሳሌ በ2ኛው ክፍለ ዘመን እ.አ.አ በ79 የፈነዳው የቪሱቭየስ እሳተ ገሞራ በጣሊያን የፓምፔ ከተማንና በርካታ ነዋሪዎቿን አመድ ውስጥ ቀብሯል። እንዲሁም እ.አ.አ በ1875 ጃቫ አጠገብ ክራካቶ የተከሰተው የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ እስከዛሬ ድረስ በሰው ልጅ ታሪክ ታይቶ አይታወቅም።

እ.አ.አ በ1894 በማርቲንክ ደሴት (ምዕራብ ኤንዲስ) በሚገኘው የፔሊ ተራራ ላይ የተከሠተው የእሳተ - ገሞራ ፍንዳታም የቅዱስ ፔር ከተማን በሚንበለበል የጋዝና የአመድ ደመና ከመሸፈኑ በላይ ለ25,000 ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት ነበር።

እ.አ.አ በ1935 በመካከለኛው ሜክሲኮ በታረሱ የሰብል ማሳዎች መካከል የፓርኩቲን እሳተ - ገሞራ የፈነዳው በድንገት ያለበቂ ቅድመ - ማስጠንቀቂያ ነበር። ይህ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታም ያለማቋረጥ ለአራት ዓመታት ዘለቋል፡፡ በዚህ ቆይታው 2000 ጫማ ርዝመት ያለውን ተራራ በመፍጠር አካባቢውን ሙሉ በሙሉ አመድ ውስጥ ቀብሯል፡፡

## ውስን ጥናት

### ኤርታሌ

ኤርታሌ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ንቅ እሳተ ገሞራ የሚገኝበት አካባቢ ነው፡፡ ኤርታሌ የሚለው ቃል በአፋርኛ ቋንቋ "የሚጨሰው ተራራ" ማለት ነው፡፡ ኤርታሌ በአፋር በረሃ አስደናቂና ማራኪ ውበት ያለውና ከጎብኚዎች ሕሊና በቀላሉ የማይረሳ ትዝታ የሚፈጥር ተፈጥሯዊ የጎብኝዎች መስህብ ነው፡፡ በኤርታሌ ጉብኝት ለማድረግ የሚመከረው ጊዜ ማለዳ ነው፡፡ ምክንያቱም ከረፈደ በኋላ የአካባቢው ሙቀት በጣም ስለሚጨምር ከፍታው እየጨመረ የሚሄደውን አቀበት መውጣት አስቸጋሪ ነው፡፡ ምንም እንኳ በቅርብ ከሚገኘው መንደር እስከ ኤርታሌ ያለው ርቀት ሦስት ሰዓት ያክል የሚያስኬድ ቢሆንም ሰዓቱ እየረፈደ ሲሄድ ሙቀቱን መቋቋም በጣም ከባድ ነው፡፡ በማለዳ ወደ ኤርታሌ ተራራ እናት የሚደረገው ጉዞ ልብ ይሰቅላል፣ ስሜትን ያማልላል፣ አስደናቂ እይታን ይፈጥራል፡፡ በአካባቢው የሚታዩት በርካታ ቆሬዎች (Craters) ግዙፍ የእሳተ ገሞራ ምልክት ያሳያሉ፣ ኃይለኛ ሽታ ያለው ጭስ (fumes) ይተፋሉ፡፡ ቆሬው ጠርዝ ላይ ጎብረ-ቀለማት ያለው ገሞራ ትፍና አመድ ሲወጣ ይታያል፡፡ በተለይ በምሽት ሰዓት በኤርታሌ ዋድያት (Caldera) ባለ ቀይ ቀለም ገሞራ ትፍ ሲፍለቀለቅ ማየት ልዩ ትንግርት ይፈጥራል፡፡ በተለይ ደግሞ ኤርታሌ ንቁ እሳተ-ገሞራ መሆኑና በሁሉም ቦታ የማይገኝ መሆኑ ሲታሰብ ልዩ የደስታ ስሜት ይፈጥራል፡፡




*ምስል 2.14 ኤርታሌ*

### መ) የመሬት መንቀጥቀጥ (Earth quake)

- የመሬት መንቀጥቀጥ ምንድን ነው?
- የመሬት መንቀጥቀጥ ሲያስከትል ስለሚችለው ውጤት አብራሩ፡፡

የመሬት መንቀጥቀጥ የሚከሰተው ሁለት ሰፍሃኖች (Plates) በተቃራኒ አቅጣጫዎች ለመንቀሳቀስ የሚሞክሩበት ቦታ ላይ ነው፡፡ በሰፍሃኖች ግጭት ምክንያት የሚከሰተው ሰበቃ (Friction) እንቅስቃሴያቸውን

ሲገታው ግፊት (Pressure) ይፈጥራል፡፡ በመጨረሻም በድንገተኛ የመሬት የአግድሞ እንቅስቀቃሴ (Horizontal earth movement) የተነሣ ቀደም ብሎ የተፈጠረው ግፊት ወደ ቅርፊተ መሬት ወለል ሲወጣ መሬት ላይ የሚደርሰው ንዝረትና መናጋት የመሬት መንቀጥቀጥ ይባላል፡፡ የግፊት መጀመሪያ ነጥብ የመሬት መንቀጥቀጥ መነሻ (Focus) ሲባል በቀጥታ ከአናት ላይ (የመሬት ወለል አካባቢ) የሚገኘውና ከፍተኛ ንዝረት የሚከሰትበት ነጥብ ደግሞ እንቅጥፍጣፍ (Epicenter) ይባላል፡፡ የንዝረት ሞገድ ከመሬት መንቀጥቀጥ መነሻ ጀምሮ በሁሉም አቅጣጫዎች ይሠራጫል፡፡

የመሬት መንቀጥቀጥ መጠንና ጥንካሬ የሚለካው በሬክተር መለኪያ ነው፡፡

## ◈ ውስጣዊ ኃይሎች በሰው ልጆች አኗኗር ላይ የሚያሳድሩት ተጽእኖ

የመሬት መንቀጥቀጥ ከሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች በበለጠ የሕይወት ጥፋትና የአካል ጉዳት እንዲሁም የንብረት ውድመት ያስከትላል፡፡ በዓለማችን በየዓመቱ ቢያንስ ሁለት ትላልቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ይከሰታል፡፡ በተመሳሳይም በሺ የሚቆጠር ዝቅተኛ የመንቀጥቀጥ መጠን ዓለማችንን ያናውጣል፡፡ በአብዛኛው የመሬት መንቀጥቀጥ ከፍተኛ ውድመት የሚያደርሰው እንቅጥፍጣፍ (Epicenter) ባለበት አካባቢ ነው፡፡ ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት ባለበትና መኖሪያ ቤቶች ተጠጋግተው በተሠሩበት አካባቢ የመሬት መንቀጥቀጥ ውድመት አደገኛ ነው፡፡

### የእሳተገሞራ ፍንዳታ ውጤቶች

የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ እጅግ አስከፊ ውጤቶችን ያስከትላል፡፡ የአደጋው መጠንና ስፋት የተለያየ ቢሆንም በዓለማችን ዘግናኝና መጠነ ሰፊ ችግሮች ታይተዋል፡፡ ለምሳሌ እ.ኤ.አ በግንቦት 18 ቀን 1972 ዓ.ም. በተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች በተለይ በዋሽንግተን የአስተዳደር ክልል **ሴንት ሄለንስ** ተብሎ በሚጠራው ተራራ ላይ የደረሰው የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ያስከተለውን አካባቢያዊ፣ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ቀውስ እንመልከት፡፡

***በእዚህ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ምክንያት፡-***

- በአካባቢው የነበረ የአንድ ተራራ ከፍታ በ390 ሜትር ቀንሷል፡፡
- በተራራው አናት ላይ ስፋቱ 3 ኪሎ ሜትር፣ ጥልቀቱ ደግሞ 0.5 ኪሎ ሜትር የሚሆን የእሳተ ገሞራ ዋድያት ተፈጥሯል፡፡
- ፍንዳታው ባስከተለው መርዛማ ጋዝ 61 ሰዎች ሞተዋል፡፡
- በርካታ የመኖሪያ መንደሮች ፈራርሰዋል፡፡
- በፍንዳታው የተረጨው አመድ የበርካታ ወንዞችና ሐይቆች ሙቀት እንዲጨምር ከማድረጉም በላይ ደለልና ጭቃ የወንዞች መወረጃ ቦዮችን ዘግቷል፡፡
- የተለያዩ የአሳ ዝርያዎች እንዲጠፉና ሐይቆች በደለል እንዲሞሉ አድርጓል፡፡
- ፍንዳታው በአስከተለው የጎርፍ መጥለቅለቅ በርካታ የባቡር ሀዲዶችና የአስፋልት መንገዶች ፈራርሰዋል፡፡ በጎርፉም ተወስደዋል፡፡
- በፍንዳታው ዙሪያ 250 ስኩዌር ኪሎሜትር በሚሸፍነው ደን ውስጥ የነበሩ ዛፎች ከሥራቸው ተነቅለው በጎርፍ ተወስደዋል፡፡
- የመብራትና የስልክ አግልግሎት ተቋርጧል፡፡
- የዱር እንስሳት ሙሉ በሙሉ አልቀዋል፡፡
- ፍንዳታው በፈጠረው አቧራ በማሳ ላይ ከነበረው ሰብል 12 በመቶ ያህሉ ከጥቅም ውጪ ሆኗል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች 2.2

### ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች፡-

- በእንቅጥፍጣፍ እና በመሬት መንቀጥቀጥ መነሻ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
- የሬክተር መለኪያ ምንድነው?
- በአፍሪካ የሚገኙ የቅልብሽና የዝንፈት ምሳሌዎችን ጥቀሱ፡፡
- የገሞራ-ትፍ እና የገሞራ ህጽም ልዩነት ምንድነው?

### ለ. የቡድን ሥራ

በሁለት ቡድኖች ተከፍላችሁ የመጀመሪያው ቡድን የንፋስ ሸርሸራን በተመለከተ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ የበረዶ ሸርሸራን አስመልክቶ መረጃዎችን አሰባስቡ፡፡ ከዚያም በቡድን ተጠሪዎች አማካኝነት የተገኘው መረጃ ለክፍሉ ይቅረብ፡፡ በመጨረሻም በቀረበው መረጃ መሠረት ተጨማሪ ውይይት አድርጉ፡፡

### ሐ. የግል ሥራ

- በቅርቡ በአካባቢያችሁ ስላያችሁት ሸርሸራ ግለጹ፡፡ በተቻለ መጠን የሸርሸራውን ምክንያትና የተሸረሸረው አፈር ወዴት እንደሄደ አብራሩ፡፡
- ስለ ኤርታሌ አጭር የመረጃ ዳሰሳ አድርጉ፡፡ መረጃችሁ የሚከተሉትን ጉዳዮች የሚያሳይ ይሁን፡፡
    - ኤርታሌ የተፈጠረበትን ዘመንና የአፈጣጠሩ ሁኔታ
    - ኤርታሌ የሚሰጠው ምጣኔ ሀብታዊና ሳይንሳዊ ጠቀሜታ

በመጨረሻም እያንዳንዳችሁ የሰበሰባችሁትን መረጃ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማቅረብ የጋራ ውይይት አድርጉ፡፡

### መ. የሚሠሩ ተግባራት

- እምብርተ መሬትን፣ ገሞራ–ህጽምን እና ገሞራ–ትፍን የሚያሳይ ሥዕል ሥሩ፡፡
- የአፍሪካ ካርታ ሠርታችሁ ቅልብሽ ተራራዎች የሚገኙባቸውን ቦታዎች አመልክቱ፡፡

## 2.3 ከካርታ ላይ ርቀትንና ስፋትን መለካት

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- የካርታ መስፈርት ምን ማለት እንደሆነ ታስረዳላችሁ፡፡
- የካርታ መስፈርት የሚገለጽባቸውን የተለያዩ መንገዶች ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የካርታ መስፈርትን በመለዋወጥ ትሰራላችሁ፡፡
- ከካርታ ላይ ርቀትንና ስፋትን ታሰላላችሁ፡፡

## ቁልፍ ቃላት

- ሥዕላዊ መስፈርት
- ሐተታዊ መስፈርት
- ወካይ መስፈርት

## ◈ የካርታ መስፈርት ምንነት

- መሥፈርት ምንድነው?

የካርታ መስፈርት(Scale)፡- በካርታ ርቀትና በመሬት ላይ ባሉ ሁለት ቦታዎች መሐከል ያለውን ርቀት የምናዛምድበት ወይንም የምናመዛዝንበት ዘዴ ነው፡፡

## ◈ የካርታ መስፈርት መገለጫ መንገዶች

መስፈርት በሦስት በተለያዩ መንገዶች ይገለጣል፡፡ እነርሱም፡-


### ሀ. ሐተታዊ መስፈርት (Scale Statement)

ይህ መስፈርት በካርታና በመሬት መካከል ያለውን ግንኙነት በቃላት አማካይነት ለመግለጽ ይጠቀማል፡፡ ለምሳሌ፡- **"አንድ ሴንቲ ሜትር ለአንድ ኪሎ ሜትር"** ማለት በካርታ ላይ አንድ **ሴንቲ ሜትር በመሬት ላይ አንድ ኪሎ ሜትር** ርቀት ይወክላል ማለት ነው፡፡

### ለ. ሥዕላዊ መስፈርት (Graphic Scale)

ይህ መስፈርት ብዙውን ጊዜ በካርታ ግርጌ ይገኛል፡፡ ከካርታ ላይ ርቀት የማንበብ ሥራን ያቀላጥፋል፡፡ በዚህ መስፈርት አንድ ቀጥተኛ መስመር ይሰመርና በሐተታዊ መስፈርቱ መሠረት በአሐዶች (Units) ይከፋፈላል፡፡ በስተግራ ያለው የመስመሩ አካል በአነስተኛ ክፍልፋዮች (fractions) ይከፋፈላል፡፡ በዚህም የተነሣ ከካርታው የተወሰዱ ርቀቶችን ወደ መሬት ርቀት መቀየር ቀላል ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ሐተታዊ መስፈርቱ 1 ሴንቲ ሜትር ለ1 ኪሎ ሜትር ቢሆን ካርታ ላይ 4 ሴንቲ ሜትር የሚወክለውን ርቀት በሥዕላዊ መስፈርት ለማሳየት የሚሰመረው መስመር አራት እኩል ቦታ በአንድ ሴንቲ ሜትር ርቀት ይከፋፈላል፡፡ ይህም ማለት ካርታ ላይ የሚታየው አንድ ሴንቲ ሜትር በመሬት ላይ አንድ ኪሎ ሜትር ርቀት ይወክላል ማለት ነው፡፡

**ምሳሌ** 1 ሴንቲ ሜትር ለ2 ኪሎ ሜትር የሚለውን ሐተታዊ መስፈርት በሥዕላዊ መስፈርት ማሳየት ቢፈለግ የሚከተለውን ይመስላል ማለት ነው፡፡




*ምሥል 2.15 ሥዕላዊ መስፈርት*

## ሐ. ወካይ መስፈርት (Representative Fraction/R.F. Scale)

ወካይ መስፈርት ካርታ ላይ ያለውን ርቀትና መሬት ላይ ያለውን ርቀት በማመዛዘን ወይንም በማመጣጠን(ratio) በቁጥር የሚያስቀምጥ መስፈርት ነው፡፡ ለምሳሌ በሐታዊ መስፈርቱ 1 ሴንቲ ሜትር ለ1 ኪሎ ሜትር (1 ሴንቲ ሜትር ለ 100,000 ሴንቲ ሜትር) ቢሆን በወካይ መስፈርት በማመዛዘን ሲገለጽ 1:100,000 ይሆናል፡፡ በክፍልፋይ (fraction) ደግሞ $\frac{1}{100,000}$ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረት፡-

ከፊት ለፊት የተጻፈው 1 ቁጥር የካርታ ላይ ርቀትን ሲያመለክት ቀጥሎ የተጻፈው 100,000 ደግሞ የመሬት ላይ ርቀትን ያመለክታል፡፡

**ምሳሌ፡-** ከላይ የተሰጠውን ሐተታዊ መስፈርት ማለትም 1 ሴንቲ ሜትር ለ 1 ኪሎ ሜትር የሚለውን በወካይ መስፈርት ለማስቀመጥ የሚከተለውን ቅደም ተከተል እንመልከት፡-

1. የመሬት ላይ ርቀትና የካርታ ላይ ርቀት የተገለጸበት አሐድ ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡ ይህም ማለት አንድ ኪሎ ሜትር ወደ ሴንቲ ሜትር ተለውጦ 100,000 ሴንቲ ሜትር ይሆናል ማለት ነው፡፡
2. የካርታ ላይ ርቀት በሴንቲ ሜትር ከተሰጠ የመሬት ላይ ርቀትም በተመሳሳይ አሐድ 100,000 ሴንቲ ሜትር ተብሎ ይሰጣል፡፡
3. ስለዚህ ወካይ መስፈርቱ

   1፡ 100,000 ወይንም $\frac{1}{100,000}$ ሲሆን አካፋዩ (100,000) የመሬት ላይ ርቀት ሲሆን የተሰጠውም የካርታ ርቀቱ በተሰጠበት በተመሳሳይ አሐድ ነው፡፡

## ◈ መስፈርቶችን መለዋወጥ

አንድን ዓይነት የመስፈርት መግለጫ ወደ ሌላ ዓይነት የመስፈርት መግለጫ መለወጥ ይቻላል፡፡ የሚከተለውን የአሠራር ደንብ ተከትሎ አንድን ዓይነት የመስፈርት መግለጫ ወደ ሌላ አይነት የመስፈርት መግለጫ መቀየር ይቻላል፡፡

### 1. ከወካይ መስፈርት ወደ ሐተታዊ መስፈርት መለወጥ

ወካይ መስፈርትን ወደ ሐተታዊ መስፈርት ለመለወጥ በመጀመሪያ አካፋዩን ለ100,000 ሴንቲ ሜትር አካፍሎ በ 1 ኪሎ ሜትር ማባዛት ያስፈልጋል፡፡

**ምሳሌ 1:** 1፡ 250,000

1 ሴንቲ ሜትር ለ $\frac{250,000 \text{ ሴንቲ ሜትር}}{100,000 \text{ ሴንቲ ሜትር}} \times$ በ1 ኪሎ ሜትር

ስለዚህ ሐተታዊ መስፈርቱ = 1 ሴንቲ ሜትር ለ2.5 ኪሎ ሜትር ይሆናል፡፡

### 2. ከሐተታዊ መስፈርት ወደ ወካይ መስፈርት መለወጥ

የተሰጠውን ሐተታዊ መስፈርት ወደ ወካይ መስፈርት ለመለወጥ የመሬት ላይ ርቀትን የሚያሳየውን ሁለተኛውን ቁጥር በ100,000 ሴንቲ ሜትር ማባዛትና ያለ አሐድ ማስቀመጥ ይሆናል፡፡

**ምሳሌ1:** መስፈርቱ 1 ሴንቲ ሜትር ለ 2 ኪሎ ሜትር ቢሆን 2 ኪሎ ሜትር ወደ ሴንቲ ሜትር ሲለወጥ = 2ኪሎ ሜትር × 100,000 ሴንቲ ሜትር = 200,000 ሴንቲ ሜትር ይሆናል

= ይህም 1 ሴንቲ ሜትር ለ 200,000 ሴንቲ ሜትር ይሆናል፡፡ መለኪያ አሐዶችን እርስ በእርስ ስናጣፋ ወካይ መስፈርቱ፡-

= 1፡ 200,000

**ምሳሌ 2:** 2½ ሴንቲ ሜትር ለ 2 ኪሎ ሜትር

= 2.5 ሴንቲ ሜትር ለ 2 ኪሎ ሜትር = 2 ኪሎ ሜትር × 100, 000 ሴንቲ ሜትር

= 200,000 ሴንቲ ሜትር

= 2.5 ሴንቲ ሜትር ለ 200,000 ሴንቲ ሜትር እርስ በእርስ ሲጣፋ ወካይ መስፈርቱ፡-

= 1፡ 80, 000 ይሆናል፡፡

### 3. ከወካይ መስፈርት ወደ ሥዕላዊ መስፈርት መለወጥ


በመጀመሪያ በቂ የሆነ ቀጥተኛ መስመር ይሰመርና ተመጣጣኝ ርቀት ባላቸው አሐዶች እኩል ይከፈላል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የ1 ሴንቲ ሜትር ርቀት ያላቸው ዋነኛውን ክፍልፋይ (Primary division) የሚያሳዩ ከዜሮ በስተቀኝና ክፍልፋዮችን የሚያሳይ አንድ አሐድ ከዜሮ በስተግራ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በኋላ የመሬት ላይ ርቀትን የሚያመለክቱ ቁጥሮች እያንዳንዱ ክፍልፋይ አናት ላይ መጻፍ ተገቢ ነው፡፡ የበለጠ ለመረዳት ምስል 2.16 ን መመልከት በቂ ይሆናል፡፡

ምሳሌ፡- - ወካይ መስፈርት 1፡100,000

- ሐተታዊ መስፈርት

$$= 1 \text{ ሴንቲ ሜትር ለ } \frac{100{,}000 \text{ ሴንቲ ሜትር}}{100{,}000 \text{ ሴንቲ ሜትር}} \times \text{በ1 ኪሎ ሜትር}$$

= 1 ሴንቲ ሜትር ለ 1 ኪሎ ሜትር





*ምሥል 2.16 ሥዕላዊ መስፈርት*

## ◈ ከካርታ ላይ የመሬት ርቀትን መለካት

የካርታ ርቀት የምንለው ካርታ ላይ በሚታዩ በሁለትና ከዚያ በሚበለጡ ነጥቦች መካከል ያለ ርቀት ሆኖ በመለካት የምንደርስበትና በሚሊ ሜትር ወይንም በሴንቲ ሜትር የምንገልፀው ርቀት ነው፡፡ ከተሰጠው መስፈርት ጋር በማገናዘብ የካርታ ርቀትን በምናሰላበት ወቅት ይህ ርቀት **የአግድም ርቀት** በመባል ይታወቃል፡፡ የሚገለጸውም በሜትር ወይንም በኪሎ ሜትር ይሆናል፡፡ ስለሆነም የአግድም ርቀት የሚታወቀው ቀጥታ መስመር ወይንም ጠመዝማዛ መስመርን በመለካት ሊሆን ይችላል፡፡

## ◈ የቀጥታ መስመር ርቀት አለካክ

በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ከተሞች ወይንም የእርሻ ማሳዎች መካከል ያለውን ርቀት የምንለካበት መንገድ ነው፡፡ መሬት ላይ የምናገኛቸው የመኖሪያ አካባቢዎች ካርታ ላይ በነጥብ ተወክለው ተራርቀው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ ምስል (2.17) ይኽንኑ ሁኔታ ያመለክተናል፡፡




*ምስል 2.17 የቀጥታ መስመር ርቀት አለካክ*

***የቀጥታ መስመር ርቀትን ከካርታ ላይ ለማስላት የሚከተለውን ቅደም ተከተሎች መከተል አለብን።***

ሀ) በከተማ "ሀ" እና በከተማ "ለ" መካከል ያለውን ርቀት በቀጥታ መስመር ማገናኘት

ለ) የተሰመረውን ርቀት ልኬት በማስመሪያ መለካት

ሐ) በልኬት የተገኘውን ርቀት ከተሰጠው መስፈርት ጋር ማገናዘብ።

መ) በስተመጨረሻ የቀጥታ መስመሩን ርቀት በመስፈርቱ መሠረት ማስላት ተገቢ ነው። ለምሳሌ ከላይ በተሰጠው ካርታ መሠረት፡- በከተማ "ሀ" እና ከተማ "ለ" መካከል ያለውን የቀጥታ መስመር ርቀት ስናሰላ፡-

- የተሰጠው መሥፈርት 1፡ 100,000
- በከተማ ሀ እና በከተማ ለ መካከል በልኬት የተገኘ የአግድመት ርቀት 4 ሴንቲ ሜትር ነው።
- 1ኪሎ ሜትር ማለት 100,000 ሴንቲ ሜትር በመሆኑ ካርታ ላይ የተሰጠው የአግድመት ርቀት መሬት ላይ ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚሆን ለማወቅ፡-

1 ሴንቲ ሜትር ለ 100,000 ሴንቲ ሜትር

4 ሴንቲ ሜትር = ?

$$= \frac{4 \text{ ሴንቲ ሜትር} \times 100{,}000 \text{ ሴንቲ ሜትር}}{1 \text{ ሴንቲ ሜትር}} = 400{,}000 \text{ ሴንቲ ሜትር}$$

$$= \frac{400{,}000}{100{,}000}$$ (ወደ ኪሎ ሜትር ለመለወጥ)

= ስለዚህም የአግድም ርቀቱ 4 ኪሎ ሜትር ይሆናል።

## ◈ የጠመዝማዛ መስመር ርቀት አለካክ

የጠመዝማዛ መስመር ርቀት በሁለት ነጥቦች መካከል በወንዝ፣ በመንገድ፣ በባቡር መስመር እና በጠረፍ ላይ ማግኘት ይቻላል። የጠመዝማዛ መስመር ርቀትን ለመፈለግ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፡-


- ካርታ መለኪያ (A map Measure)
- ማስመሪያ
- ዲቫይደርና ኮምፓስ
- ክርና ወረቀት ……ናቸው።

**የካርታ መለኪያ**

**የካርታ መለኪያ (plani meter) የጠመዝማዛ መስመር ርቀትን ለመለካት የሚያገለግል መሣሪያ ነው። ነገር ግን ዋጋው በጣም ውድ በመሆኑ በቀላሉ በሁሉም ትምህርት ቤቶች አይገኝም።**

ጠመዝማዛ መስመር ርቀትን ለማስላት ስንፈልግ የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች መከተል አለብን፡፡

- ጠመዝማዛውን መስመር ወደ ትናንሽ ቀጥ ያሉ መስመሮች መከፋፈል፡፡
- በወረቀት ወይንም በማከፋፈያ (divider) በመታገዝ የተለካውን ቀጥ ያለ ትናንሽ መስመር ርቀት በቅደም ተከተል ወረቀት ላይ ማስተላለፍ፡፡
- ወረቀት ላይ የተላለፉትን ትናንሽ ቀጥ ያሉ መስመሮች ርቀት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በቅደም ተከተል በአንድላይ መለካት፡፡ ይህ ርቀት ካርታ ላይ ጠመዝማዛውን መስመር ተከትሎ በሁለት ቦታዎች መካከል የሚታየውን ርቀት ይሰጠናል
- መከፋፈያ (divider) እና ኮምፓስ ባይኖሩን ክርና ወረቀት በመጠቀም ርቀቱን ማስላት ይቻላል፡፡




*ምስል 2.18 የጠመዝማዛ መስመር ርቀት አለካክ*

**ስሌት**

- የተሰጠው መስፈርት = 1:200,000
- ልኬት ከ "ሀ" እስከ "ለ" = 6.25 ሴንቲ ሜትር
- 1 ሴንቲ ሜትር ለ 200,00 ሴንቲ ሜትር

6.25 ሴንቲ ሜትር = ?

$$= \frac{6.25 \times 200{,}000}{100{,}000}$$

ስለዚህ በ "ሀ" እና በ "ለ" መካከል ያለው የመሬት ላይ ርቀት

12.5 ኪሎ ሜትር ይሆናል ማለት ነው፡፡

## ◈ መደበኛ (የተስተካከለ) ቅርጽ ያላቸው ቦታዎችን ስፋት መለካት

የመደበኛ (regular shape) ቅርጽ ያላቸውን ቦታዎች ስፋት ለማስላትና ለማወቅ በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ የሠፈረውን ቀመር (Formula) ጠንቅቆ ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል፡፡


**ሠንጠረዥ 2.1**

| መደበኛ ቅርጽ | የስፋት ቀመር (formula) |
|---|---|
| ካሬ (Square) | ርዝመት × ርዝመት (Side Square) ወይንም ር$^2$ |
| ቀጤ ጎነ አራት (Rectangle) | ርዝመት × ወርድ |
| ማዕዘናዊ ጎነ ሦስት (Triangel) | ½ × ቁ × መ |
| ክብ | $\pi r^2$ |

## ◈ የካሬ (Square) ቅርጽ ያለው የመሬት ስፋት


ስፋት = ርዝመት$^2$ (ለሁሉም ምስሎች ቀመሩን በመጠቀም ርዝመታቸውን ወደ ኪሎ ሜትር መቀየር ይቻላል::

ስፋት = ር × ር ወይንም ር$^2$




ምስል 2.19 ካሬ

## ◈ ጎነ ሦስት ማዕዘን (Triangle) ቅርጽ ያለው የመሬት ስፋት




| ማዕዘናዊ ጎነ ሦስት (Right Angled Triangel) | ባለ ዝርጥ ጎነ ሦስት አንገል (Obtuse Angled Triangel) | ባለ ሹል አንገል ጎነ ሦስት (Acute angle Triangle) |
|---|---|---|
| አንግል = 90° | አንዱ አንግል= ከ90$^0$ ይበልጣል | ሁሉም አንግሎች ከ90$^0$ ያንሳሉ:: |


ምስል 2.20 ጎነ ሦስት

ር = ርዝመት

ቁ = ቁመት

ስፋት = $^1/_2$ × ር × ቁ

## ◈ ቀጤ ጎነ አራት (Rectangle) ቅርጽ ያለው የመሬት ስፋት





ስፋት = ርዝመት × ወርድ

(height) × (Width)

ምስል 2.21 ቀጤ ጎነ አራት

ክብ ቅርጽ ያለው የመሬት ስፋት




ምስል 2.22 ቅርጽ ክብ

የ "ሀ" ስፋት $= \pi ሬ^2$

የ "ለ" ስፋት $= \frac{1}{2}\pi ሬ^2$

የ "ሐ" ስፋት $= \frac{\pi ሬ^2}{4}$

የ "መ" ስፋት $= \frac{1}{5}$ ማለትም $= \frac{72^0}{360^0} = \frac{\pi ሬ^2}{5}$

## የተግባር ክንውን

1. የአንድ ትምህርት ቤት የእግር ኳስ ሜዳ ካርታ ላይ 10 ሴንቲ ሜትር ርዝመትና የ 5 ሴንቲ ሜትር ወርድ አለው፡፡ የካርታው መስፈርት ደግሞ 1፡200,000 ነው፡፡ የኳስ ሜዳውን አጠቃላይ ስፋት ፈልጉ፡፡
2. አንድ የፍራፍሬ እርሻ ካርታ ላይ 5 ሴንቲ ሜትር ርዝመት በአራቱም ጐኖች በኩል አለው፡፡ የካርታው መስፈርት ደግሞ 1፡100,000 ቢሆን የእርሻ ቦታውን ስፋት አስሉ፡፡
3. አዲስ አበባ አካባቢ አንድ ክብ ሐይቅ አለ ብለን እናስብ፡፡ የክቡ አጋማሽ ርዝመት (radius) 10 ሴንቲ ሜትር ቢሆንና የካርታው መስፈርት 1፡50,000 እንደሆነ ቢገመት የሐይቁ ስፋት ስንት ነው?
4. አንድ የመኪና ማቆሚያ ቦታ የራይት አንግል ቅርጽ አለው፡፡ በዚህ መሠረት ራይት አንግል ትሪያንግል ቅርጽ ያለው የመኪና ማቆሚያ ርዝመቱ 6 ሴንቲ ሜትር ቁመቱ 10 ሴንቲ ሜትር ቢሆንና የካርታው መስፈርት ደግሞ 1፡25,000 ቢሆን የመኪና ማቆሚያ ቦታው ስፋት ምን ያህል ይሆናል?

## የተግባር ክንውን

### የካርታ መስፈርቶችን ማነጻጸር

ካርታዎች ብዙውን ጊዜ ባለ ትልቅ፣ ባለ መካከለኛ እና ባለ ትንሽ መስፈርት ተብለው በሦስት ይከፈላሉ፡፡ የአንድ ካርታ መስፈርት ባነሰ ቁጥር የሚያሳየው ዝርዝር መረጃም አነስተኛ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የሚቀርበው መረጃ በጣም ጥቅልና ውስን (generalized) ይሆናል፡፡ የአንድ ካርታ መስፈርት ከፍ ባለ መጠን የሚያሳየው ዝርዝር መረጃም ሰፊ ጉዳዮችን ይዳስሳል፡፡ መረጃው በጣም የተጠቃለለ ሳይሆን እያንዳንዱን ጉዳይ በግልጽ ያሳያል፡፡

ለምሳሌ የአዲስ አበባ መልክአምድራዊ ገጽታ በባለ ትልቅ መስፈርት ካርታ የኢትዮጵያ መልክአምድራዊ ገጽታ ደግሞ በባለ ትንሽ መስፈርት ካርታ ተሠርተው ቢቀርቡ በአዲስ አበባ ላይ የሚገኙት ነገሮች መንገዶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ አብያተክርስቲያን፣ መስጊዶች፣ ኳስ ሜዳዎች፣ ሌሎች ገጽታዎች በግልጽ ይታያሉ፡፡ ነገር ግን አዲስ አበባን በኢትዮጵያ ካርታ ላይ የምናገኛት በአነስተኛ የነጥብ ምልክት ተወክላ ነው፡፡ ስለዚህም የኢትዮጵያ ካርታ ከላይ የተገለፁለትን ዝርዝር ነገሮች ማሳየት አይችልም፡፡ በባለ ትልቅ መስፈርት ካርታ እና በባለ ትንሽ መስፈርት ካርታ መካከል ያሉት ካርታዎች በሙሉ ባለ መካከለኛ መስፈርት ካርታዎች ይባላሉ፡፡

**የካርታ ዓይነቶች**

**ባለ ትልቅ መስፈርት ካርታ፡-** መስፈርታቸው ከ 1፡50,000 በላይ ያሉ ካርታዎችን ይገልጻል፡፡

**ባለ መሐከለኛ መስፈርት ካርታ፡-** መስፈርታቸው ከ1፡50,000 — 1፡250,000 የሚደርሱ ካርታዎችን ያካትታል፡፡

**ባለ ትንሽ መስፈርት ካርታ፡-** መስፈርታቸው ከ 1፡250,000 በታች የሆኑ ካርታዎችን ይይዛል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች 2.3

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች፡-***

- የመስፈርትን ትርጉም ስጡ፡፡
- የመስፈርት መግለጫ መንገዶችን ዘርዝሩ፡፡
- የቀጥታ መስመር ርቀትን ስንፈልግ የምንከተላቸው ቅደም ተከተሎችን በዝርዝር አስቀምጡ፡፡
- የአንድ አነስተኛ ስፋት ያለውን የመሬት ገጽታ ይዘቶች የምናሳይበት ካርታ (ከመስፈርት አኳያ) የትኛው ዓይነት ካርታ ነው?
- ከካርታ ላይ የአንድን የተስተካከለ ቅርጽ ያለውን ቦታ ስፋት ስናሰላ በዋነኛነት ልንመለከታቸው የሚገቡ ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡
- የትምህርት ቤታችሁን የስፓርት ሜዳ በካርታ ላይ ለማሳየት የምትጠቀሙበትን መስፈርት ወስኑ፡፡ ይህን መስፈርት የመረጣችሁበትን ምክንያት አስረዱ፡፡

***ለ. የቡድን ሥራ***

- የተለያዩ ነገሮችን ካርታ ላይ ለማሳየት ሲፈለግ የተለያዩ መስፈርቶችን መጠቀም አስፈላጊ የሚሆነው ለምን እንደሆነ ተወያዩ፡፡

## ቁልፍ ቃላት

- **ሐተታዊ መስፈርት፡-** በካርታና በመሬት መካከል ያለ ርቀት በቃላት አማካኝነት የሚገለጽበት መስፈርት
- **ሜካኒካዊ ፍርፈራ፡-** ማለት አለቶች ተፈጥሮአዊ ይዘታቸው ሳይለወጥ ወደ ደቃቅ አካልነት የመቀየር እንቅስቃሴ ነው፡፡
- **ንቅ ገሞራ፡-** በየጊዜው የሚፈነዳ፣ በመፈንዳት ላይ ያለ የገሞራ ዓይነት
- **ክምችት፡-** በየዘመኑ ከከፍተኛ ቦታ በወራጅ ውኃ እየታጠበ ወደ ዝቅተኛ ቦታ በመምጣት የተለያዩ ንጣፎችን የሚሠራ የደለል ክምር
- **ዝንፈት፡-** ንጥነጣዊ እንቅስቃሴ በሚፈጥረው ግፊት የተነሣ አለቶች ከተለያዩ አቅጣጫ ወደ አንድ አቅጣጫ ሲገፉ አንዱ በሌላው ላይ ሲጫን ወይም አንዱ ከሌላው ሥር ገብቶ ሲገኝ፣ አንዳንዴም አለቶች በሌላ አለቶች ላይ ወደ ጎን ሲንሸራተቱ እንቅስቃሴው ዝንፈት ይባላል፡፡
- **የሬክተር መስፈርት (Seismograph) ፡-** የርዕደ ምድር መጠንን (ኃይልን) ለመለካት የሚያገለግል መሣሪያ ነው፡፡
- **ደለል፡-** በወራጅ ውኃ ከከፍተኛ ቦታ ታጥቦ የመጣና በዝቅተኛ አካባቢዎች የተከማች አፈር
- **ገሞራ ህጽም፡-** በመሬት ውስጥ ያለ የቀለጠ አለት
- **ገሞራ ትፍ፡-** ወደ መሬት ገጽ ሽቅብ ተወርውሮ የሚወጣ የቀለጠ ድንጋይና አመድ ወዘተ
- **ገሞራዊነት፡-** የቀለጠ አለት እየገነፈለ ወደ መሬት ገጽ መውጣት

## ማጠቃለያ

- የመሬትን ገጽ የሚለውጡ ውጪያዊ ኃይሎች የሚባሉት ወይንም በሰዎች አኗኗር ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ኃይሎች ወራጅ ውኃ፣ የንፋስ ኃይል፣ የበረዶ ሸርሸራና የባሕር ሞገድ ናቸው፡፡
- በመሸርሸርና በእጥበት የመሬትን ከፍታ የመቀነስ ሂደት ግጥግጦሽ (degradation) ይባላል፡፡
- በጊዜ ሂደት አለቶችን በመሰባበር ወደ ደቃቅ አካልነት የመቀየር እንቅስቃሴ ደግሞ ፍርፈራ ተብሎ ይጠራል፡፡
- ስርግርጌ (Stalactite) ከዋሻ ጣሪያ ላይ ቁልቁል የሚንጠለጠል የኖራ ድንጋይ ነው፡፡ ከዋሻ ወለል ወደ ላይ እየተቆለለ የሚሄድ የኖራ ድንጋይ ደግሞ ጉልት ካልሲት (Stalagmite) ይባላል፡፡ ስርግርጌና ጉሊት ካልሲት ሲገናኝ የሚፈጠረው የኖራ ድንጋይ ምሰሶ ዓምድ ይባላል፡፡
- በወራጅ ውኃ ወይንም በንፋስ ወይንም በውቅያኖስ ሞገድ እና በሚንቀሳቀስ በረዶ አማካይነት የተሰባበሩ አለቶች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ታጥበው ሲወሰዱ ሸርሸራ (Erosion) ይባላል፡፡
- ስብርባሪ አለቶች በወራጅ ውኃ፣ በተንቀሳቃሽ በረዶ፣ በውቅያኖስ ሞገድ፣ በንፋስ ኃይል ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ታጥበው በመወሰድ በአዲስ ቦታ ላይ ሲከማቹ ክምችት (Deposition) ይባላል፡፡
- የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ቅልብሽ፤ የመሬት መሰንጠቅ የመሳሰሉት የመሬት አባጣና ጎርባጣ ገጽታ የሚፈጥሩ ውስጣዊ የመሬት ገጽ ለዋጭ ኃይሎች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ።**

1. በምድረበዳ ዋነኛው የሸርሸራ ኃይል ውሃ ነው።
2. አርታሌ የሚገኘው በአፋር ብሔራዊ ክልል ውስጥ ነው።
3. ገሞራ ህጽም በመሬት ገጽ ላይ የሚፈስ ቅልጥ አለት ነው።
4. የደለል ክምችት (Deposition) ለጐርፍ መፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል።
5. ቅልብሽና ዝንፈት ውስጣዊ የመሬት ገጽ ለዋጭ ኃይሎች ናቸው።

**ለ. አዛምዱ**

***በ "ሀ" ረድፍ የተዘረዘሩትን ቃላት በ "ለ" ሥር ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ወይም ሐረጋት ጋር አዛምዱ።***

| "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|
| 1. ስርግርጌ | ሀ) | የተቆለሉ የኖራ ድንጋይ አካላት |
| 2. ሰተቶ ደለል | ለ) | በነፋስ ክምችት የሚፈጠር |
| 3. ቅልብሽ | ሐ) | የማዕከለ መሬት ቅልጠተ አለት ተገፍትሮ መውጣት |
| 4. ገሞራ ህጽም | መ) | በሁለት ስፍሃኖች ግጭት የሚፈጠር |
| 5. ገሞራዊነት | ሠ) | በዋሻ ጣራ ላይ የሚንጠለጠሉ የኖራ ድንጋይ አካላት |
| . | ረ) | በከርሠ ምድር ያለ የቀለጠ አለት |
| | ሰ) | ሰፍሃኖች (Plates) |
| | ሸ) | በወራጅ ውኃ ክምችት የሚፈጠር |
| | ቀ) | ወደ ገጸ ምድር የወጣ የቀለጠ አለት |

**ሐ. ምርጫ**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ መርጣችሁ ጻፉ።***

1. ከሚከተሉት ጥንዶች አንዱ አኅጉራትን አያመለክትም።
   - ሀ) አውሮፓና እስያ
   - ሐ) አውስትራሊያ እና አንታርክቲክ
   - ለ) የአትላንቲክና የሕንድ ውቅያኖስ
   - መ) ሰሜን አሜሪካና ደቡብ አሜሪካ

2. ከሚከተሉት አንዱ አብሮ አይሔድም።
   - ሀ) ውጨያዊ ኃይሎች - የመሬት ገጽ ለዋጮች
   - ለ) ወካይ መስፈርት - በስፋት የተለመደ
   - ሐ) ቅልብሽ - ምቅማጥ ተራራ
   - መ) ውስጣዊ ኃይሎች - የመሬት ገጽ ገንቢዎች እና አፍራሾች

3. ከሚከተሉት አንዱ ባለ ትንሽ መስፈርት ካርታ አይደለም
   - ሀ) 1፡250,000
   - ሐ) 1፡300,000
   - ለ) 1፡500,000
   - መ) 1፡50,000
4. በሁለት ነጥቦች መሐከል ያለው የካርታ ላይ ርቀት 4 ሴንቲ ሜትር ነው። የካርታው መስፈርት 1፡200,000 ቢሆን የመሬት ርቀት ምን ያህል ይሆናል?
   - ሀ) 6 ኪሎ ሜትር
   - ሐ) 8 ኪሎ ሜትር
   - ለ) 4 ኪሎ ሜትር
   - መ) 10 ኪሎ ሜትር

### መ. ባዶ ቦታ ሙሉ፡፡

***የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በተስማሚ ቃል ወይም ሐረግ ሙሉ።***

1. 1፡400,000 ወደ ሐተታዊ መስፈርት ሲቀየር ______________ ይሆናል።
2. ለአርታሌ መፈጠር ምክንያት የሆነው _________________ ነው።
3. ሰሜን አሜሪካንን በስተ ምዕራብ __________ በስተ ምሥራቅ ___________ ያዋስኗታል።

### ሠ. የአጭር መልስ ጥያቄዎች

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።***

1. በሽርሽራና በፍርፈራ አማካይነት የመሬት ወለል ከፍታ ዝቅ የሚልበት ሂደት ምን ይባላል?
2. በፍሰተ ገጽ (running Water) ምክንያት የሚፈጠሩ የሽርሽራ ዓይነቶችን ዘርዝሩ።
3. በካርታ ላይ በጣም ሰፊ አካባቢን ለማሳየት የሚያስችለው የትኛው የመስፈርት ዓይነት ነው?
4. በተደጋጋሚ ለጐርፍ አደጋ የሚጋለጡ ሀገራትን ዘርዝሩ።

**ፍተሻ**

*ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሣጥኖቹ ውስጥ በማኖር አመልክቱ፡፡*

1. የመሬት ገጽታ የሚለውጡ ውጫዊ ኃይሎችን እገልጻለሁ፡፡ ☐
2. ሸርሸራና ደለል በመሬት ገጽ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ እለያለሁ፡፡ ☐
3. የመሬትን ገጽታ የሚለውጡ ውስጣዊ ኃይሎችን እገልጻለሁ፡፡ ☐
4. የመሬት ገጽታ የሚለውጡ የውስጣዊ ኃይሎች በመሬት ገጽ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ አስረዳለሁ፡፡ ☐
5. የካርታ መስፈርት ምን ማለት እንደሆነ አስረዳለሁ፡፡ ☐
6. ሊንየር (መስመራዊ) መስፈርት የሚገለጽባቸውን የተለያዩ መንገዶች ስም እዘረዝራለሁ፡፡ ☐
7. የካርታ መስፈርትን ከአንዱ ወደ ሌላው መስፈርት መለወጥ እችላለሁ፡፡ ☐
8. ከካርታ ላይ ርቀትና ስፋትን አሰላለሁ፡፡ ☐

# ምዕራፍ ሦስት

# ሥርዓተ ምኅዳርና የሰው ልጅ ጣልቃ ገብነት

***ከምዕራፉ የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት***

**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-**

- የተፈጥሮ ሀብት ውድመት መንሥኤዎችንና ውድመቱ የሚያስከትለውን ጉዳት ትገልጻላችሁ።
- ዋና ዋና በካዮችንና የመከላከያ ተግባራትን ትለያላችሁ።
- ለዓለም የሙቀት መጠን መጨመር አስተዋጽ ሚያደርጉ ምክንያቶችንና የሚያስከትሉትን ጉዳት ትገልጻላችሁ።

## 3.1 የሰውና የተፈጥሮ ሀብት ግንኙነት

***ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት***

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኂላ:-**

- የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመንና በሥርዓተ ምኅዳር ላይ የሚያስከትሉትን ጉዳት ትተነትናላችሁ።
- የተፈጥሮ ሀብቶችን በመንከባከብ ረገድ የበኩላችሁን አስተዋፅኦ ታደርጋላችሁ።
- ዐበይት የአየርና የውኃ በካዮችን ትጠቅሳላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

- ሥርዓተ ምኅዳር
- ብክለት
- በረሃማነት

## ◈ የተፈጥሮ ሀብቶች በሁለት ዋነኛ ክፍሎች ይመደባሉ::

- **ዘላቂ ወይም ታዳሽ (Renewable resources) የተፈጥሮ ሀብቶች፡-** የዚህ ዓይነት የተፈጥሮ ሀብቶች የሚባሉት ጥቅም ላይ እየዋሉ ራሳቸውን በማደስ ዘለቄታዊ አገልግሎት የሚሰጡ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው። የእነዚህ ዓይነት የተፈጥሮ ሀብቶች ጥሩ ምሳሌዎች ውሃ፣ አየር፣ እጽዋት፣ የተፈጥሮ የግጦሽ ቦታዎች የመሳሰሉት ናቸው።
- **አላቂ ወይም ታዳሽ ያልሆኑ (Non-renewable resources) የተፈጥሮ ሀብቶች** የሚባሉት ደግሞ ለመከማቸት ብዙ ዘመናት የሚወስድባቸው ነገር ግን አንዴ ጥቅም ላይ ከዋሉ ተመልሰው የማይገኙ ወይም ራሳቸውን የማያድሱ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው። የነዚህ ዓይነት የተፈጥሮ ሀብቶች ዋና ዋና ምሳሌዎች ነዳጅ ዘይት (petroleum)፣ የድንጋይ ከሰል፣ የተፈጥሮ ጋዝ፣ ማዕድናት የመሳሰሉት ናቸው።

## ◈ የተፈጥሮ ሀብት ውድመትና በሥርዓተምኅዳር ላይ ያለው ተጽእኖ

- **ሥርዓተ ምኅዳር ማለት ምን ማለት ነው?**
- **በሥርዓተ - ምኅዳር (Ecosystem) እና በአካባቢ (Environment) መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**
- **የተፈጥሮ ሀብት ውድመት በሥርዓተ ምኅዳር ላይ የሚያደርሰው ጥፋት ምንድን ነው?**
- **በሥርዓተ ምኅዳር አካላት (Elements) መካከል ያለው መስተጋብር ምንድን ነው?**

ሥርዓተ-ምኅዳር በአንድ ተፈጥሮአዊ አካባቢ እጽዋት፣ እንስሳት፣ ሌሎችም ሕይወት ያላቸውና ሕይወት የሌላቸው ነገሮች የሕይወት ዑደት ተሳስሮ የሚገኝበት ተፈጥሮአዊ ሥርዓት ነው።

የሥርዓተ-ምኅዳር አካላት ከፍተኛ መደጋገፍ ወይም ቁርኝት አላቸው። ለምሳሌ እጽዋት በአግባቡ የሚያድጉት ለም አፈር ሲኖር ነው። የእጽዋት ቅጠል ሲረግፍ መሬት ላይ ወድቆ በመበስበስ የአፈሩን ለምነት ይጨምራል። እንስሳት ለሕይወታቸው መቀጠል እጽዋት ያስፈልጓቸዋል። የእንስሳት ቅሪት አካላት ደግሞ ለአፈር ለምነት በእጅጉ አስፈላጊ ናቸው። የሥጋ-በል እንስሳት ሕልውና የተመሠረተው በቅጠልና ሣር-በል በሆኑ እንስሳት ሕልውና ላይ ነው። ሣር በልና ሥጋ በል እንስሳት ሕልውናቸው የተመሠረተው በአካባቢው በሚገኙ እጽዋትና እንስሳት ላይ ነው። ስለዚህ በአንድ ሥርዓተ-ምኅዳር ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ አካላት (Elements) መካከል ከፍተኛ የመደጋገፍና የቁርኝት ሥርዓት በመኖሩ የአንዱ ሕልውና ወይንም ጉዳት በሌላው ላይ ቀጥተኛ ወይንም ቀጥተኛ ያልሆነ ተጽእኖ ያስከትላል። በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን በተለያዩ ምክንያት እጽዋት እየወደሙና እየተጨፈጨፉ ይገኛሉ። ማዕድናት በብዛት ይወጣሉ። መሬትም በከፍተኛ ደረጃ ይታረሳል። ውኃም ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላል። የሰው ልጅ ፍላጎትና የአኗኗር ዘይቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠና እያደገ በመምጣቱ በሥነምኅዳር ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ እየፈጠረ ነው።

- **የተፈጥሮ ሀብት ውድመት በሥርዓተ ምኅዳር ላይ ያለው ተጽእኖ ምንድነው?**

የአንድ የተፈጥሮ ሀብት ውድመት በሌላኛው የተፈጥሮ ሀብት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ወይንም ጉዳት ያስከትላል። ምክንያቱም በአንድ የተፈጥሮ አካባቢ የሚገኙ ልዩ ልዩ አካላት (elements) እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው የሚኖሩ በመሆናቸው የአንዳቸው ሕልውና በሌላኛው ሕልውና ላይ የተመሠረተ ነው። ለምሳሌ በደን ጭፍጨፋ የተነሳ በአንድ አካባቢ ያለ የደን ሽፋን በፍጥነት እየተመናመነ ሲሄድ መሬቱ ለአፈር መከላት ይጋለጣል። ይህ ደግሞ በተራው የአፈር ለምነት ማጣትን ስለሚያስከትል የምግብ እጥረትን፣ የንጹሕ የመጠጥ ውኃ አለመገኘትን፣ የከርሠ ምድር ውኃ ክምችት መጠን መቀነስን፣ የዱር እንስሳት መጥፋትን፣ የአካባቢ የአየር ለውጥ ማለትም የዓለም ሙቀት መጨመርን፣ በረሃማነትን፣ የአሲድ ዝናብ መከሰትን፣ የጐርፍ መጥለቅለቅን፣ ድርቅና ረሃብን፣ የብዝኃ ሕይወት መመናመንንና መጥፋትን ያስከትላል።

## ውስን ጥናት

### የሐሩር ዝናባማ ደን ውድመትና የእርሻ ሥራ

በሐሩር ዝናባማ ደን አካባቢ የሚገኝ አፈር ቀለሙ በደማቅ ቀይና ቢጫ መካከል የሚቀያየር ነው። ደማቅ ቀይ ቀለም ያለው አፈር የሚገኘው በደን በተሸፈነ አካባቢ ሲሆን ከፍተኛ የብረት ክምችት ያለው አፈር ነው። በደን በተሸፈነው አካባቢ በአፈሩ የላይኛው ክፍል (top soil) ላይ ለተክሎች ዕድገት አስፈላጊና ጠቃሚ ብስባሽ (humus) ይገኛል። የደን ሽፋኑ ሲመነጠር የብስባሽ መጠኑ ይቋረጥና አፈሩ ለምነቱን ያጣል። በእርጥበት ወቅት በአፈሩ ውስጥ የሚገኙ የጨው ማዕድናት ይታጠባሉ። ስለዚህም የአፈሩ የላይኛው ክፍል (upper horizon) የፓታሽ፣ የናይትሮጂንና የፎስፈረስ እጥረት ያጋጥመዋል። በአፈር ውስጥ በቀላሉ የማይሟሙት የብረትና አሉሚንየም ማዕድናት ብቻ ይቀራሉ። ይህ ዓይነቱ አፈር ጠፍ (sterile) ነው።

## ውስን ጥናት

### የግጦሽ ቦታን ከአቅም በላይ መጠቀም፣ ሸርሸራና በረሃማነት

አንድ የግጦሽ ቦታ በርካታ እንስሳት ተሠማርተውበት ከመጠን በላይ ከተጋጠ (Overgrazed) በቀላሉ ለሸርሸራ ይጋለጣል። የእርሻ ሥራ በተስፋፋ መጠን የግጦሽ ቦታውን እያሳነሰ ይመጣል። በአፍሪካ ጥብቅ ያልሆነ (uncontrolled grazing) የግጦሽ ቦታ አጠቃቀም የተለመደ የአኗኗር ሥርዓት ነው። ለምሳሌ የኬንያ አርብቶ አደሮች ማለትም ጋብራዎች፣ ቦረናዎች፣ ቱርካናዎች እና መሳዮች “የቀድሞ የግጦሽ ግዛታቸው” በመንግሥት በመወሰዱ ምክንያት በውስን የግጦሽ ቦታ ብዛት ያላቸውን የቀንድ ከብቶች ለግጦሽ በማሰማራታቸው አካባቢው በከፍተኛ ደረጃ ለሸርሸራ ተጋልጧል። ስለዚህ የተሻለ የግጦሽ ቦታና ውኃ ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳንና ታንዛንያ ይሰደዳሉ። ለኬንያ አርብቶ አደሮች ድንበርና ግዛት የሚባሉት ጉዳዮች ብዙ ትርጉም አይሰጣቸውም።

- በረሃማነት ምንድነው?

የሰው ልጅ ለኑሮው በሚያደርገው እንቅስቃሴ ሸርሸራን እያበረታታ በአንድ ወቅት ምርታማ የነበረ መሬት ወደ መካን መሬትነት የመለወጥና በጣም ኃይለኛ ሙቀት የበዛበት አካባቢ የመፈጠር ሂደት በረሃማነት ይባላል።

- ስበረሃማነት መስፋፋት ዋና ዋና ምክንያቶች ምንድናቸው?

የሚከተሉት ምክንያቶች ለበረሃማነት መስፋፋት መነሻ ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

- የሕዝብ ብዛት፡- የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት እየጨመረ መሄድ በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ጉልህ ተጽእኖ በማሳደር ለአካባቢ መጎሳቆልና ለበረሃማነት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡
- የግጦሽ ቦታን መሸከም ከሚችለው በላይ ከብቶች እንዲሠማሩበት ማድረግ አካባቢው በተገቢው ጊዜ የግጦሽ ሣር እንዳያበቅልና አካባቢው እንዲጎሳቆል ያደርጋል፡፡
- ለማገዶ፣ የእርሻ ቦታ ማስፋፊያ፣ ለጣውላ ሥራ፣ ለቤትና ለአጥር ግንባታ ሲባል ደንን መመንጠር ለበረሃማነት መፈጠር ዋና ምክንያት ነው፡፡
- የተዛባ የአስተራረስ ዘዴዎችና የደን ቃጠሎ አካባቢ እንዲጎዳና ወደ በረሃማነት እንዲቀየር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡



*ምስል 3.1 የማሳይ አርብቶ አደሮች*

## ◈ የአየርና የውኃ ብክለትና መከላከያ ዘዴዎች

### የአየር ብክለት

አየር በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ በሆኑ ምክንያቶች ይበከላል፡፡ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ የሚተፋው አመድና ጭስ አየርን የመበከል አቅም አለው፡፡ የሰው ልጅ በተለያየ ምክንያት በተፈጥሮ ደን ላይ እሳት ይለቃል፡፡ በድንገት የሚነሣ ሰደድ እሳት በደን ሀብትና በሌሎች ንብረቶች ላይ ከፍተኛ ጥፋት ከማድረሱም በላይ ጭሱም የአካባቢውን አየር ይበክላል፡፡ በንፋስ ኃይል የሚፈጠረው አቧራም ለአየር ብክለት ምንጭ ነው፡፡

ከባቢ አየር ከመሬት የሚወጡ የተለያዩ ንጥረ ነገሮችን (chemicals) ይይዛል፡፡ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቱን ለሟሟላት፣ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ፣ የተለያዩ ምርቶችን ለማምረት የተለያዩ ማዕድናትን ይጠቀማል፡፡ ብናኝ፣ ጭስና ሌሎች አካላትን በቀጥታ ወደ ከባቢ አየር በመልቀቅ የአየር ብክለትን ያስከትላል፡፡ እነዚህ ቅንጣቶችም (particles) አየር በካዮች ይባላሉ፡፡

የአየር ብክለት ምክንያቶችን በሁለት ክፍል መመደብ ይቻላል። እነርሱም

- የመጀመሪያ ደረጃ በካዮች እና
- የሁለተኛ ደረጃ በካዮች ናቸው

- **የመጀመሪያ ደረጃ በካዮች** የሚባሉት በቀጥታ ወደ ከባቢ አየር ገብተው የአየሩን ተፈጥሮአዊ የጥራት ደረጃ የሚቀንሱ በካዮች ናቸው። እነዚህ በካዮች በተፈጥሮ ወይም ሰው ሠራሽ በሆነ ምክንያት ሊፈጠሩ ይችላሉ። ለምሳሌ በነዳጅ ኃይል ከሚንቀሳቀሱ መኪናዎች፣ ከፋብሪካዎች፣ ከማዕድን ማውጫ ቦታዎች፣ ከደን ቃጠሎ፣ ከእሳተ - ገሞራ ፍንዳታ በመውጣት ወደ ከባቢ አየር የሚገቡ ብናኞች የመጀመሪያ ደረጃ በካዮች ናቸው።

  የሚከተሉት ከመጀመሪያ ደረጃ በካዮች ጥቂቶቹ ናቸው። እነርሱም፡-
  - ካርቦንዳይ ኦክሳይድ
  - ሰልፈር-ኦክሳይድ
  - ናይትሬት-ኦክሳይድ
  - አቧራ ናቸው።
- **ሁለተኛ ደረጃ በካዮች** የሚፈጠሩት ንጥረ - ነገሮች ሲደባለቁ ነው። ለምሳሌ ሰልፈርዳይ ኦክሳይድ ከኦክሲጅን ጋር ሲደባለቅ ሰልፈር ትራይኦክሳይድ ይሆናል።

| ሰልፈር ዳይኦክሳይድ + ኦክሲጅን = ሰልፈር - ትራይኦክሳይድ |
|---|

ሰልፈር - ትራይኦክሳይድ ጋዝ ከእንፋሎት (ትነት) (water vapor) ጋር ከባቢ አየር ውስጥ ሲደባለቅ ሰልፈሪክ አሲድ ይፈጥራል።

| ሰልፈር - ትራይኦክሳይድ + እንፋሎት = ሰልፈሪክ አሲድ |
|---|

ሰልፈር - ዳይኦክሳይድ በቀላሉ መተንፈስ አያስችልም። ብርሃን የሚሸፍን ቀለል ያለ ደመና ወይም ጭጋግ (Smog) የሚፈጠረው በካይ ንጥረ - ነገሮች ከፀሐይ ጋር ባላቸው መስተጋብር የተነሣ ነው።

| አቧራ እና ጭስ + ደመና + የፀሐይ ብርሃን = ጭጋግ (Smog) |
|---|

የአየር ብክለት የሚከተሉትን ችግሮች ያስከትላል።

- የሰውና የእንስሳትን ጤንነት ይጐዳል።
- የእፅዋትንም እድገት ይገታል።
- በከተማዎች አካባቢ የአየር ንብረት ለውጥ ያስከትላል።
- የአሲድ ዝናብ እንዲፈጠር ያደርጋል።
- የጕርፍ መጥለቅለቅ አደጋን ያመጣል።
- የከባቢ - አየር ሙቀት እንዲጨምር ያደርጋል።

ከፋብሪካዎችና ከተለያዩ መጓጓዣዎች የሚወጣ ጭስ በብዛት መኖር፣ የካርቦንዳይኦክሳይድ ልቀት እና ከተለያዩ ምንጮች የሚፈጠረው ካርቦንሞኖክሳይድ የከተማዎችን ሙቀት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ በከተማዎች አካባቢ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ከሰል፣ ፔትሮልየምና የተፈጥሮ ጋዝ ኃይል ለማመንጨት ጥቅም ላይ ይወላሉ፡፡ የኃይል ምንጮች ሲቃጠሉ የሚወጣው ጭስ ሰልፈር - ዳይኦክሳይድ አለው፡፡ ሰልፈር - ዳይኦክሳይድ ደግሞ ትነት ጋር ሲደባለቅ ሰልፈሪክ - አሲድ እና ናይትሪክ - አሲድ ይፈጥራል፡፡ አሲዶቹ በተራቸው የአሲድ ዝናብ እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡

- **የአየርን ብክለት መከላከያ ዘዴዎች**

አየርን ከብክለት ለመከላከል የሚከተሉትን ዘዴዎች መተግበሩ ጠቃሚ ነው፡፡

- መንግሥት በዕድገት መርሐግብሩ ለአካባቢ ጥበቃ ቅድሚያ በመስጠት በጀት መድቦ አፈጻጸሙን መከታተልና መቆጣጠር አለበት፡፡
- የበለፀጉ ሀገሮች ከፋብሪካዎቻቸው የሚወጡትን በካይ ኬሚካሎች መጠን ለመቀነስ፣ ለኃይል ማመንጫ ከሚጠቀሙባቸው የኒኩለር ጣቢያዎች ሾልከው የሚወጡትን ንጥረ ነገሮች ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- ከሰል፣ ፔትሮልየምና ጋዝ ከመጠቀም ይልቅ ጭስ - አልባ የኃይል ምንጮችን መጠቀም በስፋት ሊጠናከርና ሊበረታታ ይገባል፡፡
- የግል መጓጓዣ (transport) ከመጠቀም ይልቅ የሕዝብ መጓጓዣዎችን በስፋት መጠቀም
- በከተማዎች የሚታየውን የህዝብ መተፋፈግ ለመቀነስ የቤተሰብ ምጣኔ ፕሮግራም አገልግሎትን ማስፋፋት፡፡
- ደኖችን መንከባከብና የእሳት አደጋ መከላከያ ዘዴዎችን በተመለከተ የሕዝቡን ግንዛቤ ማሳደግ
- ቆሻሻን በየቦታው እየጣሉ አካባቢን ከመበከል መቆጠብ፡፡
- የአየር ብክለት መንስኤና መከላከያ ዘዴዎችን በተመለከተ ኅብረተሰቡን ማስተማር ናቸው፡፡

**ውስን ጥናት**

**የአየር ብክለት በሕንድ**

በሕንድ አየር ብክለት ያለው በአብዛኛው በከተማዎች አካባቢ ነው፡፡ ይኸም የሚሆነው በከተማዎች አካባቢ ብዙ የቤት አውቶሞቢሎች፣ ኢንዱስትሪዎችና የኃይል መስጫ ጣቢያዎች በብዛት ስለሚገኙ ነው፡፡ ፈጣን የኢንዱስትሪ ዕድገትና የከተማ መስፋፋት ቢኖርም የአየር ብክለቱን ለመቆጣጠር የሚያስችል ተገቢ ዘዴ አልተፈጠረም፡፡ ከሃያ ሦስት ሚልዮን በላይ የሕዝብ ቁጥር ያላቸው የሕንድ ከተሞች የዓለም የጤና ድርጅት ካስቀመጠው የጤና ደረጃ አመላካች (indicator) በላይ የሆነ የአየር ብክለት ይታይባቸዋል፡፡ በሕንድ ለተፈጠረው የአየር ብክለት የሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ እነርሱም ከተሽከርካሪዎች የሚወጣ ጭስ፣ ከኢንዱስትሪና ከቤት በጭስ መልክ የሚወጡ በካይ ጋዞች ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ከፍተኛ የአየር ብክለት የሚታይባቸው የሕንድ ከተሞች ዴልሂ፣ ካልከታ፣ ሞምባይ፣ ቼኒ፣ አህመዳባጋድ፣ ባንግሎር፣ ሀይድራባድ፣ ፑን እና ካንፑር የመሳሰሉት ናቸው፡፡




ምስል 3.2 ኬሚካል ኢንዱስትሪ በጃፓን

- **የውኃ ብክለት**
    - **የውኃ ብክለት ምንድን ነው?**
    - **ለውኃ ብክለት ዋነኛ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?**

ውኃ ተበከለ ማለት ተፈጥሮአዊ የጥራት ደረጃው ቀነሰ ማለት ነው፡፡ ለውኃ መበከል የሚከተሉት ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

- **የእርሻ እንቅስቃሴ**

የእርሻ ምርትን ለማሳደግ እንደ ግብአት የሚያገለግሉ የማዳበሪያ ዓይነቶች፣ ፀረ-ተባይና አረም ማጥፊያ መድኃኒቶች (Chemicals) አፈር ውስጥ ከተደባለቁ በኋላ በዝናብ ውኃ እየታጠቡ ወደ ወንዝ ከዚያም ወደ ባሕር ውስጥ ይገባሉ፡፡ እነዚህም ወደ ወንዝና ወደ ባሕር የገቡት ፎስፌረስና ናይትሬት ንጥረ-ነገሮች **ዋቅላሚ** (Algae) የተባሉ የውኃ ውስጥ ተክሎች እንዲበቅሉ ያበረታታሉ፡፡ ዋቅላሚዎች የኦክሲጅን ፍጆታቸው ከፍተኛ በመሆኑ የአሳዎችንና የሌሎች ፍጥረታትን የኦክሲጅን ድርሻ ይሻማሉ፡፡

- **ከመኖሪያ ቤት የሚወጣ ፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ**

በገጠርና በከተማ ከመኖሪያ ቤቶች የሚወጣው ፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ በቀጥታ ወደ ውኃ አካላት ስለሚለቀቅ የውኃ አካላትን ይበክላል፡፡ ይህንን የተበከለ ውኃ ሳይታከምና ሳይጣራ ለምግብ ዝግጅት፣ ለመጠጥ፣ ለመታጠቢያና ለማጠቢያ ለመሳሰሉት አገልግሎቶች መጠቀም በጤንነት ላይ ከፍተኛ ችግር ያስከትላል፡፡ በእርሻ ሥራ ላይም ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

- **የኢንዱስትሪ ቆሻሻ**

ብዙውን ጊዜ ፋብሪካዎች በባሕር መዳረሻ አካባቢ፣ በወንዞች መገናኛና ዳርቻ ላይ ይመሠረታሉ። ይህም ለንግድ ሥራ፣ ለፋብሪካ መሣሪያዎች ማቀዝቀዣና የማጠቢያ ውኃ ለማግኘት እንዲሁም ባሕሩን ወይንም ወንዙን በቀጥታ ለፋብሪካ ዝቃጭ ማራገፊያነት ለመጠቀም ነው። ንጹሕ የቧንቧ ውኃ ለማግኘት የማይችሉ ሰዎች በዚህ መንገድ የተበከለውን የወንዝ ውኃ ለተለያየ አገልግሎት ስለሚያውሉት ከፍተኛ የጤና ጠንቅ ያስከትላል። በተጨማሪም የውኃ አካላትን ሥርዓተ ምኅዳር ያዛባል።

- **የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች**

የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ሙቅ ውኃ ወደ ወንዝና ወደ ባሕር ይለቃሉ። ይህ ሙቅ ውኃ የወንዝና የባሕር ውኃ ሙቀት በመጨመር በውኃ ውስጥ የሚገኙ ሕይወት ያላቸው አካላት ሊቋቋሙት ስለማይችሉ ሥነ ሕይወታዊ ቀውስ ያስከትላል። በተጨማሪም የኦክሲጅን እጥረት እንዲፈጠር ያደርጋል።

በተመሳሳይ መልኩ ከኒውክለር ማብላያ ጣቢያዎችና ከነዳጅ ማጣሪያዎች ድንገት አፈትልከው የሚወጡ (leakage) አደገኛ ንጥረ ነገሮች ከፍተኛ የጤንነት ችግር ያስከትላሉ።ለምሳሌ ከኒውክለር ጣቢያ ሾልኮ የወጣ ሜርኩሪ በሕጻናት ላይ የአእምሮ ችግርና የአካል ጉዳት ከማስከተሉም በላይ ሲወለዱም ያልተስተካከሉ እጅና እግሮች ያላቸው እንዲሆኑ ያደርጋል።


- **የውኃ ብክለትን መከላከያ ዘዴዎች**
  - የማዘጋጃ ቤትና የኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች የተደባለቁበት ውኃ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በሚገባ ማከም ወይም ማጣራት
  - ከዘመናዊ እርሻ የሚወጡ የፀረ አረምና ፀረ ተባይ ኬሚካል ዝቃጮች ፣ ከማዕድን ማውጫ ጣቢያ፣ ከፋብሪካዎች፣ ከጋራዦችና ከመኖሪያ ሕንጻዎች በፍሳሽ መልክ ከወራጅ ወንዝ፣ ከሐይቆችና ባሕሮች ጋር የሚደባለቁትን ንጥረ ነገሮች መቆጣጠር፣ፍሳሾቹ ወደ ውሃ አካላት እንዳይገቡ ማገድ
  - ብክለት ቀናሽ ቴክኖሎጂዎችን ማዳበር።

**ውስን ጥናት**

**የማዳበሪያ ከረጢት ላይ የሚሰጡ መመሪያዎች/መግለጫዎች**

- እያንዳንዱ የማዳበሪያ ከረጢት ላይ ሦስት ቁጥሮች ተቀምጠዋል። እነዚህ ቁጥሮች ከረጢቱ ውስጥ ስንት በመቶ ናይትሬት፣ ስንት በመቶ ፎስፈረስ እና ስንት በመቶ ፓታሰየም እንዳለ የሚያመለክቱ ናቸው። ለምሳሌ ቁጥሮቹ 12-3-10 ቢሆኑ የከረጢቱ አስራ ሁለት በመቶ ናይትሬት፣ ሦስት በመቶ ፎስፈረስ እና አሥር በመቶ ፖታሰየም እንደሆነ ይገልጻል።
- የእያንዳንዱ ማዕድን ጥቅም ተገልጿል።
- አፈር ውስጥ መጨመር ያለበትን የማዳበሪያ መጠን ከቦታውና ከአፈሩ ዓይነት ጋር በማገናዘብ ከረጢቱ ላይ ተገልጿል
- ከተሰጠው መጠን በላይ መጨመር እንደሌለበትም ያስጠነቅቃል።
- ማደበሪያ ከተጠቀምን በኋላ ማደበሪያ የነካውን እጃችንን በደንብ መታጠብ እንዳለብን ያስጠነቅቃል።

- የማዳበሪያውን ከረጢት ለምግብ እህል ወይም ዱቄት መያዣነት መጠቀም እጅግ አደገኛ ነው።




ምስል 3.3 የማዳበሪያ ከረጢት

### የክለሳ ጥያቄዎች 3.1

**ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች፡-**

- ሥርዓተ ምኅዳር ምንድን ነው?
- የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ስንል ምን ማለታችን ነው?
- የውኃና የአየር ብክለት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
- የተፈጥሮ ሀብቶች ምንድን ናቸው?

**ለ. የቡድን ሥራ**

በአካባቢያችሁ በሥርዓተ ምኅደር ውስጥ በሚገኙ አካላት መካከል የሚኖረውን ግንኙነት በተመለተ መረጃዎችን አሰባስቡ። ከዚያም በተወካያችሁ አማካኝነት እክፍላችሁ ውስጥ ተወያዩበት።

**ሐ.የሚከናወኑ ተግባራት**

- በአካባቢያችሁ ሥርዓተ ምኅዳር ውስጥ ሕይወት ያላቸውንና የሌላቸውን ነገሮች በየፈርጃ ለይታችሁ ዘርዝሩ።

## 3.2 የዓለም ሙቀት መጨመር መንሥኤና ውጤት

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የዓለም ሙቀት መጨመር መንስሥኤን ትለያላችሁ።
- የዓለም ሙቀት መጨመር በሰዎች፣ በእጽዋትና በዱር አንስሳት ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ትገመግማላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

- አፍሳሽ
- የኦዞን ንጣፍ
- አሲዳማ ዝናብ

**የዓለም ሙቀት መጨመር (Global warming) ምክንያቶች**


- ዓለም አቀፍ የሙቀት መጨመር ስንል ምን ማለታችን ነው?
- የዓለም አቀፍ ሙቀት መጨመር ምክንያቶችና ውጤታቸውን ዘርዝሩ፡፡
- የዓለም አቀፍ የሙቀት መጨመር ሁኔታን ለመቀነስ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ምንድን ናቸው?
- ስለ አፍሳሽ (Green house effect) የምታውቁትን አጭር መግለጫ ጻፉ፡፡


## ◈ የአፍሳሽ (Green house effect) ተጽእኖ

በከባቢ አየር (Atmosphere) የሚካሄድ ድርጊት ውጤት ጣሪያ ግርግዳው መስታወት ሆኖ አረንጓዴ ቀለም ከተቀባ ቤት ውስጥ ከሚካሄድ ድርጊት ውጤት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ምክንያቱም ከባቢ አየር ወደ መሬት የሚመጣውን አብዛኛውን ባለአጭር ሞገድ የፀሐይ ብርሃን በቀላሉ ሲያስተላልፍ ከመሬት ተንፀባርቆ የሚመለሰውን ባለረጅም የሙቀት ሞገድ ግን እንዳያመልጥ ፍጥነቱን ያዘገየዋል፡፡ በዚህ መንገድ የመሬት የአካባቢው ሙቀት ከፍተኛ ሆኖ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በቀንና በማታ የሙቀት መጠን መካከል ከፍተኛ ልዩነት እንዳይኖር ይከላከላል፡፡ አፍሳሽ (Green house effect) የምንለው ይኸንን ሁኔታ ነው፡፡ የአፍሳሽ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በርና መስኮቶቹ ሙሉ በሙሉ የተዘጉ መኪና ነው፡፡ የዚህን መኪና በር በመክፈት ወደ ውስጥ ስትገቡ ሙቀቱ ከፍተኛ ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡ ሙቀት ከመሬትና ከከባቢ አየር ወደ ላይ ማለትም ወደ ሕዋ መውጣቱ የማያቋርጥ ሂደት ነው፡፡

መሬት ከቀን እስከ ቀትር ባለው ጊዜ ወደ ከባቢ አየር አንጸባርቃ ከምትመልሰው የሙቀት ሞገድ በላይ ከፍተኛ ሙቀት ታገኛለች፡፡ በዚህ የተነሳ በመሬት አካባቢ ያለው የሙቀት መጠን ከሰዓት በኋላ ከስምንት እስከ አሥር ሰዓት ድረስ ሙቀቱ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ማታ ማታ የሚኖረው ሁኔታ ግን ከዚህ ለየት ያለ ነው፡፡ መሬት ማታ ሙቀትን አንጸባርቃ በመመለሷ ምክንያት የሙቀት መጠን ይቀንሳል፡፡ የመሬት ወለል ከመቀዝቀዙም በላይ የከባቢ አየር ሙቀትም ይቀንሳል፡፡ መሬት ከከባቢ አየር በበለጠ የሙቀት ሞገድን ስለምታንጸባርቅ ከከባቢ አየር የበለጠ ትቀዘቅዛለች፡፡

ስለ አፍሳሽ (Green house effect) ሲነሣ በከባቢ አየር የሚገኙ ጋዞች ሚና መረሳት የለበትም፡፡ ከአፍሳሽ ጋዞች በተለይ ካርቦንዳይ ኦክሳይድ በተለያዩ ምክንያቶች ከመሬት ወጥቶ ከከባቢ አየር ጋር ይደባለቃል፡፡ ይህም ፀሐይ በተቃራኒው ወደ መሬት የሚመጣውን ባለአጭር ሞገድ የፀሐይ ጨረር ያለአንዳች ችግር ወደ መሬት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡ ከመሬት ተንጸባርቆ ወደ ከባቢ አየር የሚመለሰውን ባለ ረጅም ሞገድ ጨረር እንደብርድልብስ አምቆ በመያዝ የከባቢ አየር ሙቀት መጠን እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ ከባቢ አየር ውስጥ ከሚገኙት የአፍሳሽ ጋዞች 0.03 በመቶ የሚሆነው ካርቦንዳይኦክሳይድ ነው፡፡ ስለዚህም ይህ ጋዝ የአየር ንብረትን ለመለወጥ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የአፍሳሽ ጋዞች መጠንና ዓይነት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል፡፡ ይህም ሙቀትን አፍኖ በመያዝ የዓለም ሙቀት መጠን እንዲጨምር (Global warming) ምክንያት ሆኗል፡፡ የዓለም የሙቀት መጠን እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ብቻ በ5° ሴልሸየስ ጨምሯል፡፡ ይኸን ለውጥ የበለጠ ለመረዳት ቀጥሎ የቀረበውን ምስል ተመልከቱ፡፡




የአፍላሽ ጋዞች ድርሻ በመቶኛ

- መሬት የምትጠቀምበት ሙቀት 51%
- የሚባክነው ሙቀት 49%

*ምስል 3.4 የአፍላሽ ተጽእኖ*

## የዓለም ሙቀት መጨመር (Global Warming) ውጤቶች

- በአፍላሽና በዓለም ሙቀት መጨመር መካከል ያለው ግንኙነት ምንድነው?

### ሀ. የካርቦንዳይኦክሳይድ ($Co_2$) መጠን መጨመር

ለዓለም ሙቀት መጨመር ዋነኛ መንሥኤ የካርቦንዳይኦክሳይድ መጠንና የሌሎች የአየር በካይ ጋዞች መጠን መጨመር ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከሁሉም በላይ ለሙቀት መጨመር ዋነኛው መንስሥኤ የካርቦንዳይኦክሳይድ መጠን መጨመር ነው፡፡ ባለፈው መቶ አመት ብቻ የከባቢ አየር ሙቀት አሥራ - አምስት በመቶ ጨምሯል፡፡ ይህ ሁኔታ በዚሁ ከቀጠለ በ2042 ዓ.ም የካርቦንዳይ ኦክሳይድ መጠን አሁን ያለውን እጥፍ ይሆናል፡፡ በቀጣዩ ምዕተ ዓመት የዓለም አማካኝ (average) የሙቀት መጠን ከ1.50 — 4.5° ሴልሽየት ሊጨምር እንደሚችል ይገመታል፡፡ የበለጸጉ ሀገሮች በዓለም ላይ ከሚገኘው የኃይል ፍጆታ ¾ ኛውን ተጠቃሚዎች እንደመሆናቸው ለዓለም ሙቀት መጨመር ዋናዎቹ ተጠያቂ ናቸው፡፡ ከአፍላሽ ጋዞች የካርቦንዳይኦክሳይድ ድርሻ ሰባ ሁለት በመቶ ነው፡፡

### ለ. የክሎሮፍሎሮ ካርቦን (CFCS) ጋዞች መለቀቅ

የሰው ልጅ ወደ ከባቢ አየር የሚለቃቸው የክሎሪን (chlorine) ቤተሰብ ንጥረ - ነገሮች ክሎሮፍሎሮ ካርቦንኖች (Chloroflurocarbons — CFCs) ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነርሱም የሚገኙት ከኤሮሶሎች (Aerosols) ለምሳሌ የፀጉር ቀለም (hair spray)፣ የጠረን ማስወገጃ ንጥረ - ነገሮች (deodorants)፣ በራሪ ነፍሳትን ማጥፊያ መድኃኒቶች (Fly killers)፣ ከታሸጉበት ቆርቆሮ ለማስወጣት የሚጠቅሙ (propellants) ጋዞች ናቸው፡፡ ሌሎች የክሎሮፍሎሮካርቦን ጋዝ ምንጮች ደግሞ የአየር ሙቀት ማስተካከያዎች (Air conditioners)፣ ማቀዝቀዣዎች፣ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ከአፍላሽ ጋዞች የክሎሮፍሎሮ - ካርቦን ድርሻ አሥራ ሦስት በመቶ ነው፡፡

### ሐ. የሜቴን ጋዝ መጨመር

ሜቴን ጋዝ ሽታና ቀለም የሌለው እንደ ነዳጅ ጥቅም ላይ የሚውል ጋዝ ነው፡፡ የሚገኘውም ከብስባሽ ሙት አካላት፣ ከቆሻሻ መጣያና ማጠራቀሚያዎች፣ ከአረንቋማ መሬቶች፣ ከእንስሳት ፍግና ከእርሻ ማሳዎች ነው፡፡ ከአፍላሽ ጋዞች የሜቴን ድርሻ አሥር በመቶ ነው፡፡

### መ. የኒውትርየስ ኦክሳይድ (Nitrous oxide)መጨመር

ኒውትርየስ ኦክሳይድ የሚገኘው ከመኪናዎች ጭስ፣ ከኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች እና ከእርሻ ማዳበሪያ ማዕድናት ነው፡፡ ከአፍላሽ ጋዞች ውስጥ አምስት በመቶ ድርሻ አለው፡፡

**ውስን ጥናት**

### ኤልኒኖ (*El NiNo*)

በሰላማዊ ውቅያኖስ(Pacific Ocean) ጠረፋማ አካባቢ የሚመላለሱ የፔሩና የኢኳዶር አሳ አስጋሪዎች ኤልኒኖን ለብዙ ዓመታት ያውቁታል፡፡ በየሰባት ዓመቱ በታኅሣሥና በጥር ወራት በእነዚህ ሀገሮች ጠረፋማ የውቅያኖስ ዳርቻዎች የሚገኙ አሳዎች ሙሉ በሙሉ ይጠፋሉ፡፡ የአሳ ማስገሩም ሥራ ይቋረጣል፡፡ የደቡብ አሜሪካ አሳ አስጋሪዎች ይህንን ክስተት ኤልኒኖ በማለት ይጠሩታል፡፡ ኤልኒኖ በስፖንኛ ቋንቋ "ሕጻኑ ክርስቶስ" እንደማለት ነው፡፡ ይህንን ስም የሰጡበት ምክንያትም ወቅቱ የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል የሚከበርበት በመሆኑ ነው፡፡

ኤልኒኖ በሂደት ላይ ባለበት ወቅት በነፋስና በውቅያኖስ ሞገድ፣ በውቅያኖስና በከባቢ አየር ሙቀትና በሥረ-ሕዋ መካከል ያለውን ግንኙነት (መስተጋብር) በመቀየር በዓለም ዙሪያ ያልተጠበቀ የአየር ጠባይ ሁኔታን በማስከተል ከፍተኛ ጥፋት ያመጣል፡፡

በመሠረቱ ሳይንቲስቶች እንኳ እስከዛሬ ድረስ ኤል-ኒኖ እንዴት እንደሚፈጠር በትክክል አልተረዱም፡፡ ይሁን እንጂ በ1985 ዓ.ም. በካሊፎርንያ (የተባበሩት አሜሪካ ግዛቶች) የደረሰው የጐርፍ አደጋ፣ በ1987ዓ.ም. በደቡብ አሜሪካ፣ በአፍሪካና በአውስትራሊያ ለታየው ድርቅ መከሰት ኤልኒኖ ምክንያት እንደነበረ ይታመናል፡፡ ኤልኒኖ በተከሰተበት አካባቢ በጥቂት ሰዓታት ያለፈ ቢሆንም ሞት፣ የንብረት ውድመት፣ የመሠረተ ልማት መፈራረስ፣ የዛፎች መገንደስ፣ የቤቶች መፈራረስ አስከትሏል፡፡ ሁሉም ኤልኒኖዎች በባሕርያቸው አንድ ዓይነት አይደሉም፡፡ የከባቢ አየር መስተጋብርም ቢሆን በሁሉም ዓይነት ኤልኒኖ ወቅት አንድ ዓይነት ላይሆን ይችላል፡፡ የኤልኒኖን አመጣጥ፣ ምንነት፣ የሚያስከትለውን ጥፋት ለማወቅ እንዲሁም ቅድመ - ማስጠንቀቂያ ለመስጠት የሚያስችል ጥናት በመደረግ ላይ ነው፡፡

## ◈ የኦዞን ንጣፍ ($O_3$ ንጣፍ) መሸንቆር

የኦዞን ንጣፍ ሥረ-ሕዋ በሚባለው የከባቢ አየር ክፍል(ከባሕር ወለል በላይ ከ25-30 ኪሎሜትር) ውስጥ ይገኛል፡፡ የኦዞን ንጣፍ አደገኛ ባለአጭር ሞገድ የፀሐይ ጨረር (ultraviolet rays of the sun) ወደ መሬት

እንዳይደርስ የሚከላከል የከባቢ አየር ክፍል ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በሥረ-ሕዋ (stratosphere) ውስጥ የሚገኘው የኦዞን ንጣፍ እየሳሳና እየተሸነቆረ ነው፡፡ በየዓመቱ የተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶችን የቆዳ ስፋት ያክል ሽንቁር (ቀዳዳ) በአንታርክቲክ ውቅያኖስ አካባቢ (አናት ላይ) ባለው የኦዞን ንጣፍ ላይ እየተሰተዋለ ነው፡፡ በ1981ዓ.ም ተመሳሳይ ሽንቁር በአርክቲክ አካባቢም (አናት ላይ) መኖሩ ታይቷል፡፡ ይህ አደገኛ የፀሐይ ጨረር ወደ መሬት ከደረሰ በተለይ የቆዳ ካንሰርን ያስፋፋል፡፡ የቆዳ ካንሰሩ በስፋት የሚታየው ጥቁር ቆዳ ካላቸው ሰዎች ይልቅ ነጭ ቆዳ ባላቸው ሰዎች ላይ ነው፡፡ የምግብ ሰብል ዕድገትንም ያስተጓጉላል፡፡ በሰዎች ላይ የአተነፋፈስ ችግር ከማስከተሉም በተጨማሪ መጥፎ ሽታና የራስ ምታት ያመጣል፡፡ የአየር ሙቀትም ይጨምራል፡፡

ለኦዞን ንጣፍ መሸንቆር ዋነኛ ምክንያቶች ክሎሮፍሎሮ-ካርቦንስ የተባሉ የክሎሪን ቤተሰብ የሆኑ ንጥረ ነገሮች ወደ ከባቢ አየር መለቀቃቸው ነው፡፡ የአንድ በመቶ የኦዞን መሸንቆር አሁን ያለውን የቆዳ ካንሰር መጠን በአመስት በመቶ ያሳድገዋል፡፡ ይኸ የኦዞን ንጣፍ መሸንቆር ከ1961 ዓ.ም ጀምሮ ዕድገቱ ሦስት በመቶ ነው፡፡

## ◈ አሲዳማ ዝናብ

አሲዳማ ዝናብ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየውና የታወቀው በ1940ዎቹ ዓ.ም በስካንዲኔቪያን ሀገሮች ንጹሕ ውኃ ውስጥ በርካታ አሣዎች ሞተው ከተገኙ በኋላ ነበር፡፡ ሞተው የተገኙት አሳዎች የነበሩበት ውኃ ከመጠን ያለፈ የአሲድ መጠን ተገኝቶበታል፡፡ ተጨማሪው አሲድ በዝናብ ውኃ አማካኝነት የመጣ መሆኑም ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአሲድ ዝናብ የሚለው ስያሜ እየተለመደ መጥቷል፡፡ ለአሲድ መፈጠርም ምክንያት የሆኑት ከኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች፣ ከኢንዱስትሪና ከመኪናዎች የሚወጡ ሰልፈር - ዳይኦክሳይድ (Sulphur-dioxide) እና ናይትሮጂን - ኦክሳይድ (Nitrogen — oxide) የሚባሉ ጋዞች ናቸው፡፡ እነዚህ ጋዞች በንፋስ ግፊት ባሕርና ሀገሮችን አቋርጠው በደረቅ ክምችት (dry deposition) መልክ መሬት ላይ የሚከማቹ አለበዚያም ወደ አሲድነት ተቀይረው ሰልፈሪክ አሲድ (sulphuric acid) እና ናይትሪክ አሲድ (Nitric acid) በመሆን በዝናብ መልክ በእርጥብ ክምችትነት (wet deposition) ሊመጡ ይችላሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ በመላው ሰሜን ምዕራብ አውሮፓ ሀገሮች የ "PH" መጠን በ4 እና 4.5 መካከል ነው፡፡ እስከዛሬ ከተመዘገቡት ሁሉ ዝቅተኛው PH 2.4 ነው፡፡ እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈልገው የ PH መጠን በአንድ ቁጥር ቀነሰ ማለት የአሲድ መጠን በአሥር እጅ ጨመረ ማለት ነው፡፡

- ➢ የ "PH" ቁጥሮች ከ0-14 ነው፡፡ የ“PH” ዋጋ የሚገልጸው የአንድ ነገር የአሲድ ወይም የአልካላይን መጠን ነው፡፡

## ◈ የአሲድ ዝናብ የሚያስከትላቸው ተጽእኖዎች

- የሐይቆች አሲዳማነት በመጨመሩ በርካታ አሣዎችና እጽዋት ሞተዋል፡፡
- የአፈር አሲዳማነት ሲጨምር የሰብል ዓይነቶች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል፡፡
- ደኖች በሚበቅሉበት አካባቢ ያሉ ተክሎች በጣም አስፈላጊ የሆኑ ንጥረነገሮች እንደ ካልሰየምና ፓታስየም ያሉት ታጥበው ስለሚሄዱ (leached) ደኖቹ ይጠፋሉ፡፡ ለእጽዋት ዕድገት አስፈላጊ በሆኑ ማዕድናት ምትክ ለእጽዋት ሥር አደገኛ የሆኑ ማንጋኒዝና አልሙኒየም የተባሉ ማዕድናት ብቅ ይላሉ፡፡ በዚህም የተነሣ እጽዋቱ ድርቅን፣ ውርጭንና የእጽዋት በሽታዎችን መቋቋም ይሳናቸዋል፡፡ ቅጠሎቻቸውንም ያራግፋሉ፡፡
- በአሲድ ዝናብ ምክንያት ሕንጻዎች ቀለማቸውን ያጣሉ፡፡ መሸርሸርም ይደርስባቸዋል፡፡
- ውኃ የበለጠ አሲዳማ ሲሆን የጤና ጠንቅ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ውኃ ውስጥ የአልሙኒየም መጠን ሲበዛ አዕምሮ ነገሮችን እንዳያስታውስ /እንዲረሣ / ለሚያደርግ በሽታ (Alzheimer's disease) ያጋልጣል፡፡



ምስል 3.5 የአሲድ ዝናብ ውጤቶች



ምስል 3.6 የአሲድ ዝናብ በሕንጻዎች ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ

## ◈ የግግር በረዶ መቅለጥ (Melting Ice /Glacier)

የግግር በረዶ መቅለጥና በፈሳሽ/በውኃ መልክ መኀዝ የሙቀት መጠን ለመጨመሩ ማሳያ ነው፡፡ በመካከለኛው እስያ የሚገኘው የቲቤት ተራራ አናት ላይ የነበረው ግዙፍ ግግር በረዶ የአካባቢው ሙቀት ከ2.5 እስከ 4 ሴልሽየስ በመጨረመሩ ምክንያት መጠኑ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል፡፡ የአልፓየን ግግር በረዶም ቢሆን መጠኑ ሃምሳ በመቶ ቀንሷል፡፡

የዓለም የሙቀት መጠን በዋልታዎች አካባቢ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ይህም የዋልታዎች አካባቢ ግግር በረዶዎች እየቀለጡ ወደ ውቅያኖሶች በመግባት የውቅያኖሶችን ከፍታ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ አማካይ የባሕር ወለል ከፍታ(mean sea level) በአሥር ጫማ እንኳ ቢጨምር በርካታ የዓለም ሀገሮችንና የጠረፍ ከተማዎችን የማጥለቅለቅ አቅም ይኖረዋል፡፡

## ◈ የጐርፍ አደጋ (flooding)

በጐርፍ የመጥለቅለቅ አደጋ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል፡፡ እነርሱም፡-

1. በሐሩራዊ አውሎ ንፋስ (Tropical Cyclone) ምክንያት ወደፊት ወይም ወደላይ የሚንቀሳቀሱ ተገፍቶ ገብ ኃይለኛ ንፋሶች (storms or tidal surges) ይፈጠራሉ፡፡ እነዚህ አውሎ ንፋሶች በተለያዩ ስሞች ይጠራሉ፡፡ ለምሳሌ ሃሪኬን፣ ታይፉን፣ ዊሊ ዊሊ በመባል ይጠራሉ፡፡
2. የወንዞች ያለቅጥ መሙላትና ከመውረጃ በዮቻቸው አልፈው መውጣት ናቸው፡፡

## ◈ በወንዞች መሙላት የሚፈጠር የጐርፍ አደጋ

በሕንድ የጋንጀስና (Ganges) የብራህማፑትራ (Brahmaputra) ወንዞች ከሂማሊያ ተራራ ተነሥተው ቁልቁል በመፍሰስ ዝቅተኛ አካባቢ ሲደርሱ (ውቅያኖስ አካባቢ የሚደባለቁበት አካባቢ) ከተራራው አጥበው ያመጡትን ደለል ያከማቻሉ፡፡ የደለሉ መጠን እየጨመረ ሲሄድ በርካታ ደሴቶችን ይፈጥራል፡፡ እነዚህ ደሴቶች ደግሞ ወንዞቹን ባለ ብዙ ቅርንጫፎች ወይም አካፋዮች (distributories) አድርገዋቸዋል፡፡ የደለል ክምር ደሴቶቹም ለም ስለሆኑ ብዙ የሩዝ ሰብል አምራች ገበሬዎች ሠፍረውባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የደለል ክምችት መጠን እየጨመረ በሄደ ቁጥር የወንዞቹ ዋና መውረጃ በዮች ይዘጋሉ፡፡ ስለዚህ የወንዞቹ ውኃ ወደ ውጪ ስለሚፈስ ከጊዜ ወደ ጊዜ

የጐርፍ መጥለቅለቅ አደጋውን የከፋ ያደርገዋል፡፡ ይህ የጐርፍ መጥለቅለቅ አደጋ የሚከሰተው ሁልጊዜ ሰገር ዝናብ /ከሕንድ ውቅያኖስ የሚመጣ ዝናብ(monsoon rain) ወቅቱን ጠብቆ በሚዘንብበት ጊዜ ነው፡፡ ሌላው ለባንግላዴሽ በጐርፍ የመጥለቅለቅ አደጋ ምክንያት የሚሆነው ከሂማላያ ተራራ እየቀለጠ በውኃ መልክ የሚወርደው የበረዶ ክምር ነው፡፡ የተራራው ላይ ተክሎች (ደን) መመንጠር ደግሞ ሁኔታውን ያባብሰዋል፡፡

### ◈ በአውሎ ንፋስ (Storm or Tidal surge) የሚፈጠር የጐርፍ አደጋ

በደቡባዊ ባንግላዴሽ የጋንጀስና የብራህማፑትራ ወንዞች በሚያመጡት የደለል ክምችት የተፈጠሩት ደሴቶች ለሩዝ ምርት ተስማሚ በመሆናቸው ከ30 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ገበሬዎች ሠፍረውባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከመስከረም 15 እስከ ታኅሣሥ 15 ባለው የመጸው ወቅት (Autumn) የታይፉን ንፋስ የሕንድ ውቅያኖስን ውኃ እየገፋ እስከ ቤንጋል የባሕር ወሽመጥ ያደርሰዋል፡፡ የቤንጋል የባሕር ወሽመጥም ወደ ባንግላዴሽ አቅራቢያ እየጠበበና ጥልቀቱም እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ በዚህ መልክ የመጣው ውኃ አንዳንድ ጊዜ እስከ አራት ሜትር ርዝመት ያለው አውሎ ነፋስ ይፈጥራል፡፡ በነፋሱ ምክንያት የተፈጠረው ሞገድ ደግሞ ሌላ ተጨማሪ የአራት ሜትር ከፍታ (ሽቅቦሽ) ይኖረዋል፡፡ ከዚህ የተነሣ ምንም ዓይነት የጐርፍ አደጋ የሌላቸው ደሴቶች በጐርፍ የመጥለቅለቅ አደጋ ያጋጥማቸዋል፡፡ ይህም ከፍተኛ የሕይወትና የንብረት ውድመት ያስከትላል፡፡ ለምሳሌ ቀይ መስቀል በ1973 ዓ.ም በተከሰተ አውሎ ነፋስ የደረሰውን አደጋ ከሦስት ቀናት በኋላ እንዳረጋገጠው 40,000 ሰዎች ሞተዋል፡፡ በወቅቱ ከአደጋው የተረፉት በሰዓት 180 ኪሎ ሜትር ፍጥነት ይጓዝ የነበረውን የነፋስ ግፊት መቋቋም የቻሉ ብቻ ነበሩ፡፡



*ምስል 3.7 የባንግላዴሽ የጐርፍ መጥለቅለቅ*

## ክለሳ ጥያቄዎች 3.2

### ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች

- በከባቢ አየር (Atmosphere) ውስጥ ከሙቀት ጋር በተያያዘ የሚከናወኑ ድርጊቶች ከአፍላሽ (Green house) ጋር የሚመሳሰሉበትን ሁኔታ አስረዱ፡፡
- ለዓለም ሙቀት መጨመር በዋነኛነት የሚጠቀሰው ጋዝ ምን ይባላል? ድርሻውስ ስንት በመቶ ነው?
- የክሎሮፍሎሮ ካርቦን ንጥረ ነገር ምንጮች ምንድን ናቸው?
- የኦዞን ንጣፍ ጠቀሜታ ምንድን ነው?
- የአሲድ ዝናብ ምንድነው? አመጣጡና ውጤቱ ምን እንደሆነ በአጭሩ ግለጹ፡፡
- ለግግር በረዶመቅለጥ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ዐበይት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የግግር በረዶ መቅለጥ የሚያስከትላቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?

### ለ. የሚከናወኑ ተግባራት

- የዓለም ካርታ ሠርታችሁ የጐርፍ አደጋ በተደጋጋሚ የሚያጠቃቸውን አካባቢዎች አመልክቱ፡፡

## ቁልፍ ቃላት

- **ሥርዓተ ምኅዳር:-** በአንድ ተፈጥሮአዊ አካባቢ በሚገኙ እጽዋት፣ እንስሳትና ሌሎችም ሕይወት ያላቸው ነገሮች የሕይወት ዑደት ተሳሥሮ፣ ከሌሎች ሕይወት ከሌላቸው ነገሮች ጋር ያላቸው ተጣምሮ እንዲሁም ከአካባቢያቸው ጋር ያላቸው ቁርኝት የሚገለጽበት ተፈጥሮአዊ ሥርዓት ነው።
- **ብክለት:-** የአንድ የተፈጥሮ ሀብት (ውሃ፣ አየር፣ አፈር ወ.ዘ.ተ) የጥራት ደረጃ መቀነስና በሚፈለገው መጠን ጥቅም ላይ ለመዋል ያለመቻል ነው።
- **የተፈጥሮ ሀብቶች:-** በአንድ ተፈጥሮአዊ አካባቢ የሚገኙ ለሰው ልጅ አገልግሎት የሚውሉ ውኃ፣ አፈር፣ ማዕድናት፣ እጽዋት፣ የዱር እንስሳት፣ አየር፣ ወንዝ የመሳሰሉትን ማለት ነው። የተፈጥሮ ሀብቶች በቀጥታ ወይንም በተዘዋዋሪ ለሕይወታችን፣ ለቁሳዊና ለመንፈሳዊ ፍላጎታችን አገልግሎት የሚሰጡን በተፈጥሮ የምናገኛቸው ነገሮች ናቸው።
- **የተፈጥሮ ሀብት ውድመት:-** የተፈጥሮ ሀብት ያለአግባብ ጥቅም ላይ ሲውሉ፣መጠናቸው ከጊዜ ወደጊዜ እያነሰ ሲሄድ፣ ሲጎሳቆሉና ሲጠፉ ያለው ሂደት ወይንም ጥፋት ነው።
- **የአሲድ ዝናብ:-** በአየር መበከል ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ የአሲድ መጠን የያዘ ዝናብ ነው።
- **የዓለም ሙቀት መጨመር:-** (Global warming) በአፍላሽ ጋዞች በተለይም በካርቦንዳይኦክሳይድ ልቀት ምክንያት የዓለም ሙቀት እየጨመረ መሄድን ይመለከታል።
- **ጠፍ አፈር(laterite soil):-** በሐሩራዊው ዝናባማ ደን የሚገኝ የፖታሽ፣ የናይትሮጂን እና የፎስፎረስ ማዕድናት እጥረት የሚታይበት ነገር ግን በብረትና በአሉሚኒየም ማዕድናት የዳበረ መካን አፈር (ለምነት የሌለው አፈር) ማለት ነው።

## ማጠቃለያ

- ሥርዓተ ምኅዳር በአንድ ተፈጥሮአዊ አካባቢ (natural unit) የሚኖሩ የተክሎች፣ የእንስሳት፣ የሰውና የጥቃቅን ነፍሳት (organisms) የሕይወት ዑደት ትስስር፣ ከሌሎች ሕይወት ከሌላቸው ጋር ያላቸው ተጣምሮ እንዲሁም ከአካባቢያቸው ጋር ያላቸው ቁርኝት የሚታይበት ተፈጥሮአዊ ሥርዓት (Ecosystem) ነው፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶች በአንድ ተፈጥሮአዊ አካባቢ የሚገኙ ለሰው ልጅ ጥቅም የሚሰጡ ልዩ ልዩ አካላት (Elements) ስብሰብ ነው፡፡
- የተፈጥሮ ሀብትን በተገቢ መንገድ መጠቀም ያለመቻልና በተፈጥሮ ሀብቱ ላይ ጥፋት (ጉዳት) ማድረስ የተፈጥሮ ሀብት ውድመት ያስከትላል፡፡
- በተፈጥሮ ሀብቶች መካከል ጥብቅ ቁርኝት በመኖሩ ከፍተኛ መደጋገፍ አለ፡፡ ስለዚህ የአንድ የተፈጥሮ ሀብት ሕልውና መነካት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በሌላኛውም የተፈጥሮ ሀብት ሕልውና ላይ ተጽእኖ ያስከትላል፡፡
- የሰው ልጆች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ለአየር፣ ለውኃና ለአፈር መበከል አስተዋጽኦ አለው፡፡
- አፍላሽ (Green house effect) ለዓለም ሙቀት መጨመር ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡
- የኦዞን ንጣፍ (ozone layer) እንደ ጃንጥላ ሆኖ አደገኛ የፀሐይ ጨረር (Ultraviolet rays of the sun) ወደ መሬት እንዳይደርስ የሚከላከል በከባቢ አየር (Atmosphers) የሚገኝ ንጣፍ ነው፡፡
- ክሎሮ ፍሎሮ ካርቦን (CFCS) ጋዝ ለኦዞን ንጣፍ መሸንቆር በዋና ምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡
- አሲዳማ ዝናብ በውኃ አካላት የብዝኃ ሕይወት መጥፋትን፣ የሰብል ዕድገት መዘግየትን፣ የጤና ስጋትን፣ የሕንጻዎችና ሐውልቶች መሸርሸርን ያስከትላል፡፡
- የዓለም የሙቀት መጠን መጨመር በአካባቢያችን ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ እያስከተለ ይገኛል፡፡ የዓለም ሙቀት መጨመር በተለይ የዋልታዎች አካባቢ የግግር በረዶ የመቅለጥ መጠን መጨመርን፣ የባሕር ጠለል ከፍታ መጨመርን ያስከትላል፡፡ ይህ ደግሞ በተራው በአካባቢው የሚገኙ ዝቅተኛ ቦታዎችን በጐርፍ መጥለቅለቅን የሕይወትና የንብረት ውድመትን ያስከትላል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የክለሳ ጥያቄዎች

## ሀ. እውነት ወይንም ሐሰት

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ።***

1. የዓለም የሙቀት መጠን መጨመር ለግግር በረዶ መቅለጥ አስተዋጽኦ አለው።
2. የክሎሮፍሎሮ-ካርቦንስ ወደ ከባቢ አየር መለቀቅ ለኦዞን ንጣፍ መሸንቆር ዋነኛ ምክንያት ነው።
3. የደኖች መጨፍጨፍ ለዓለም ሙቀት መጨመር ምንም ዓይነት አስተዋጽኦ የለውም።
4. አሲዳማ ዝናብ በውኃ አካላት ላይ የብዝኃ ሕይወት መመናመንን ያስከትላል።
5. የተፈጥሮ ሀብት ውድመትን ለመከላከል ከአካባቢያችን ምንም ነገር መጠቀም አይገባም።

## ለ. አዛምድ

***በ"ሀ" ረድፍ ሥር ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች በ"ለ" ረድፍ ሥር ካሉት ቃላት ጋር አዛምዱ።***

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ______1. የእጽዋት መጨፍጨፍ | ሀ. ካርቦን ዳይኦክሳይድ |
| ______2. የአፍላሽ ጋዝ ውጤት | ለ. የኦዞን ንጣፍ |
| ______3. የዋቅላሚ መራባት | ሐ. የዓለም ሙቀት መጨመር |
| ______4. የከባቢ አየር ሙቀት ይጨምራል | መ. የተፈጥሮ ሀብት ውድመት |
| ______5. መሬትን ከአደጋኛ ፀሐይ ጨረር ተከላካይ | ሠ. የቆዳ ካንሰር |
| | ረ. አሲዳማ ዝናብ |
| | ሰ. ብክለት |
| | ሸ. ፎስፈረስና ናይትሬት |
| | ቀ. ሥርዓተ ምኅዳር |

## ሐ.ምርጫ

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ መርጣችሁ ጻፉ።***

1. ከሚከተሉት አንዱ ለበረሃማነት መከሰት ምክንያት አይደለም።
   ሀ. የሕዝብ ቁጥር መጨመር
   ለ. ዘመናዊ የእርሻ ዘዴዎችን መጠቀም
   ሐ. የግጦሽ ቦታን ከአቅም በላይ መጠቀም
   መ. ደኖችን መመንጠር

2. ከሚከተሉት አንዱ የአፍላሽ ጋዞችን ምንነት አይገልጽም፡፡
   ሀ. አደገኛ የፀሐይ ጨረር ወደ መሬት እንዳይደርስ ይከላከላሉ፡፡
   ለ. የዓለም ሙቀት እንዲጨምር ያደርጋሉ፡፡
   ሐ. የበረዶ መቅለጥና የጐርፍ መጥለቅለቅ አደጋን ያመጣሉ፡፡
   መ. ለበረሃማነት መስፋፋት አስተዋጽኦ አላቸው፡፡
3. በአንድ ተፈጥሮአዊ አካባቢ የሚኖሩ ሕይወት ያላቸውና የሌላቸው ነገሮች የእርስ በእርስ ግንኙነትና ከአካባቢያቸው ጋር ያላቸው ቁርኝት ________ይባላል፡፡
   ሀ. ሥነ ምኅዳር
   ለ. ምቹጌ
   ሐ. ሥርዓተ ምኅዳር
   መ. ብዝኃ ሕይወት
4. ከሚከተሉት አንዱ በሥርዓተ ምኅዳር ውስጥ አይካተትም፡፡
   ሀ. አለቶችና ማዕድናት
   ለ. አፈር፣ ውኃና አየር
   ሐ. ጥቃቅን ነፍሳት፣ እጽዋትና እንስሳት
   መ. መልሱ የለም፡፡
5. ከሚከተሉት አንዱ የእርሻ ማዳበሪያ ከመጠን በላይ በመጠቀም ይከሰታል፡፡
   ሀ. የአየር ብክለት
   ለ. የሰዎችና የእንስሳት መካንነት
   ሐ. የከርሠ ምድር ውኃ ብክለት
   መ. የፀረ ሰብል ነፍሳት ወረርሽኝ

**መ. ባዶ ቦታ ሙሉ፡፡**

***የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በተስማሚ ቃላት ወይም ሐረጋት ሙሉ፡፡***

1. የአሲድ ዝናብ በውኃ አካላት ላይ ________________ ያስከትላል፡፡
2. የኦዞን መሸንቆር በሰዎች ጤና ላይ ____________________________ ያስከትላል፡፡
3. ወደ ከባቢ አየር በቀጥታ በመግባት የአየሩን ተፈጥሮአዊ የጥራት ደረጃ የሚቀንሱ ነገሮች _____ ይባላሉ፡፡
4. የአሲድ ዝናብ በሰው ልጆች ላይ የሚያስከትለው የጤና ችግር ______ በመባል ይታወቃል፡፡

**ሠ. የአጭር መልስ ጥያቄዎች**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡***

1. የማዳበሪያ ንጥረ - ነገሮችን ከሚፈለገው በላይ መጠቀም የሚያመጣው ችግር ምንድነው?
2. የኤሊኒኖ ምንነትና ውጤቱን በአጭሩ አብራሩ፡፡
3. በዓለም ሙቀት መጨመር፣ በግግር በረዶ መቅለጥና በጐርፍ መጥለቅለቅ መካከል ያለውን ተያያዥነት (ግንኙነት) በአጭሩ ግለፁ፡፡
4. ከኒውክሊየር ማብላያ ጣቢያዎች አፈትልከው የሚወጡ ንጥረ ነገሮች የሚያስከትሉትን ጉዳት ዘርዝሩ፡፡

## ፍተሻ

*ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሳጥኖቹ ውስጥ በማኖር አመልክቱ፡፡*

1. የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመንና በሥርዓተ ምኅደር ላይ የሚያስከትሉትን ጉዳትእተነትናለሁ፡፡ ☐
2. የተፈጥሮ ሀብቶችን በመንከባከብ ረገድ የበኩሌን አስተዋኦ አደርጋለሁ፡፡ ☐
3. ዐበይት አየርና ውኃ በካዮችን እጠቅሳለሁ፡፡ ☐
4. የዓለም ሙቀት መጨመር መንሥኤን እለያለሁ፡፡ ☐
5. የዓለም ሙቀት መጨመር በሰዎች፣ በተፈጥሮ እጽዋትና በዱር እንስሳት ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ እገመግማለሁ፡፡ ☐

# ምዕራፍ አራት

# ሕዝባዊ ጉዳዮች

***ከምዕራፉ የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት***

**ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-**

- ወጣቶች ኤች. አይ. ቪ . / ኤድስን በመዋጋትና፣ የሥነሕዝብ ፖሊሲንና የጾታ እኩልነትን በማረጋገጥ ዙሪያ ያላችሁን አስተዋጽኦ ታደንቃላችሁ፡፡
- የወጣት አጥፊነትን መቀነስ የሚያስችሉ ዘዴዎችን በምሳሌ ታስረዳላችሁ፡፡
- የተባበሩት መንግሥታት ዋና ዋና ተግባራት የመተዳደሪያ ደንቦችና የዓለም አቀፍ ትስስር ጽንሰ ሐሳብ ትገልጻላችሁ፡፡

## 4.1 ሕዝብ ነክ ጉዳዮች

***ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት***

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-**

- ኤች አይ.ቪ/ኤድስን ለመዋጋት የሚያስችል የሕይወት ክህሎት ታዳብራላችሁ፡፡
- የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ያለ ወገኖችን የሚንከባከቡ ግለሰቦች አርአያ አድርጋችሁ ትከተላላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- መታቀብ
- መገለል
- መድሎ

## 4.1.1 ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመዋጋት ዙሪያ የወጣቶች ሚና

በዓለም ከሚገኘው ሕዝብ ግማሽ የሚሆነው ዕድሜው ከ25 ዓመት በታች ነው። በኤች.አይ.ቪ. ከተያዙ ከ10 ሚሊዮን በላይ የሚደርሱ ወጣቶች ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 24 ዓመት ነው። በአፍሪካ ደግሞ ዕድሜያቸው ከ15-24 ዓመት የሚደርስ አራት ሚሊዮን ወጣት ሴቶች በቫይረሱ ተይዘዋል። በኢትዮጵያም በኤች.አይ.ቪ. ከተያዙት የኅብረተሰብ ክፍሎች አብዛኛዎቹ ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 24 ዓመት የሆኑ ወጣቶች ናቸው። በተለይም የወጣት ሴቶች ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ ጠለፋ፣ የሴት ልጅ ግርዛትና አስገድዶ መድፈር ሴቶች ለቫይረሱ ያላቸውን ተጋላጭነት ከፍተኛ ያደርገዋል።



ምስል 4.1 ቀዩ ሪቫን

የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስን ከደም ውስጥ የሚያጠፋ ወይም ኤድስን ፈጽሞ የሚያድን ክትባትም ሆነ ፈዋሽ መድኃኒት እስከዛሬ ድረስ አልተገኘም። ነገር ግን ቫይረሱ በደም ውስጥ ከገባ በኋላ በብዛት እንዳይራባ ወይንም የተፈጥሮ አቅምን በማዳከም ለሞት እንዳያደርስ የሚረዳ ፀረ ኤች.አይ.ቪ. መድኃኒት ተገኝቶለታል። ፀረ ኤች.አይ.ቪ. መድኃኒት ተጓዳኝ በሽታዎችን ለመከላከል፣ ሕመምን ለመቀነስና የተሻለ ሕይወት ለመምራት ያስችላል። ይህ መድኃኒት የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታት የሚያስችል ባለመሆኑ ቫይረሱ የሚያስከትለውን ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ተጽእኖ ዋነኛው ስልት መከላከል ነው። የኤች.አይ.ቪ./ ኤ.ድ.ስን ሥርጭት ለመግታት ሁሉም ዜጎች ይልቁንም ወጣቶች በሽታው የሚተላለፍበትን መንገድ ጠንቅቀው በማወቅና የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት ራሳቸውንና ኅብረተሰቡን ከቫይረሱ መከላከል ይጠበቅባቸዋል። ስለዚህም ወጣቶች ኤች.አይ.ቪ. የሚተላለፍባቸውን መንገዶች ለመከላከል የሚከተሉትን ሦስቱን የ **መ** ሕግጋት (መታቀብ፣ መወሰንና መጠቀም) ማወቅ ይጠበቅባቸዋል።

1. **መታቀብ፡-** ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከማድረግ መቆጠብ ለኤች.አይ.ቪ፣ ለተለያዩ የአባላዘር በሽታዎች፣ ላልተፈለገ እርግዝና እንዲሁም ከሥጋት ነጻ ያደርጋል። ስለዚህም ተማሪዎች ትምህርታቸውን አጠናቀው ትዳር እስኪመሠርቱ ድረስ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ታቅበው መኖር አለባቸው።
2. **መወሰን፡-** ዕድሜያቸው ለትዳር የደረሱ ተቃራኒ ጾታዎች ትዳር እስኪመሠርቱ ድረስ እንዲሁም በትዳር ያሉ ለፍቅረኛቸውና ለትዳር ጓደኛቸው ታማኝ በመሆን አንድ ለአንድ ተወስነው መኖራቸው አስደሳችና ጤናማ ግንኙነትን ለመፍጠር ያስችላል።
3. **መጠቀም፡-** የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲደረግ በተገቢው መንገድ ኮንዶም መጠቀም ያልታቀደ እርግዝናን፣ የአባላዘር በሽታና ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስን ለመከላከል ይረዳል።

### የሕይወት ክህሎትን ማሳደግ

ወጣቶች የሕይወት ክህሎትን በማዳበር የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ይችላሉ። የሕይወት ክህሎት ዓላማና ተግባር ወጣቶችን ከመጥፎ ተግባር ማዳንና በመልካም ሥነ ምግባር ጸንተው እንዲቆዩ ማስቻል ነው። የሕይወት ክህሎት ለዕለት ተዕለት ሕይወት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማሟላት፣ በየዕለቱ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት፣ ራስን ከአደጋ ለመከላከል፣ አመለካከትን ለመለወጥ፣ አቅምንና ብቃትን ለማሳደግ ይረዳል።

ወጣቶች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭትን ለመግታት በሚደረገው ትግል የበኩላቸውን ሚና መጫወት አለባቸው። ወጣቶች በኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ እንዳይያዙ የሚከተሉትን የሕይወት ክህሎት ማዳበር ይገባቸዋል።

- ራስን ማወቅ፣ ለራስ ክብር መስጠትና ለሌሎችም ክብር መስጠት ተገቢ መሆኑን መገንዘብ፣
- ከሰዎች ጋር መግባባት፣ ከሰዎች ጋር የሚደረጉ የእርስ በእርስ ግንኙነቶችን በማወቅ በመከባበርና በመቻቻል አብሮ የመኖር ልምድን ማዳበር፣
- በጾታና በዕድሜ አቻ የሚመጡ በጎ ያልሆኑ ተጽእኖዎች፣ ፈተናዎች ወይንም ተግዳሮቶች (Challenges) መቋቋምና ለፈተናዎች መከሰት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት መፍታትና ውሳኔ መስጠት፣
- ከተቃራኒ ጾታ ጋር የሚፈጠር ግንኙነት መደምደሚያን ከጊዜያዊ ስሜት ወጣ ብሎ አርቆ ማሰብ፣
- የውስጥ ስሜትን መቋቋም እንዲሁም ከሌሎች ጋር ስሜትን መጋራት፣
- በችግር፣ መከራንና ፈተናን መጋፈጥና መወጣት
- ጤናን ሊጎዱ ከሚችሉ ተግባራት መራቅ
- አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን በመገምገም ራስን ከአደጋ ማራቅ
- ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት በግል ሕይወት፣ በቤተሰብ ኑሮና በኅብረተሰብ ደረጃ የሚያስከትለውን የጤና፣ የሥነ ልቦና፣ የምጣኔ ሀብትና የማኅበረሰብ ቀውስ በመረዳት የመታቀብ መርህ ማዳበር
- ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያስከትለውን አደጋ መገንዘብ ናቸው።

በተጨማሪም ወጣቶች ጎጂ ወይም አሉታዊ ተግባራትን አስወግደው የሚከተሉትን ጤናማ ተግባራት ማዳበር አለባቸው።

- አዘውትሮ የአካል እንቅስቃሴ ማድረግ፣
- በቂና የተመጣጠነ ምግብ መብላት፣
- ራስን ከኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ እና ከሌሎች ተላላፊ በሽታዎች መከላከል፣
- የግልንና የአካባቢን ንጽሕና መጠበቅ፣
- ማናቸውንም ዓይነት ሱስ ከሚያስይዙ እንደ ሲጋራ፣ ሺሻ፣ አደንዛዥ ዕጽ፣ አልኮል የመሳሰሉት መራቅ፣
- በኅብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ድርጊት ከመፈጸም (ለምሳሌ ከቡድን ጸብ፣ በመንገድ ላይ ሴቶችንና አረጋውያንን ከመስደብ፣ ስርቆት፣ ከማጭበርበር፣ ከአሉባልታና ወላጆችንና ታላላቆችን ከማዋረድ) መቆጠብ ተገቢ ነው።

## የአቻ ግፊትን መቋቋም

- **በአቻዎቻችሁ ግፊት የፈጸማችሁትና የምታስታውሱትን ድርጊትና ውጤቱ ምን እንደነበር አንሥታችሁ ተወያዩ።**

ተማሪዎች የተለያየ ውሳኔ ላይ እንድትደርሱ የሚያስገድዷችሁ የተለያዩ ሁኔታዎች ሊያጋጥሟችሁ ይችላሉ። በተለይ የአቻ ግፊት ሲያጋጥም አስቀድሞ **ምን ማድረግ አለብኝ?** የሚል ውሳኔ የሚሻ የሕሊና ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። የአቻ ግፊት ሲያጋጥም በጉዳዩ ምንነት ላይ በጥልቀት ማሰብና ተያይዘው ሊመጡ የሚችሉ አደጋዎችን አስቀድሞ በማየት ተገቢ ውሳኔ ላይ መድረስ ያስፈልጋል።

አንዳንድ ጊዜ የዕድሜ አቻዎቻችሁ ያልተፈለጉ ወይም አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን እንድትቀበሉ ወይንም እንድትፈጽሙ ግፊት ሊያደርጉ ይችላሉ። ለምሳሌ፡-

- አልኮል እንድትጠጡ ሊጋብዟችሁ ወይም ሊያዋክቧችሁ ይችላሉ።
- የተለያየ አደንዛዥ ዕጽ እንድትጠቀሙ ሊጠይቋችሁ ወይም ሊያስገድዷችሁ ይፈልጋሉ።
- የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንድትፈጽሙ ሊያግባቧችሁ ወይም ሊያታልሏችሁ ይችላሉ።።

በአቻዎቻችሁ በትምህርታችሁ፣ በነገው ራዕያችሁ፣ በአካላችሁ፣ በሕይወታችሁ፣ በጤናችሁ ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ የተለያዩ ጥያቄዎች ወይም ግብዣዎች ሲቀርቡላችሁ በእርጋታ ማስተዋል የተሞላበት ውሳኔ በመወሰን ራሳችሁን ከማይጠቅም ቁጭትና ጸጸት ማዳን አለባችሁ። ዘወትር **አስተውሎ የሚራመድ ብዙ ርቀት እንደሚጓዝ** በማመን ከቤተሰባችሁ፣ በአካባቢያችሁ ጥሩ የሕይወት ተሞክሮ ካላቸው ሰዎችና ከመምህራን ጋር በገጠማችሁ ፈተና ላይ ያለምንም ፍርሐትና ይሉኝታ በግልጽ የመወያየት ልምድ እንዲሁም ያመናችሁበትን ጉዳይ በጽናት በመያዝ የአቻ ግፊትን የመቋቋም ችሎታ ማዳበር አለባችሁ። የተለያየ የሕይወት ክህሎት በማዳበር ዘወትር ራሳችሁን ከአቻ ግፊት ተጽእኖ ነጻ ማድረግ ይጠበቅባችኋል።

**ተማሪዎች ራዕይ ሊኖራቸው ይገባል።**

ተማሪዎች በሕይወታቸው ሊደርሱበት ወይም ሊያሳኩት የሚያልሙት ራዕይ ሊኖራቸው ይገባል። ራእይ ማስቀመጥ የሕይወት አቅጣጫን ለመለየትና ጊዜን፣ ሀብትንና ጉልበትን በተገቢ ተጠቅሞ ስኬታማ ሕይወት ለመምራት ያስችላል። ራዕይ የሌለው መድረሻውን አያውቅም። ሕይወቱን በዘፈቀደ ስለሚመራ ሕይወቱ ግራ የተጋባና በፍርሃት የተሞላ ነው። ተማሪዎች ከዚህ ችግር ለመውጣት ግልጽ ራዕይ ነድፎ ማስቀመጥ ተገቢ ነው።

ተማሪዎች ራዕያችሁን ለማሳካት እንቅፋት የሚሆኑ ብዙ ነገሮች ሊያገጥሟችሁ ይችላል። በሕይወታችሁ የሚገጥሟችሁን ፈተናዎች ተቋቁማችሁ ማለፍ ካልቻላችሁ ካሰባችሁበት መድረስ አትችሉም። ለምሳሌ፡-

- ራዕይን አጥብቆ አለመያዝ፣
- በተለያየ ሱስ መጠመድ፣
- ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም፣
- በአቻ ግፊት መሸነፍ፣
- ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ራዕያችሁ እንዳይሳካ ሊያደናቅፉ ይችላሉ።

የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ራዕይን ለማሳካት ይረዳሉ።

- ራዕይን በጽናት ለመወጣት መዘጋጀት፣
- ራዕይን ለማሳካት በጽናት መሥራት፣
- የመምህራንን፣ የወላጆችና የሌሎች ሰዎች ጠቃሚ ምክሮችን ማዳመጥና መተግበር፣
- ከመጥፎ ሱስና ልማድ መራቅ፣
- የጥናት፣ የሥራና የእረፍት ጊዜን በመወሰን በዕቅድ መመራት፣
- ተመሳሳይ ራዕይ ያላቸው ጓደኞችን መምረጥ፣
- የራዕይ ስኬትን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ነገሮችን መለየትና ሲያጋጥሙ እርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው።

## ኤች አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው የሚገኝ ወገኖችን መንከባከብ

የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው የሚገኝ ወገኖችና የኤድስ ሕሙማን ከቤተሰባቸውና ከማኅበረሰባቸው ጥላቻና መገለልን ሳይሆን ፍቅርንና ሥነ አዕምሯዊ ድጋፍን ሊያገኙ ይገባል። ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ላለባቸው ወገኖች የሚሰጥ ፍቅርና እንክብካቤ የመከላከያ ኃይላቸው በቶሎ እንዳይጎዳ አዎንታዊ አስተዋጽኦ አለው።

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ  በደማቸው ላለባቸው ወገኖች የሚሰጥ ፍቅርና እንክብካቤ ትልቅ ጥረትን ይጠይቃል፡፡ ይህንን ፍቅርና እንክብካቤ ለመስጠት ተማሪዎች፡-

1. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ካለባቸው ወገኖች ጋር በቂ ጊዜ ማሳለፍ አለባቸው፡፡
2. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ወገኖች ክብደታቸው እንዲጨምርና ከሕመማቸው እንዲያገግሙ የአመጋገብ ሁኔታቸውን፣ የመመገቢያ ሰዓታቸውን፣ የሚወዱትንና የማይወዱትን የምግብ ዓይነት በተመለከተ ማወያየት ያስፈልጋል፡፡
3. ገንቢ፣ ኃይል ሰጪና በሽታ ተከላካይ የተለያዩ ማዕድናትን የያዙ ምግቦችን በቀላሉ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ እንዲሁም በቀላሉ እንዴት የተመጣጠነ ምግብ ማዘጋጀት እንደሚችሉ ማስተማር ይችላሉ፡፡
4. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ወገኖች የተመጣጠነ ምግብ መመገባቸው የመከላከያ ኃይላቸው በፍጥነት እንዳይቀንስ ስለሚያደርግ በአንጻራዊ ረጅም ዕድሜ እንዲኖሩ ያግዛቸዋል፡፡ ስለዚህም ተማሪዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ወገኖች ለዚህ ጉዳይ እርዳታ ለመስጠት ከተቋቋሙ ድርጅቶች ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡
5. አዳዲስ የሕመም ምልክቶች በታዩ ቁጥር በወቅቱ ወደ ሐኪም በመሄድ የሕክምና እርዳታ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡
6. መልካም የጤና ሁኔታ ሲኖራቸው ቀላል የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንዲያርጉ መርዳት ያስፈልጋል፡፡
7. ብቻቸውን የሚኖሩ ወገኖችን በቂ ጊዜ ሰጥቶ ማጫወት ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች ሰዎች እንዲጐበኟቸውና አብረዋቸው እንዲጫወቱ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

## ማግለል ምንድ ነው?

ማግለል አንድን ሰው ወይም ማኅበረሰብ በሌሎች ፊት ዝቅ ተደርጎ የሚታይበት ሥነ አእምሮአዊና ማኅበራዊ ተጽእኖ ነው፡፡ ማግለል ከቆዳ ቀለም፣ ከብሔረሰባዊ ማንነት፣ ከቋንቋ፣ ከሙያ፣ ከጤና ሁኔታና፣ ከሰውነት አካላዊ ክፍሎች ጋር በተገናኝ የዝቅተኝነት ስሜት እንዲፈጠር የሚያደርግና አሉታዊ ተጽእኖ የሚያስከትል ደርጊት ነው፡፡

## አድሎ ምንድን ነው?

አድሎ ለሰዎች እኩል ወይም ተመሳሳይ መብት፣ ትኩረት፣ እንክብካቤና ድጋፍ በመስጠት ፋንታ አንድን ወገን ከሌላው አስበልጦ ወይም አሳንሶ በማየት የሚፈጠር ልዩነት ነው፡፡ በአድሎ የተነሣ አንዳንዶች ፖለቲካዊና ሰብአዊ መብታቸውን ተነፍገው ወይም ከሌሎች የተለዩ ተደርገው ፍትሐዊ ባልሆነ መንገድ ይስተናገዳሉ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ወገኖች በተለያዩ አካላት አድሎ ሲደርስባቸውና መብታቸው ሲጣስ ይስተዋላል፡፡ በሀገራችን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር በተያያዘ የሚደርሰውን የመገለልና የአድሎ ችግር ለመቅረፍ በመንግሥትና በፍትሕ አካላት በየደረጃው የሚወሰዱ ተግባራዊ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው፡፡

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ባለባቸው ወገኖች የሚደርሰውን አድሎና መድሎን ለማስወገድ የሃይማኖት አባቶች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወጣቶች፣ የፍትሕ አካላትና አጠቃላይ ኅብረተሰቡ ከመንግሥት ጎን መቆም አለባቸው፡፡ ይህም፡-

- ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ወገኖችን በራስ የመተማመን ብቃት ለመገንባት ያስችላል፡፡
- ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ወገኖች የሚደርስባቸውን ማኅበራዊ መገለል የሚቋቋሙበት ክህሎትን ያዳብራሉ፡፡

- የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ ይረዳል፡፡
- ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ወገኖች ሊኖራቸው የሚችለውን ማኅበራዊ ግንኙነት ለማስተካከል እገዛ ያደርጋል፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች 4.1.1**

***በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- *ኤች. አይ. ቪ./ ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ መንገዶችን ግለጹ፡፡*
- *ተማሪዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ወገኖችን ለመንከባከብ የምትችሉበትን መንገዶች ዘርዝሩ፡፡*
- *በአካባቢያችሁ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ባለባቸው ወገኖች ላይ የሚደርስ መገለልና አድሎ እንዴት መወገድ እንደሚችል ግለጹ፡፡*

## 4.1.2 ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን መቆጣጠሪያ ስልቶች

***ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት***

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- የሕዝብ ዕድገትን ሁኔታ በኢትዮጵያ ትተነትናላችሁ፡፡
- የሕዝብ ዕድገትን ለመግታት የተነደፉ ስልቶችን ትለያላችሁ፡፡
- የኢትዮጵያን የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ጠቀሜታንና የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ትደግፋላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ
- የወልደት መጠን
- የሞት መጠን
- ሥነ ሕዝብ

### ◈ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በኢትዮጵያ

እ.ኤ.አ በ1900 ዓ.ም. አካባቢ የኢዮጵያ ሕዝብ ብዛት 11.8 ሚሊዮን ነበረ፡፡ በዚያን ወቅት ዓመታዊ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጠን 0.2 በመቶ ነበር፡፡ ይህ የዕድገት መጠን ቢቀጥል ኖሮ የሕዝቡ ቁጥር በእጥፍ ለመጨመር 346 ዓመታት ይወስድ ነበር፡፡ ነገር ግን እ.ኤ.አ ከ1900 ዓ.ም. በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር በፍጥነት እያደገ በመምጣቱ በ60 ዓመት ውስጥ በእጥፍ ጨምሯል፡፡ በተጨማሪም እ.ኤ.አ ከ1960 ዓ.ም. እስከ 1990 ዓ.ም. በነበረው ሠላሳ ዓመት የሕዝቡ ቁጥር በሚያስገርም ፍጥነት እንደገና ጨምሯል፡፡ በዚህ የተነሣ እ.ኤ.አ ከ1970 ዓ.ም. ጀምሮ የሕዝብ ቁጥር በእጥፍ የሚጨምርበት ጊዜ ወደ 24 ዓመት ወርዷል፡፡ የሕዝብ ቁጥር በእጥፍ የሚጨምርበትን ጊዜ የሚወስነው የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጠን ነው፡፡

እ.ኤ.አ በ1984 ዓ.ም. በተደረገው የመጀመሪያ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ መሠረት ኢትዮጵያ በአጠቃላይ 40.07 ሚሊዮን ሕዝብ ነበራት፡፡ እ.ኤ.አ በ1994 ዓ.ም. በተደረገው ሁለተኛው የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ደግሞ አጠቃላይ የሕዝቡ ብዛት 53.48 ሚሊዮን ሕዝብ ደርሶ ነበር፡፡ እ.ኤ.አ ከ1984 ዓ.ም. እስከ 1994 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ የሕዝቡ

ቁጥር በዓመት 2.9 በመቶ ዕድገት አሳይቶአል:: የሕዝቡ ብዛት በአሥር ዓመት ውስጥ 13.4 ሚሊዮን ሕዝብ ጨምሮአል::

**የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን የሚወስኑት የውልደት መጠን፣ የኅልፈተ ሕይወት መጠን እና የፍልሰት መጠን ናቸው::**

- **በወሊድ መጠንና በኅልፈተ ሕይወት መጠን መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**

***ውልደት መጠን:-*** ማለት ከአንዲት ሴት በሕይወት የሚወለዱ የሕጻናት ቁጥር ነው::

***የኅልፈተ ሕይወት መጠን:-*** ማለት ከአንድ ሺህ ሰው መካከል በዓመት ውስጥ በሞት የሚለየው ሰው መጠን ነው::

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የውልደት መጠን ከሚያስመዘግቡ ሀገር አንዷ ናት:: እ.ኢ.አ በ1984 ዓ.ም. በእያንዳንዷ ሴት የነበረው አጠቃላይ የውልደት መጠን 7.52 የነበረ ሲሆን እ.ኢ.አ በ1994 ዓ.ም. ደግሞ ወደ 6.74 ወርዷል:: በከተማና በገጠር የሚታየው የውልደት መጠን የተለያየ ነው:: በተመሳሳይ ሁኔታ በዓለም ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሞት መጠን ከሚታይባቸው ሀገራት ኢትዮጵያ አንዷ ናት:: የኅልፈተ ሕይወት መጠን በጣም ከፍተኛ ሊሆን የቻለው በሕዝቡ ድህነትና ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የተነሣ ነው:: ይህ ሁኔታ በተደጋጋሚ በሚከሰተው ድርቅና ረኃብ ምክንያት እየጨመረ መጥቷል:: የፍልሰት መጠን በኢትዮጵያ የሕዝብ ዕድገት ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ አነስተኛ ነው:: ምክንያቱም የሕዝቡ እንቅስቃሴ ዝቅተኛ በመሆኑ የተነሣ ነው::

## ◈ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ በኢትዮጵያ

- **ሥነ ሕዝብ ምንድን ነው?**
- **የሥነ - ሕዝብ ፖሊሲ ዓይነቶችን ዘርዝሩ::**

ሥነ ሕዝብ በአንድ በታወቀ ቦታ የሚኖር ሕዝብ የተለያዩ ገጽታዎች(ብዛት፣ የጾታና የዕድሜ ቅንብር፣ የዕድገት ምጣኔና መልክአ ምድራዊ ሥርጭት) ከማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እንዲሁም ለኑሮ አስፈላጊ ከሆኑ ሀብቶች አንጻር የሚጠናበት የዕውቀት ዘርፍ ነው::

የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ የምጣኔ ሀብት፣ የማኅበራዊና የሥነ ሕዝብ ገጽታዎችን ማለትም የሕዝቡን ብዛት፣ የጾታና የዕድሜ ቅንብር፣ አሠፋፈርና የዕድገት ምጣኔን ለመለወጥ የሚወሰድ እንዲሁም የሥነ ሕዝብ ገጽታዎች በሕዝቡ ኑሮና በሀብት አጠቃቀም ላይ የሚያሳድረውን ጫና ለመቀነስ የአንድ ሀገር ፍላጎት የሚገለጽበትና መወሰድ ያለበት የመፍትሔ እርምጃ የሚገለጽበት ሀገራዊ ሰነድ ነው:: የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ በሕዝብ ብዛትና በተፈጥሮ ሀብቶች መካከል ጤናማ ግንኙነት ለመፍጠር የሚጠቅም መመሪያ ነው:: ይህም በሕዝብ ብዛትና በምጣኔ ሀብት መካከል ሚዛናዊ ዕድገት ለማምጣት ይረዳል:: የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ የአንድ ሀገር የዕድገት አቅጣጫን ለመቀየስ፣ በሕዝብ ብዛትና በምጣኔ ሀብት መካከል ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነት እንዲሁም የሕዝብ ቁጥርን ዕድገት በተመለከተ መወሰድ ስላለበት እርምጃ መረጃ ይሰጣል::

## ◈ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ዓይነቶች

በዓለም ላይ ሁለት ዓይነት የሥነ ሕዝብ ፖሊሲዎች አሉ:: እነርሱም:-

- ውልደትን የሚያበረታታ፣
- ውልደትን የማያበረታታ ተብለው ይከፈላሉ::

***ሥነተዋልዶን የሚያበረታታ ፖሊሲ:-*** የሚነደፈው የሕዝብ ብዛት ዕድገትን ለመጨመር ሲታሰብ ነው::

***ሥነተዋልዶን የማያበረታታ ፖሊሲ:-*** የሕዝብ ብዛትን ለመቀነስ ታስቦ የሚወጣ ፖሊሲ ነው::

የኢትዮጵያ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ውልደትን የማያበረታታ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ምሳሌ ነው። ኢትዮጵያ የምትታወቀው በፈጣን የሕዝብ ብዛት ዕድገት መጠን ነው። ዛሬ ሀገሪቱ በዓለም ላይ የሕዝብ ብዛታቸው እጅግ በጣም ፈጣን በሆነ መንገድ በመለወጥ ላይ ከሚገኙት መካከል አንዷ ናት። የሕዝብ ብዛት ዕድገት መጠን እ.ኤ.አ በ1900 ዓ.ም. ከነበረው 0.2 በመቶ እ.ኤ.አ በ1999 ዓ.ም ወደ 2.9 በመቶ አድጓል።

### የኢትዮጵያ የሥነ ሕዝብ ሁኔታ

- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት፣
- አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል በወጣትነት ዕድሜ ክልል የሚገኝበት ሁኔታ፣
- ያልተመጣጣነ የሕዝብ ሥርጭት ዐበይት መገለጫዎቹ ናቸው።

### የኢትዮጵ የሥነ ሕዝብ ባሕርይ

1. በበርካታ የሀገሪቷ አካባቢዎች የምግብ ዋስትና እጥረት መኖር
2. መሠረታዊ ማኅበራዊ አገልግሎቶች አሰጣጥ ዝቅተኛ መሆን ለምሳሌ የትምህርት፣ የጤናና የመኖሪያ ቤት አቅርቦት የመሳሰሉት
3. የተለያዩ ዘርፎች ምጣኔ ሀብታዊ ምርታማነት ዝቅተኛ መሆን
4. የአንድ ሰው አማካይ የመኖር ዕድሜ ዝቅተኛ መሆን
5. የእናቶችና የሕጻናት ሞት ከፍተኛ መሆን ሀገሪቱ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ እንድታወጣ አስገዳጅ ሁኔታ ፈጥሯል።

- የኢትዮጵያ የሥነ-ሕዝብ ፖሲሲ አጠቃላይ ዓላማዎች ምንድናቸው?

### የኢትዮጵያ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ አጠቃላይ ዓላማዎች

- የምጣኔ ሀብት ግንባታውን በማጠናከር የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔን በዕቅድ በመቀነስ በሕዝብ ቁጥር ዕድገትና በዝቅተኛ ምጣኔ ሀብት መካከል ያለውን ልዩነት ማስወገድ፣
- በተቀናጀ የልማት መርሐ ግብር አማካኝነት የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴውን ማስፋፋት፣ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ማድረግ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበራዊ ልማትን ማፋጠን፣
- ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን የሕዝብ ፍልሰት መጠን መቀነስ፤
- የአካባቢ ጥበቃንና እንክብካቤን የሚያጠናክሩ ተገቢ እርምጃዎችን በመውሰድ በተለይ የገጠሩ አካባቢ ሰዎችን የማኖር አቅሙ እንዲጠበቅ ወይንም እንዲሻሻል ማድረግ፣
- ሴቶችን ከባህላዊ ተጽእኖዎች፣ ከከባድና አሰልቺ ሥራዎች በማላቀቅና በማኅበረሰቡ ውስጥ ምርታማ ሆነው እንዲሳተፉ በማድረግ ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበራዊ ደረጃቸውን ከፍ ማድረግ
- የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ማለትም የሴቶችን፣ የወጣቶችን፣ የሕጻናትንና የአዛውንቶችን ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ማድረግ ናቸው።

### ◈ ፈጣን የሕዝብ ብዛት ዕድገትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የማስፈጸሚያ ስልቶች

#### በኢትዮጵያ ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ላይ የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀምጠዋል።

1. ከመንግሥትና ከግል በሚገኝ የሀብት ድጋፍ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ሥርጭት በክሊኒኮችና በቤት ለቤት ዕደላ ጭምር ማስፋፋት፣
2. የሕጻናትን የአመጋገብ ችግር ለማስተካከል የጡት ማጥባት ዘዴ መጠቀም እንዲሁም ከእርግዝና በፊት ያለውን ጊዜ በትምህርት፣ መረጃ በመስጠትና፣ ግንኙነት በማጠናከር እንዲራዘም ማድረግ።
3. የሴቶች የጋብቻ ዕድሜ 18 ዓመትና ከዚያም ከፍ ያለ እንዲሆን ማድረግ፤
4. የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ማሳደግ

5. ሴቶች በምጣኔ ሀብትና በማኅበራዊ ልማት ዘርፍ ተሳትፏቸውን እንዲያጎለብቱ መርዳት
6. ተማሪዎች በተለይም ልጃገረጆች ተስማሚ የሆነ ሥራ እንዲመርጡ በሁለተኛ ደረጃና ከዚያም በላይ ባለው የትምህርት ተቋም የምክር አገልግሎች መስጠት፤
7. የሥነ ሕዝብና የቤተሰብ ኑሮ ትምህርት በመደበኛውና መደበኛ ባልሆነው የትምህርት ዘርፍ ተካቶ እንዲሰጥ ማድረግ፤
8. ሥነ ተዋልዶ ጤናን በተመለከተ የወጣቶች የምክር አገልግሎት የሚያገኙባቸው ማዕከላት እንዲመሠረቱ ማድረግ፤
9. በሥነ ተዋልዶ ጤና ዙሪያ የምርምር መርሐ ግብር ማመቻቸት፤
10. የሥነ ሕዝብ መርሐ ግብሮችን በተለይም ወንዶች በቤተሰብ ምጣኔ ጉዳይ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ፤
11. በዘመናዊው ምጣኔ ሀብት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ የሚጨምርበትን ሁኔታ ማመቻቸትና የረጅም ጊዜ ፖሊሲ መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ፤
12. የሥነ ሕዝብ መረጃዎችንና ትምህርት በመገናኛ ብዙኃን፣ በፖስተር፣ በበራሪ ወረቀቶችና በሌሎች ዘዴዎች ወደ ኅብረተሰቡ የሚደርስበትን መንገድ ማመቻቸት፡፡

## በኢትዮጵያ የሥነ ሕዝብና ድህነት ቅነሳ ፖሊሲዎች ላይ የወጣቱ ሚና

በኢትዮጵያ የተከሠተው ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት በአካባቢ ላይ ተጽእኖ አስከትሏል፡፡ የምግብ አቅርቦትና የሕዝብ ብዛት ስላልተጣጣሙ ችግሩ ጎልቶ ይታያል፡፡

ከማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ጋር ያልተገናዘበ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በኅብረተሰቡ አጠቃላይ የኑሮ ደረጃ፣ የጤንነት ሁኔታና የጤና አገልግሎት ሽፋን፣ በትምህርት ሥርዓትና ጥራት፣ በሥራ ዕድል፣ በመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት በሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ስለዚህም መንግሥት ምጣኔ ሀብታዊና ማኅበራዊ ልማትን ያስቀደመ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ አውጥቷል፡፡ መንግሥት ያወጣው የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ዐቢይ ግብ የሕዝብ ዕድገት ምጣኔንና የሀገሪቷን የተፈጥሮ ሀብቶች የአጠቃቀም ስልት በማጣጣም የሕዝቡን የኑሮ ደረጃና ደኅንነት ማሻሻል ነው፡፡

የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጠንን ለመቆጣጠር የቤተሰብ ምጣኔና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ሥርዓት ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ነገር ግን አሁን ያለው የአገልግሎት ሥርጭት በስፋትም ሆነ በዓይነት እያደገ ነው፡፡ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት በመደበኛ የጤና ተቋማትና በጤና ባለሙያዎች የቤት ለቤት አገልግሎት በወረዳዎችና በቀበሌዎች እየተሰጠ ነው፡፡ ስለዚህ የሥርጭት ሽፋኑን ለማስፋፋትና የተለያዩ የመከላከያ ዘዴዎችን ለተገልጋዮች ለማቅረብ ወጣቱ ወሳኝ ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ ወጣቱ የሚከተሉትን እርምጃዎች በመውሰድ ለሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ዓላማዎች ተግባራዊነት ይንቀሳቀሳል፡፡

1. ቤት ለቤት በሚደረግ የወሊድ መከላከያ ዘዴዎች ዕደላ ይሳተፋል፡፡
2. ጋብቻን ልደትንና ሞትን በመሳሰሉ ዋና ዋና ክስተቶች ምዝገባ ላይ ይሳተፋል፡፡
3. በአንዳንድ ወረዳዎችና ቀበሌዎች እንዲሁም በብዙ ትምህርት ቤቶች በተቋቋሙ የሥነ ሕዝብ ክበባት አማካኝነት የቤተሰብ ምጣኔን አስፈላጊነትና ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በልማት ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽእኖ አስመልክቶ ለኅብረተሰቡ ትምህርት በመስጠት ይሳተፋል፡፡
4. ጤናማ አወላለድን በተመለከተ ወጣቶችን በምክር የሚረዳ የወጣቶች የምክር አገልግሎት ማዕከላት በመመሥረትና ከተመሠረተም በኋላ በንቃት በመሳተፍ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

ከምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የመጀመሪያው ከዓለም ላይ ድህነትንና የረሃብን መስፋፋት መቀነስ ነው፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ መንግሥት ድህነትን ለመቀነስ ያወጣቸውን መመሪያዎችና መርሐ ግብራት ተግባራዊነት ወጣቶች በተግባር የሚገለጽና የሚጨበጥ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

ወጣቶች ለዕድገት በመተባበርና በጽኑ ዓላማ በመደራጀት ሀገሪቱን ከምትገኝበት የድህነት አዘቅት ማውጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ሥራን ሳይንቁ በተፈጠረላቸው የሥራ ዕድል ሁሉ ተጠቅመው ራሳቸውንና አገራቸውን ከድህነት ለማላቀቅ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንዲሁም ራሳቸውን ከተረጂነት ስሜት በማላቀቅ የሥራ ፍቅርን በማዳበር ድህነትን በጽኑ ታግለው ለመጣል በቁርጠኝነት መነሣት አለባቸው፡፡

## ውስን ጥናት

### የቻይና የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ

የእስያ አኅጉር ዓመታዊ የሕዝብ መጠን ዕድገት 1.3 በመቶ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአኅጉሩ በየዓመቱ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ይመዘገባል፡፡ አንዳንድ ሀገራት የሕዝብ ቁጥር ምጣኔ መቀነስን ዐቢይ ተግባር አድርገው መንቀሳቀስ ጀምረዋል፡፡ እ.አ.አ በ1970ዎቹ ዓ.ም. ገደማ የቻይና የሕዝብ ቁጥር በአስደንጋጭ መጠን በመጨመሩ መንግሥት የወሊድ ምጣኔን የልማት መርሐ ግብሩ ዋና አካል በማድረግ ቻይና ያላትን ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለመቀነስ ውልደትን የማያበረታታ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ነድፋለች፡፡ ይህ ፖሊሲ ተግባራዊ በመደረጉ በሕዝብ ቁጥር ምጣኔ ላይ ጉልህ ለውጥ ታይቷል፡፡

ቻይናውያን እ.አ.አ ከ1979 ዓ.ም. ጀምሮ አንድ ቤተሰብ አንድ ልጅ ብቻ እንዲኖረው የሚያበረታታውን የቤተሰብ ምጣኔ ፖሊሲን (one child policy) ተግባራዊ በማድረጋቸው የተነሣ ባለፉት ሁለት አሥርተ ዓመታት ከ300 ሚሊዮን በላይ የሚደርሱ ሕጻናት ሳይጸነሱ ቀርተዋል፡፡ ይህም የቻይና የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እንዳያሻቅብ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከዓለም ሕዝብ ሃያ በመቶው በቻይና የሚገኝ ሲሆን የቻይና ጠቅላላ የሕዝብ ብዛት ከ1.3 ቢሊዮን በላይ እንደሆነ ይገመታል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች 4.1.2

*ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥየቄዎች*

- እ.አ.አ ከ1984 ዓ.ም. እስከ 1994 ዓ.ም. ባለው ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዕድገት መጠን ምን ይመስል ነበረ?
- በኢትዮጵያ ዋና ዋናዎቹን የሞት ምክንያቶች ግለጹ፡፡

*ለ. የሚሠሩ ተግባራት*

- በአካባቢያችሁ የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ካለ ፖሊሲው ያመጣውን ጥቅምና ያስከተለውን ችግር በመጠየቅ ያገኛችሁትን መረጃ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማቅረብ ተወያዩበት፡፡

## 4.2 ሰብአዊ መብቶችና ደኅንነት

***ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት***

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- በጾታና በሥርዓተ ጾታ መካከል ያለውን ልዩነት ትለያላችሁ፡፡
- የጾታ እኩልነትን ገጽታዎችን ትለያላችሁ፡፡
- ወጣቶች የጾታ እኩልነትን በማስፋፋት ረገድ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ ታደንቃላችሁ፡፡
- በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በምሳሌ በማቅረብ ትወያያላችሁ፡፡
- የሴቶችን ተሳትፎ በማሳደግና በጋራ በመሥራት ድህነትን የመቀነስ ጠቀሜታ ታረጋግጣላችሁ፡፡
- የወጣት ጥፋተኝነትን በምሳሌ ትገልጻላችሁ፡፡
- ወጣት ጥፋተኝነትን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ትገልጻላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ ስላለው የወጣት ጥፋተኝነት ማስታወሻ ትጽፋላችሁ፡፡

### ቁልፍ ቃላት

- ሥርዓተ ጾታ
- የወጣት ጥፋተኝነት
- ሥልጣን መስጠት
- ድህነትን መቀነስ

### ◈ ሥርዓተ ጾታ

- **የጾታና ሥርዓተ ጾታ ልዩነት ምንድን ነው?**
- **የጾታ እኩልነትን ማረጋገጫ ስልቶች ዘርዝሩ፡፡**

***ጾታ*** የሚለው ቃል የሚገልጸው የወንዶችና የሴቶችን ሥነ ሕይወታዊ ልዩነት ነው፡፡
***ሥርዓተ ጾታ*** የሚለው ሐረግ ደግሞ ወንዶችና ሴቶች በማኅበራዊ ሕይወታቸው ጾታቸውን መሠረት በማድረግ እንዲያከናውኑ የተሰጣቸው ማኅበረሰባዊ የሥራ ወይንም የሚና ክፍፍል ነው፡፡

በሌላ በኩል **ወንድ** ወይም **ሴት** ስንል ጾታን ለመግለጽ እንዲሁም **ተባዕታይ** ወይም **አንስታይ** ስንል ደግሞ ሥርዐተ ጾታን የሚመለከት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በተለያዩ ሀገራትና በተለያየ ኅብረተሰብ መካከል የጾታ ሚና ልዩነት የለውም፡፡ ነገር ግን የሥርዓተ ጾታ ክፍፍል ከአካባቢ አካባቢ እንዲሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡

### የጾታ ልዩነት

- ሴቶች የወር አበባ ሲኖራቸው፣ ወንዶች ግን የላቸውም፡፡
- ሴቶች ይጸንሳሉ፣ ወንዶች ግን አይጸንሱም፡፡
- ሴቶች ወተት የሚያወጡ ትልልቅ ጡቶች አሏቸው፤ ወንዶች ግን የዚያ ዓይነት ጡት የላቸውም፡፡
- ወንዶች በተፈጥሮአቸው ከሴቶች የበለጠ ትላልቅ አጥንቶች አሏቸው፡፡

### የሥርዓተ ጾታ ልዩነት

- በዩናይትድ ስቴትስ እና በሌሎችም ሀገሮች ሴቶችና ወንዶች ለተመሳሳይ ሥራ የሚከፈላቸው ክፍያ እኩል አይደለም፡፡
- በቬትናም ብዙ ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ሲጋራ ያጨሳሉ፡፡
- በሳውዲ አረቢያ ለወንዶች መኪና መንዳት የተፈቀደ ሲሆን ለሴቶች ግን አይፈቀድም፡፡
- በብዙ የዓለም ሀገሮች አብዛኛውን የቤት ውስጥ ሥራ የሚሠሩት ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ናቸው፡፡
- በኢትዮጵያ ሴቶች በቤት ውስጥ ልጅ እንዲያሳድጉ የሚጠበቅ ሲሆን ለወንዶች ግን እንደነውር ይቆጠራል

### በኢትዮጵያ የሥርዓተ ጾታ እኩልነት

- የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ምንድን ነው?
- በወንዶችና በሴቶች መካከል እንዴት እኩልነት ሲሰፍን ይችላል;

የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ሲባል በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ እኩልነት ነው፡፡ የሥርዓተ ጾታ እኩልነት በጾታ ላይ የተመሠረተ እድሎን ማስወገድ ማለት ነው፡፡ ወንዶችና ሴቶች የተፈጠሩት እኩል በመሆኑ በእኩልነት ሊታዩ ይገባል፡፡ በሀገራችን የቆየ ልማድ ሴቶች ከወንዶች እኩል አይታዩም ነበር፡፡ ሴቶች በተለያዩ መንገዶች የሚገባቸውን መብቶችና ዕድሎች ሳያገኙ ቆይተዋል፡፡ ሴቶች ከወንዶች እኩል የመማር ዕድል፣ የንብረት ባለቤት የመሆን መብት፣ የፖለቲካና የአስተዳደር ሥልጣን የመያዝ መብትና የውሳኔ ሰጪነት ዕድል አልነበራቸውም፡፡ ይህ ልዩነት ደግሞ ሴቶችን ብቻ ሳይሆን ኅብረተሰቡን የሚጎዱ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ ሴቶች ባይማሩ የሕጻናት እንክብካቤና የመላው ቤተሰብ የጤና ሁኔታ ከፍተኛ አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ ሴቶች በምርት ተግባር ላይ ካልተሳተፉ ግማሽ የሚሆነው የኅብረተሰብ የሥራ ኃይል ይባክናል፡፡ ስለዚህ የሥርዓተ ጾታ እኩልነት የችሮታ ጥያቄ ሳይሆን የመብትና የልማት ጥያቄ በመሆኑ ሴቶች ከወንዶች እኩል መብቶቻቸው ሊከበሩላቸው ይገባል፡፡ የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ለሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝ በመሆኑ ሴቶች በፖለቲካ፣ በምጣኔ ሀብት፣ በሀገር ልማትና በጸጥታ ጉዳዮች ሁሉ እኩል ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

- በወንዶችና በሴቶች መካከል እኩልነትን ለማረጋገጥ ምን መደረግ አለበት?

በ1987 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 35 የሚከተሉትን መብቶች ለሴቶች አጐናጽፏል፡፡

- የሴቶች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ከወንዶች እኩል ይከበራሉ፡፡
- በሥነ ሕይወታዊ አፈጣጠር ምክንያት ሴቶች የተለዩ መብቶች ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ልጅ ከመውለዳቸውና ከወለዱም በኋላ የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ ደሞዝ ጋር ያገኛሉ፡፡
- ሴቶች በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ በሚዘጋጁ ፖሊሲዎች ላይ የመካፈልና ውሳኔ የመስጠት መብት አላቸው፡፡
- ሴቶች ከወንዶች እኩል የንብረት ባለቤት የመሆንና የማስተዳደር መብት አላቸው፡፡
- ሴቶች ከጋብቻ በፊት፣ በጋብቻ ወቅትና ከጋብቻ በኋላ ከወንዶች እኩል መብት አላቸው፡፡
- ሴቶች ከማንኛውም ጐጂ ድርጊቶች የመጠበቅ መብት አላቸው፡፡

የሴቶችን መብት በተመለከተ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍና በብሔራዊ ደረጃ ንቁ ተሳትፎ አድርጋለች፡፡ የሴቶችን መብቶች የሚያስጠብቁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ድንጋጌዎችን ተቀብላ በሥራ ላይ አውላለች፡፡ ኢትዮጵያ በሴቶች ላይ የሚፈጸመውን አድሎ የሚያስወግድ ስምምነት እና የቤይጂንግን ስምምነት (***Beijing Declaration of the Fourth World Conference on Women*** **and Plan of Action**) ተቀብላ አጽድቃለች፡፡

**የሴቶች ጉዳይ ስምምነት** ሴቶችን ከሁሉም ዓይነት አድልዎና መንገላታት የሚከላከሉ በርካታ ሕጎችን በጽሑፍ አሥፍሯል፡፡
**የቤይጂንግ ስምምነት** በሴቶች ጉዳይ ስምምነትና በሌሎች ስምምነቶች ውስጥ የተካተቱትን የሴቶችን መብቶችና ደኅንነት ተግባራዊ የሚያደርግ ስልት ነድፎ አዘጋጅቷል፡፡

- በኢትዮጵያ ያለ ዕድሜ ጋብቻ መፈጸም የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽእና ግለጹ፡፡
- በቤተሰብ ጉዳይ ላይ አባትና እናት የሚኖራቸውን መብት በተመለከተ ተወያዩ፡፡

ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሰኔ 28 ቀን 1992 ዓ.ም የጸደቀው አዲስ የተሻሻለው የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ለሥርዓተ ጾታ እኩልነት ተገቢ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት የጋብቻ ዝቅተኛ ዕድሜ 18 ዓመት ሆኖአል፡፡ ከዚያ በፊት ግን ሴቶች በ15 ዓመት ወንዶች ደግሞ በ18 ዓመት ዕድሜያቸው ማግባት ይችሉ ነበር፡፡ በአብዛኛው የኢትዮጵያ አካባቢ ሴቶች ያለ ዕድሜያቸውና ያለ ፍላጎታቸው እንደሚያገቡ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ይህ ሁኔታ በሴቶች ትምህርት፣ ጤና እንዲሁም ሰብእና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አለው፡፡ ይህ ሁኔታ በገጠር አካባቢ በስፋት የተለመደ ነው፡፡ ያለ ዕድሜ ጋብቻ ብሎም በልጅነት እናት መሆን በኢትዮጵያ ለሚታየው ከፍተኛ የእናቶች ሞት ዋና ምክንያት ነው፡፡

ኢ.ፌ.ዲ.ሪ በ1952 ዓ.ም. በወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግ የቤተሰብ መሪነትና የሕጻናት ጠባቂነት ወይም አሳዳጊነት መብት የተሰጠው ለአባት ነበር፡፡ ነገር ግን በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ለባልና ሚስትም እኩል መብት ተሰጥቷቸዋል፡፡ በባለትዳሮች መካከል ፍች ወይም መለያየት በሚያጋጥምበት ወቅት ሕጻናት ዕድሜያቸው አምስት ዓመት እስኪሞላ ድረስ ከእናታቸው ጋር እንዲቆዩ ተደንግጓል፡፡

- የሴት ልጅ ግርዛት የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው?
- የሴት ልጅን ግርዛት የሚያስከትለውን ከባድ ጉዳት እንዴት ለወላጆቻቹ ማስረዳት እንደምትችሉ ተወያዩ፡፡

**የሴት ልጅ ግርዛት በመፈጸም አካላዊ ጉዳት ማድረስ፡-** በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛት በስፋት የተለመደ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ነው፡፡ የሴት ልጅ ግርዛት ወይም የብልት ትልተላ የሴቶችን የውጭ ብልት በከፊል ወይንም በሙሉ ቆርጦ በመጣል የሚከናወን አስከፊ ድርጊት ነው፡፡ የሴት ልጅ ግርዛት ደም መፍሰስን፣ ጠባሳን፣ በወሊድ ጊዜ ምጥ መራዘምን እንዲሁም በመራቢያ አካላት፣ በጤናና በሥነ አእምሮ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ በርካታ ሴቶች የዚህ አስከፊ ድርጊት ሰለባ ሆነዋል፡፡ ይህ ድርጊት የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው፡፡ በአዲሱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይህንን ተግባር ሲፈጽም የተገኘ ሰው ከሦስት ወራት በማያንስ ጊዜ በእሥራት ሊቀጣ ወይንም አምስት መቶ ብር የገንዘብ መቀጫ እንደሚከፍል ተደንግጓል፡፡

## ድህነትን ለመቀነስ በጋራ መሥራት

- የድህነት መገለጫዎችን በዝርዝር ጻፉ፡፡

ድህነት ቅነሳ ማለት ቢያንስ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ማሟላት ማለት ነው፡፡ ድህነት መሠረታዊ ፍላጎቶችን ማሟላት አለመቻል ነው፡፡ የማይምነት መስፋፋት፣ የማኅበራዊ አገልግሎቶች ማነስ፣ የመሠረተ ልማት በበቂ ሁኔታ ያለመኖር የመሳሰሉት የድህነት መገለጫዎች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ከሚገኙ ድሀ ሀገሮች አንዷ ናት፡፡ በርካታ ዜጎች ማንበብና መጻፍ አይችሉም፡፡ ለቴክኖሎጂ ቅርበት ስለሌላቸው አሠራራቸው ኋላ ቀርና የሚፈለገውን ያህል ውጤታማ አይደለም፡፡ የማኅበራዊ አገልግሎቶች ሽፋን ዝቅተኛ ነው፡፡ ግብርናው በዝናብ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በተደጋጋሚ በሚደርሰው ድርቅ ምክንያት ሕዝቡ ለረኃብ፣ ለስደትና ለሞት ሲጋለጥ ቆይቷል፡፡ ስለዚህ የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብት ለማሳደግና ይህንን አስከፊ ሁኔታ ለመለወጥ ሁሉም ዜጎች በተለይም ወጣቶች በቁርጠኝነት ድህነትን ለመዋጋት በጋራ የመሥራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

### ሴቶችን ስለልጣን ማብቃት፣ የቤት ውስጥ ግጭቶችንና በደሎችን ማስወገድ

በሴቶች ለሥልጣን መብቃት የቤተሰብ አባላት ጤናን በመጠበቅ፣ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱ የሕጻናት ቁጥርን በመጨመርና የእርሻ ምርታማነት በማሻሻል የኅብረተሰቡ ተጠቃሚነት ይረጋገጣል፡፡ ይህ ደግሞ ድህነትን ለማጥፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

እ.ኢ.ት.አ ከ1983 ዓ.ም. በፊት በሀገራችን የነበረው የመንግሥት ሥርዓት ሴቶችን ለሥልጣን ለማብቃት የተደረገው ጥረት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነበር፡፡ እ.ኢ.ት.አ በ1987 ዓ.ም. ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተደረገው ምርጫ የተመረጡት ሴቶች ቁጥር 14 ሲሆን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የተመረጡት ደግሞ 8 ሴቶች ብቻ ነበሩ፡፡ እ.ኢ.ት.አ በ1983 ዓ.ም የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ሲመሠረት በካቢኔው ውስጥ ሁለት ሴቶች በሚኒስትርነት ሲሾሙ፣ በ1987 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሲመሠረት ደግሞ ከ18 የካቢኔ አባላት ውስጥ አምስት ሴቶች ተሾመዋል፡፡ በተጨማሪም አራት ሴቶች በአምባሰደርነት ደረጃ ተሾመዋል፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት በምርጫና በሹመት በተለያዩ ከፍተኛ ደረጃዎች ላይ በውሳኔ ሰጪነት የተቀመጡ ሴቶች ቁጥር 130 ያህል ደርሷል፡፡

ሴቶች ከሚገጥሟቸው ችግሮችም ሆነ ከሙያቸው አንጻር በመደራጀት የተለያዩ የሙያ ማኅበራትን አቋቁመዋል፡፡ ለዚህም የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር የተቋቋመው እ.ኢ.ት.አ ግንቦት 30 ቀን 1987 ዓ.ም. ነበር፡፡ ይህ ማኅበር ዋና ትኩረቱ ሴቶች በሕግ ፊት የሚደርስባቸውን ችግርና ጫና እየተከታተለ፣ በተለይ ችግረኛ ለሆኑ ሴቶች ሕጋዊ የምክር አገልግሎት በመስጠትና ጥብቅና በመቆም ያለምንም ክፍያ ሙያዊ ድጋፍ መስጠት ነው፡፡ በተጨማሪም ሴቶች በቤት ውስጥ በወንዶች (በባል፣ በጓደኛ፣ በአሠሪዎች፣ ወዘተ) የሚደርስባቸውን በደልና የአካል ጉዳት እንዲሁም ለወሲብ የሚገደዱበትን ሁኔታ ማጋለጥና ለኅብረተሰቡ ማሳወቅ ነው፡፡

ማኅበሩ በሴቶች ላይ የሚፈጸምን የኃይል ጥቃት ለማስወገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ማለት ማንኛውም ጾታን መሠረት በማድረግ በማኅበራዊም ሆነ በግል ሕይወታቸው ላይ አካላዊ፣ ወሲባዊ ወይም ሥነ አእምሮአዊ ጉዳት ወይም ስቃይ ሊያስከትል የሚችል ተግባር ነው፡፡ በተጨማሪም በሴቶች ላይ የሚሰነዘር ዛቻ፣ ማስፈራሪያ፣ የማስገደድ ተግባር ወይም አላግባብ ነጻነትን የሚገፍ ተግባር ሁሉ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡

**ውስን ጥናት**

**ወይዘሮ ሙሉ እመቤት እምሩ**

ወይዘሮ ሙሉ እመቤት እምሩ ምንም እንኳን በንግድ አውሮኘላን አብራሪነት ባይሠለጥኑም በኢትዮጵያ ይልቁንም በአፍሪካ የመጀመሪያዋ ሴት አውሮኘላን አብራሪ ናቸው፡፡


የመጀመሪያዋ አውሮኘላን ወደ ኢትዮጵያ ስትገባ ወይዘሮ ሙሉ እመቤት ትንሽ ልጅ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ነገሮችን ለማወቅ የሚጥሩና መንፈሰ ጠንካራ ሴት ስለነበሩ በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንኳንስ ስለ አውሮኘላን ቀርቶ ስለመኪናም በቂ ግንዛቤ ባልነበረበት ወቅት እ.ኢ.ት.አ በ1926 ዓ.ም. በአሥራ ስድስት ዓመታቸው ኢትዮጵያዊው ኮሎኔል ዕቁባይና ጥቁሩ አሜሪካዊው ኮሎኔል ሮቢንስን በሰጧቸው ሥልጠና አውሮኘላን ማብረር ችለዋል፡፡

ወይዘሮ ሙሉ እመቤት ለበረራ የሠለጠኑባት አውሮፕላን "Tiger Moth" በመባል ትታወቃለች፡፡ ወይዘሮ መሉ እመቤት በየሳምንቱ ከአሠልጣኞቻቸው ጋር በአዲስ አበባ ዙሪያ የበረራ ልምምድ ያደርጉ ነበር፡፡ ከአንድ ዓመት በኋላ ግን ያለረዳት ብቻቸውን መብረር ችለዋል፡፡ ይህም በሕዝብ ዘንድ አድናቆትን አትርፎላቸዋል፡፡ ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ሲወር የአውሮፕላን በረራውን በማቋረጥ ትዳር በመያዛቸውና ቤተሰብ በመመሥረታቸው በሙያው አልገፉበትም፡፡

## ሴቶች በአርአያነት

### ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ (ታዋቂ ሴት አርበኛ)

ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ በአማራ ብሔራዊ ክልል በሚገኘው በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ብርሃን ከተማ እ.ኢ.ት.አ በ1878 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ እ.ኢ.ት.አ በ1928 ዓ.ም ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ ከወንድ አርበኞች ጐን በመሰለፍ ታላቅ የጀግንነት ሥራ አከናውነዋል፡፡ በወቅቱ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ወርዶ የኢጣሊያን ባንዲራ ሲውለበለብ አይተው በማልቀሳቸው ታስረው ብዙ ግፍ ደርሶባቸዋል፡፡ ከተለቀቁም በኋላ እ.ኢ.ት.አ በ1932 ዓ.ም በአዲስ ዓለም ከተማ የፋሺስት ምሽግ እንዲሰበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡



*ምስል 4.2 ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ*

### ዶክተር ውዳድ ኪዳነማርያም (በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት ሐኪም)

**(እ.ኢ.ት.አ ከ1928 እስከ 1980 ዓ.ም)** በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት ሐኪም ሲሆኑ በማኅፀን ሕክምና ሙያ ልዩ ትምህርት ከወሰዱ በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው በጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል ከአሥር ዓመታት በላይ አገልግለዋል፡፡

### ክብርት ዶክተር ወይዘሮ አበበች ጎበና (በኢትዮጵያ ሀገር በቀል የበጎ አድራጎት ድርጅት ያቋቋሙ ሴት)

**ብሩህ ተስፋ** ብለው በሠየሙት የበጎ አድራጎት ድርጅት አማካኝነት ከውጭ እርዳታ በማግኘት ወላጆቻቸውን ያጡ ሕጻናትን ሰብስበው ከማሳደጋቸውም በላይ ሌሎች ልጆችን ደግሞ የምግብና የሕክምና አገልግሎት እየሰጡ በተመላላሽነት በማስተማር ለሀገር ግንባታ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ዜጎችን አፍርተዋል፡፡



*ምስል 4.3 ክብርት ዶክተር ወይዘሮ አበበች ጐበና*

### ወይዘሮ ብርነሽ አስፋው (በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት መሐንዲስ)

በ1956 ዓ.ም. ትምህርታቸውን ከአዲስ አበባ መሐንዲስ ኰሌጅ በማጠናቀቅ በቀድሞው የአውራ ጐዳና ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ተቀጥረው ለአንድ ዓመት በልዩ ልዩ ክፍሎች የሙያ ሥልጠና ሲሰጣቸው ከቆዩ

በኋላ በሠርቬይና በዲዛይን ክፍል የአንድ ቡድን ኃላፊ ሆነው በመመደብ የመንገድና የፍሳሽ ዲዛይን ሥራ ጀመሩ። ከዚያም በኋላ በተከታታይ ሙያቸው በሚፈቅድላቸው ቦታ ሁሉ በዋና ኃላፊነት አገልግለዋል።

### የሴቶችን ትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ የሚረዱ የማስፈጸሚያ ስልቶች

- በአብዛኛው ሴቶች በገጠር የሚኖሩ በመሆናቸው በገጠሩና ትምህርት ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች ትምህርት ቤቶችን መክፈት ሴቶች ልጆችንም ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ ወላጆችን መቀስቀስ ተገቢ ይሆናል።
- በሕይወታቸው ላይ ለውጥ ሊያመጣ የሚያስችል የሕይወት ክህሎት ትምህርት እንዲጨብጡ ማበረታታት።
- በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችና የሙያ መስኮች ሴቶች የሚበረታቱበትን መንገድ ማመቻቸት።
- በክፍል ውስጥ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግ።
- ሴት ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚሰጡ ኃላፊነቶችን እንዲወስዱ ማድረግ።
- በትምህርት ቤትና በክፍል ውስጥ በሚደረጉ ውይይቶች የቡድን ሥራዎች ሁለቱም ጾታዎች ያለፍርሃት እዲሳተፉ ማበረታታት።
- በትምህርት አመራርና በሌሎችም የኃላፊነት ቦታዎች ሴቶች እንዲሳተፉና በኃላፊነት ቦታ እንዲመደቡ ዕድሉን መክፈት ሴቶች የመማርን ጠቀሜታ እዲገነዘቡ ያስችላል።
- ራሳቸውን የሚያሻሽሉባቸውን ስልጠናዎች ማካሔድ።

**የክለሳ ጥያቄዎች 4.2**

**ክንውን ሀ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- በጾታ እና በሥርዓተጾታ መካከል ያለውን ልዩነት ግለጹ።
- የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ምንነትን አብራሩ።
- እ.ኢ.ት.አ በ1987 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ለይ ለሴቶች ከተሰጡ መብቶች ጥቂቶቹን ጻፉ ።
- አዲስ በተሻሻለው በኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ለሴቶች የተሰጡ ዋና ዋና መብቶችን ዘርዝሩ።
- የድህነት ቅነሳ ምንነትን ግለጹ።

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- በአካባቢያችሁ በሥርዓተ ጾታ ላይ በመመሥረት የወንድና የሴት ተብለው የተለዩ ተግባራትን በመለየት እንዴት ይህንን ልማዳዊ የሥራ ክፍፍል መለወጥ እንደምትችሉ ተወያዩ።

## ◈ ከአደጋ መራቅ

- ወጣት ጥፋተኛነት ማለት ምን ማለት ነው?

በዘመናችን በወጣቶች ላይ የተለያዩ አደጋዎች ተደቅነዋል። በጥባጭነት፣ ሱሰኝነት፣ ሥነ ምግባር አልባነትና አስገድዶ መድፈር የመሳሰሉትን የወንጀል ድርጊቶች የሚፈጽሙ ወጣቶች ወጣት ጥፋተኛ ይባላሉ።

በከተማ ከሚከሰቱ ማኅበራዊ ችግሮች አንዱ የወጣት አጥፊነት ነው፡፡ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት ያላለፈ ወጣቶች ወንጀል ፈጽመው ሲገኙ በወጣት አጥፊነት ይመደባሉ፡፡ በወጣት ጥፋተኞች ላይ የሚወሰደውም የሕግ እርምጃ ከአዋቂዎች የተለየ ነው፡፡ በሀገራችን የወጣት አጥፊነት የኅብረተሰቡን ትኩረት መሳብ የጀመረው ከዛሬ ሃምሳ ዓመት በፊት ነው፡፡

ስርቆት፣ ድብድብ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ጠለፋ፣ ቁማር፣ ጫት መቃም፣ ሲጋራ ማጨስ፣ መዋሸት፣ ማስፈራራት፣ ማንጓጠጥ፣ ማፌዝ፣ መሳደብ፣ የቡድን ጸብና ሌሎችም የወጣት አጥፊዎች በስፋት ከሚፈጽሟቸው የወንጀል ድርጊቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

## የወጣት አጥፊነት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

የወጣት አጥፊዎች የተለያዩ የጥፋት ድርጊቶችን የሚፈጽሙት ከሰብእና (personality) አለመስተካከል የተነሣ ነው፡፡ ለወጣት ጥፋተኝነት መስፋፋት የቤተሰብ መፍረስ፣ የአሳዳጊዎች የአያያዝ ችግር፣ አስቸጋሪ ማኅበራዊ አካባቢ፣ በትምህርት ቤት በቡድን የሚፈጠር ጸብ፣ የአደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚነት፣ በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት የሚተላለፉ መልእክቶች፣ ድህነት፣ የከተማና የኢንዱስትሪ መስፋፋት በምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

## የወጣት አጥፊነት መገለጫዎች

ከትምህርት ቤት አዘወትሮ መቅረት፣ ጸያፍ ንግግር ወይም ቃላትን መጠቀም፣ ቤተሰብና ማኅበረሰብ የሚሰጠውን ደንብ መጣስ፣ የትምህርት ቤትን ሕግ መተላለፍ፣ ሰዎችን መተናኮልና በቁጣ ማናገር፣ ትምህርት ማቋረጥ፣ ሰዎችን ሆን ብሎ ማበሳጨትና በሰዎች ማፌዝ፣ልመና፣ የጎዳና ኑሮ የመሳሰሉት የወጣት ጥፋተኝነት መገለጫዎች ናቸው፡፡

## የወጣት ጥፋተኝነትን መከላከል

የወጣት ጥፋተኝነትን ችግር ለመቅረፍ ወላጅ፣ ትምህርት ቤት፣ ኅብረተሰቡና መንግሥት በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ ወጣት ጥፋተኞች ያሉበትን ሁኔታ በማጥናት ማኅበራዊ አካባቢያቸውን መለወጥ ወጣት ጥፋተኝነትን ለመከላከል ከሚወሰዱ እርምጃዎች አንዱ ነው፡፡ በተጨማሪም ወጣት ጥፋተኞችን ለማረም የሚወጣን ሕግ ከሕጻናት መብት ስምምነት ጋር በማጣጣም ጥፋተኛ ወጣቶች የሚታረሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ ነው፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች የሚፈጸሙ የወጣቶች ጥፋት የተለያዩ በመሆናቸው እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የወጣት ጥፋተኝነትን ምንነት በግልጽ ማስገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ለማዳበር በትምህርት ቤቶች የሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ክበብ ወሳኝ ሚና መጫወት ይችላል፡፡

በወጣቶች ላይ የሚታየውን ጥፋት ለማረም ጭካኔ በተሞላበት መንገድ ከመቅጣት ይልቅ ለአጥፊዎቹ ያሉበትን አደገኛ ሁኔታ በማሳየት ከአደጋው እንዲወጡ መርዳቱ ተገቢ ነው፡፡ አጥፊ ወጣቶችን ከችግር ለማውጣት በትምህርት ቤት የምክርና የአመራር አገልግሎት ባለሙያዎች እንዲሁም በመምህራንና በኅበዝ ተማሪዎች ጾታንና አጥፊዎቹ ያሉበትን የዕድሜና የብስለት ደረጃ መሠረት ያደረገ የምክርና የተሐድሶ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡

በወላጆችና በትምህርት ቤቶች መካከል የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር ኅብረተሰቡ በተማሪዎች ሥነ ምግባር ዙሪያ ተገቢውን ክትትል እንዲያደርግ ማበረታታት፣ ስለጸታ ትምህርት በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ ወጣቶች የዕረፍት ጊዜያቸውን በተገቢ ሁኔታ የሚያሳልፉበት ሁኔታ መፍጠር፣ በችግሮቻቸው ዙሪያ የምክር አገልግሎት

መስጠት፣ የትምህርት ቤቶችን ሁኔታ መለወጥና ማስተካከል የወጣት አጥፊነትን ለመቀነስ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

## ውስን ጥናት

### የአስገድዶ መድፈር ወንጀል

አንዲት ታዳጊ ሴት ልጅ የምትጠብቃቸው አህዮች ጠፍተውባት በፍለጋ ላይ እንዳለች ከሳር ክምር ሥር ተደብቆ የነበረ አንድ ጎረምሳ በድንገት ይይዛታል፡፡ ልጅቷ እንዳትጮህ አፏን በጨርቅ አፍኖ በመያዝ አስገድዶ ይደፍራታል፡፡ ከዚያም ሜዳ ላይ እንደወደቀች በጨርቅ ሸፍኖ ጥሏት ከአካባቢው ይሠወራል፡፡

በመጨረሻም ታዳጊዋ ሕጻን በወደቀችበት አካባቢ የሚያልፉ ሰዎች የምታሰማውን የሲቃ ድምጽ ሰምተው ሊያነሷት ሲሞክሩ ሰውነቷ በደም ተነክሯል፡፡ ከዚያም የአካባቢውን ነዋሪዎች ርዳታ በመጠየቅ ወደ ቤተሰቦቿ ያደርሷታል፡፡ ቤተሰቦቿም ጉዳዩን ለፓሊስ በማሳወቅ በፍርድ ቤት ክስ ሊመሠርቱ ችለዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በዋለው ችሎት የአሥር ዓመቷን ሕጻን አስገድዶ በመድፈር የተከሰሰው ግለሰብ ጥፋተኝነቱ በመረጃ ስላረጋገጠ በ18 ዓመት እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች 4.2

**ክንውን ለ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- የወጣት ጥፋተኝነት መገለጫዎችን ግለጹ፡፡
- ወላጆች ወጣት ጥፋተኝነትን ለመከላከል ምን ማድረግ ይገባቸዋል?
- ትምህርት ቤቶች ወጣት ጥፋተኝነትን ለመከላከል ምን ማድረግ ይገባቸዋል?
- ወጣት ጥፋተኛን ለማረም መወሰድ ስላለበት እርምጃ ግለጹ፡፡

***ለ. የሚሠሩ ተግባራት***

- በውስን ጥናት በቀረበው ታሪክ ላይ የአስገድዶ መደፈር ጥቃት የደረሰባት አዳጊዋ ሕጻን ከማኅበራዊ ሕይወት፣ ከጤና፣ ከአካላዊ ጉዳት አንጻር ሊያጋጥማት የሚችለውን ችግር በማንሣት ተወያዩበት፡፡ በመጨረሻም ሕጻናት አስገድዶ የመድፈር ጥቃት እንዳይደርስባቸው መውሰድ ስላለባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች በዝርዝር በመወያየት ድርጊቱን የሚያወግዝ የጋራ የአቋም መግለጫ አዘጋጁ፡፡

## 4.3 የአጋርነት መርሐ ግብር

*ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:-**

- የተመድን ጠቀሜታና መተዳደሪያ ደንቦች ታብራራላችሁ፡፡
- የተመድን ዋና ዋና አካላትና ሥራቸውን ትለያላችሁ፡፡
- የዓለም አቀፋዊነት ትስስር ሐሳብን ታስረዳላችሁ፡፡
- ለንግድ፣ ለባህልና መረጃ የተፈጠሩ ጥሩ አጋጣሚዎችንና የታወቁ ችግሮችን ትገልጻላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ዓለም አቀፋዊነት
- ድምፅን በድምፅ መሻር

### ◈ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት

- ተመድ መቼ፣ የትና ለምን ተቋቋመ?
- የተመድ ዋና ዋና አካላትን አወቃቀርና ተግባር ግለጹ፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ የተመሠረተው የቀድሞውን የዓለም መንግሥታት ማኅበርን(League of Nations) ለመተካት ታስቦ ነው፡፡ እ.ኢ.ት.አ ከሚያዚያ 17 እስከ ሰኔ 26 ቀን 1937 ዓ.ም. በሰሜን አሜሪካ በሚገኘው በሳን ፍራንሲስኮ ከተማ በተደረገው ጉባኤ የሃምሳ ሀገሮች ተወካዮች በተገኙበት ለድርጅቱ ምሥረታና አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያገለግል መተዳደሪያ ደንብ (Charter) ተዘጋጀ፡፡ እ.ኢ.ት.አ ጥቅምት 16 ቀን 1937 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በይፋ ተመሠረተ፡፡ ይህ ቀን የተባበሩት መንግሥታት ቀን እየተባለ በየዓመቱ ይከበራል፡፡

**የተባበሩት መንግሥታት ዓላማዎች:-**

- ዓለም አቀፍ ሰላምና ደኅንነትን ማስከበር፣
- በመንግሥታት መካከል የወዳጅነት ግንኙነቶችን ማዳበር፣
- ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማኅበራዊና ባሕላዊ ችግሮችን ለመፍታት ትብብር ማድረግ
- ሰብዓዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነጻነቶችን እንዲከበሩ ማድረግ ናቸው፡፡

**የተባበሩት መንግሥታት ዋና ዋና መርሆዎች**

- የመላውን አባል ሀገሮች ሉዓላዊነት መጠበቅ፣
- አባል ሀገሮች ለድርጅቱ ያለባቸውን ግዴታ በታማኝነት እንዲወጡ ማድረግ፣
- አባል ሀገሮች ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱና ከማንኛውም ዓይነት ማስፈራራት ወይንም የኃይል እርምጃ እንዲቆጠቡ ማድረግ፣
- አባል ሀገሮች ማንኛውንም ዓይነት ዕርዳታ ለተባበሩት መንግሥታት እንጂ በጦርነት ላይ ለሚገኙ ሀገሮች ዕርዳታ ከመስጠት እንዲቆጠቡ ማድረግ፣
- በማንኛውም አባል ሀገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት የሚገኘው በሰሜን አሜሪካ ኒው ዮርክ ከተማ ነው፡፡ የድርጅቱን ውሳኔዎች ለመቀበል ፈቃደኛ የሆነና በቻርተሩ ላይ የሠፈሩትን ግዴታዎች ተቀብሎ ተግባራዊ ለማድረግ የተስማማ ማንኛውም ሰላም ወዳድ ሀገር የድርጅቱ አባል ሊሆን ይችላል፡፡



*ምሥል 4.4 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት በኒውዮርክ*

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሚከተሉት አካላት አሉት፡-

- ✓ ጠቅላላ ጉባኤ
- ✓ የጸጥታው ምክር ቤት
- ✓ ዋና ጽሕፈት ቤት
- ✓ የምጣኔ ሀብትና የማኅበራዊ ምክር ቤት
- ✓ የሞግዚት አስተዳደር ምክር ቤት
- ✓ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት

## ጠቅላላ ጉባኤ

- የተ.መ.ድ. ጠቅላላ ጉባኤ ኃላፊነት ምንድን ነው?

ጠቅላላ ጉባኤ ሁሉንም አባል ሀገሮች የያዘ የድርጅቱ ከፍተኛ አካል ነው፡፡ ጉባኤው በየዓመቱ ከመስከረም እስከ ታኅሣሥ አጋማሽ በኒው ዮርክ እንዲሁም ሌሎች አስቸኳይ ጉዳዮች ሲከሰቱ ይሰበሰባል፡፡ በጉባኤው እያንዳንዱ አባል ሀገር አንድ ድምፅ አለው፡፡ ዓለም አቀፍ ሕግጋትንና መመሪያዎችን ያወጣል፡፡ ጉባኤው በአባል ሀገራት መካከል ምጣኔ ሀብታዊ ትብብር እንዲሰፍን እንዲሁም የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ እንዲጎለብት ያበረታታል፡፡ ኢትዮጵያም ድርጅቱ ከተመሠረተበት የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤ ጀምሮ በአባልነት ተሳታፊ ናት፡፡



*ምስል 4.5 የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ*

## የጸጥታ ምክር ቤት

- ድምፅን በድምፅ መሻር ማለት ምን ማለት ነው?

የጸጥታ ምክር ቤት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከፍተኛው አካል ነው። የምክር ቤቱ ተቀዳሚ ተግባርና ኃላፊነት ዓለም አቀፍ ሰላምና ደኅንነትን ማስጠበቅ ነው። በምክር ቤቱ አምስት ቋሚ አባል ሀገራት ይገኛሉ። እነርሱም ብሪታኒያ፣ ሩሲያ፣ አሜሪካ፣ ፈረንሳይና ቻይና ናቸው። የምክር ቤቱ ቋሚ አባል ሀገራት በምክር ቤቱ የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ወይም ለውሳኔ የተሰጠ ድምፅን በድምፅ የመሻር መብት (Veto power) አላቸው። ይህም ማለት በሁሉም ቋሚ አባላት ድጋፍ ያላገኘ ውሳኔ ሊተላለፍ አይችልም ማለት ነው።
በምክር ቤቱ በየሁለት ዓመቱ የሚመረጡ ቋሚ አባል ያልሆኑ 15 ሀገራት በአባልነት ይሳተፋሉ። ቋሚ ያልሆኑ የምክር ቤት አባላት ድምፅን በድምፅ የመሻር መብት የላቸውም።

በጸጥታው ምክር ቤት ሥር የሚገኙ ወኪል ድርጅቶች የሚከተሉት ናቸው:-

- **የከፍተኛ ወታደራዊ አዛዦች ኮሚቴ:-** ይህ ኮሚቴ ዓለም አቀፍ ሰላም ለማስጠበቅ ወታደራዊ ኃይል እንዴት መጠቀም እንደሚቻል የጸጥታውን ምክር ቤት ያማክራል።
- **የጦር መሣሪያ ቅነሳ ኮሚሽን:-** የጦር መሣሪያዎችን አጠቃቀም ሥርዓት ለማስያዝና እንዲቀነሱ ለማድረግ፣ እንዲሁም የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎችን ጨርሶ ለማስወገድ ዕቅድ ያወጣል።

የጸጥታው ምክር ቤት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊን አመራረጥና ደርጅቱን ለመቀላቀል ጥያቄ የሚያቀርቡ ሀገራትን የመቀበል ሁኔታዎችን ይቆጣጠራል። በተጨማሪም ግጭትና ብጥብጥ በተነሡባቸው አካባቢዎች ያለውን ችግር የሚያጣራ ኮሚሽን የመላክ ሥልጣን አለው።



*ምስል 4.6 በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ስብሰባ*

## ዋናው ጽሕፈት ቤት


ዋናው ጽሕፈት ቤት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊን ጨምሮ ከተለያዩ አባል ሀገሮች የተወጣጡ 15,000 ሠራተኞች አሉት፡፡ ዋናው መሥሪያ ቤት የሚገኘው ኒው ዮርክ ከተማ ሲሆን ሌሎች የተባበሩት መንግሥታት ማዕከላት በጄኔቭ (ስዊዘርላንድ)እና በቪየና (ኦስትሪያ) ከተሞች ይገኛሉ፡፡

## የዋናው ጽሕፈት ቤት ዋና ዋና ተግባራት

- የጠቅላላ ጉባኤውንና ልዩ ልዩ ምክር ቤቶችን ውሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣
- በጣም አሳሳቢ የሆኑ ጉዳዮችን ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣
- የድርጅቱን ዓመታዊ ሪፖርት ያዘጋጃል፣
- የተለያዩ ወኪል ድርጅቶችን ሥራ ያስተባብራል፡፡

የድርጅቱ ዋና ጸሐፊ በጸጥታው ምክር ቤት አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባኤው ለአምስት ዓመት ይሾማል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.1 የተመድ ዋና  ጸሐፊዎች እ.አ.አ ከ1946 ዓ.ም. እስከ 2011 ዓ.ም.**

| የዋና ጸሐፊዎች ሥም | የዋና ጸሐፊዎች ሀገር | የዋና ጸሐፊዎች የአገልገሉት ዘመን እ.አ.አ |
|---|---|---|
| ትሪጊቭ ሳይ |  ኖርዌይ | 1946-1953 እ.አ.አ |
| ዳግ ሐመርሾልድ |  ስዊድን | 1953-1961 እ.አ.አ |
| ኡ ታንት |  በርማ | 1961-1971 እ.አ.አ |
| ኩርት ቫልድሐይም |  ኦስትሪያ | 1972-1981 እ.አ.አ |
| ፔሬዝ ደ ኩየር |  ፔሩ | 1982-1991 እ.አ.አ |
| ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ |  ግብጽ | 1992-1996 እ.አ.አ |
| ኮፊ አናን |  ጋና | 1997-2007 እ.አ.አ |
| ባን - ኪ- ሙን |  ደቡብ ኮሪያ | 2008 እ.አ.አ |

### የምጣኔ ሀብትና ማኅበራዊ ምክር ቤት

ይህ ምክር ቤት የሚመረጠው በጠቅላላ ጉባኤ ሲሆን ቆይታውም ለሦስት ዓመታት ጊዜ ነው፡፡ በማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ሰብአዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ውይይት በማካሄድ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፡፡

### የተመድ ልዩ ልዩ አካላት

- ዓለም አቀፍ የሠራተኛ ድርጅት (ILO)
- የምግብና የእርሻ ድርጅት (FAO)
- የዓለም ጤና ድርጅት (WHO)
- በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (UNESCO) እና ሌሎችም፡፡

የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት በአዲስ አበባ ከተማ ዓለም አቀፍ የአቅም ግንባታ ተቋም አቋቁሟል፡፡

### የሞግዚት አስተዳደር ምክር ቤት

ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማብቂያ በኋላ (እ.አ.አ. ከ1945 ዓ.ም.) በጦርነቱ የተሸነፋት የኢጣሊያና የጃፓን ቅኝ ግዛቶች በሙሉ ባለ አደራ ግዛቶች ተብለው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የበላይ ተቆጣጣሪነት ሥር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

የሞግዚት አስተዳደር ምክር ቤት ግዛቶችን የሚያስተዳድሩ ሀገሮች በግዛታቸው የሚኖረው ሕዝብ የራሱን አስተዳደር እንዲመሠርት ለማዘጋጀትና የሞግዚት አስተዳደር ምክር ቤቱን የበላይ ተቆጣጣሪነት ለመቀበል ቃል ገብተዋል፡፡

በሞግዚት አስተዳደር ምክር ቤት በአባልነት የሚገኙት የአደራ ግዛት ያሏቸውና የሌሏቸው ሀገሮች ቁጥር እኩል ነው፡፡ ውሳኔ የሚተላለፈው በአባላት ድምፅ ብልጫ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ የሚገኙ ሀገሮች በሙሉ ነጻነታቸውን በማግኘታቸው ይህ አካል ምንም ሥራ የለውም፡፡

### ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት

ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጡ 15 ዳኞችን ይይዛል፡፡ ዳኞች የሚመረጡት ባላቸው ችሎታ እንጂ ዜግነታቸው ታይቶ አይደለም፡፡ ነገር ግን ከአንድ ሀገር ሁለት ዳኞች ሊመረጡ አይችሉም፡፡ የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መቀመጫ ኔዘርላንድ በሚገኘው ዘ ሔግ ከተማ ነው፡፡ ዳኝነት የሚሰጠው በድምፅ ብልጫ ነው፡፡ በመንግሥታት መካከል የሚነሱ ግጭቶችን የመፍታት ሥልጣን አለው፡፡ በተለያዩ የሕግ ጥያቄዎች ዙሪያ የተባበሩት መንግሥታት አካላትን ያማክራል፡፡

ሀገራት ማንኛውንም ዓይነት የግጭት ጉዳይ ለፍርድ ቤቱ ሲያቀርቡ የሚሠጣቸውን ውሳኔ ለመቀበል አስቀድመው በመስማማት ነው፡፡

| የክለሳ ጥያቄዎች 4.3 |
|---|
| **ክንውን ሀ**<br>***በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***<br>• የፀጥታው ምክር ቤት ተግባራት ምን ምን ናቸው?<br>• የዋናው ጽሕፈት ቤት ተግባር ምንድነው?<br>• የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የመጀመሪያው ዋና ፀሐፊ ማን ነበሩ?<br>• የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ተግባራት ምን ምን ናቸው?<br>• የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ልዩ ልዩ ወኪል መሥሪያ ቤቶችን ተግባራት አብራሩ፡፡ |

## ◈ ዓለም አቀፋዊነት (Globalization)

- ዓለም አቀፋዊነት ማለት ምን ማለት ነው?

### የዓለም አቀፋዊነት ጽንሰ ሐሳብ

ዓለም አቀፋዊነት የሚለውን ቃል በተለያዩ መንገዶች መግለጽ ይቻላል፡፡ ዓለም አቀፋዊነት በግለሰቦች፣ በሕዝቦችና በሀገሮች መካከል እያደገ የመጣውን ግንኙነቶች ይመለከታል፡፡ አስደናቂ የሆነ የመረጃ፣ የባሕል፣ የምጣኔ ሀብትና ቴክኖሎጂ ልውውጥና መጋራትን ይመለከታል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በሕዝቦች መካከል የተጠናከረ መደጋገፍን ያስከትላል፡፡

### የምጣኔ ሀብት ዓለምአቀፋዊነት

የዓለም አቀፋዊነት ነጸብራቅ የሆኑ በርካታ ተቋማት ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሁለቱም የገንዘብ ተቋማት በብዙ የዓለም ሀገሮች የጋራ ፖሊሲዎችን ዕድገት ያመቻቻሉ፡፡

### ለንግድ፣ ለባህልና ለመረጃ ልውውጥ የተፈጠሩ ጥሩ አጋጣሚዎችና ተግዳሮቶች(Challenges)

ዓለም አቀፋዊነት የሸቀጣ ሸቀጦችን፣ የካፒታልን፣ የአልግሎትና የሠራተኛን ፍሰት ለማመቻቸት ይረዳ ዘንድ በሀገሮች ድንበሮች ላይ ያለውን እገዳ ያነሣል፡፡ ካለፉት ሃምሳ ዓመታት ወዲህ በዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት በዓለም አቀፍ ንግድ ተጥሎ የነበረው ገደብ ዝቅ ተደርጓል፡፡ ባለፉት ጥቂት አሥርተ ዓመታት በተለያዩ ሀገሮች ግዙፍ የንግድ ሥራዎች በመመሥረታቸው ምክንያት የዓለም አቀፍ የምጣኔ ሀብት አቅጣጫ ሊለወጥ ችሏል፡፡

በተለያዩ ሀገሮች የንግድ ሥራ የሚሠሩ ኩባንያዎች «የብዙ ሀገሮች ማኅበራት» (Multinational Corporations) በመባል ይታወቃሉ፡፡ የዓለም አቀፍ የንግድ ማኅበራት ዋነኛ ተግባር የንግድ ሥራውን ባለቤትነት፣ ሥራ አመራር፣ ምርትና ሽያጭ ወደ ተለያዩ የዓለም ሀገሮች ማስፋፋት ነው፡፡ የኮካ ኮላ እና የጄኔራል ሞተርስ ኩባንያዎች እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ዛሬ ወደ 35,000 የሚሆኑ በየሀገሩ የሚሠሩ ድርጅቶች በዓለም ላይ ተሠራጭተው ይገኛሉ፡፡ 80 በመቶ የሚሆነው የዓለም የንግድ ሥራ የሚንቀሳቀሰው በብዙ ሀገሮች ማኅበራት ሠራተኞች አማካኝነት ነው፡፡

### ባሕላዊ ዓለም አቀፋዊነት

ከምጣኔ ሀብታዊ ዓለም አቀፋዊነት ጐን ለጐን ባሕላዊ ዓለም አቀፋዊነት ይገኛል፡፡ የባሕላዊ ዓለምአቀፋዊነት ስፋት የሚለካው በምዕራባውያኑ የመዝናኛ ተግባራትና የመገናኛ ብዙኀን በሚጫወቱት ሚና ነው፡፡ ይህን ሁኔታ የምዕራባውያን በተለይም የአሜሪካውያንን ባሕል ለማስፋፋት የሚደረግ የባሕል ወረራ ተጽእኖ እንደ ሆነ የሚያስቡ ወገኖች አሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በሌላው የዓለም ክፍል ላይ የምዕራባውያንን የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ የአነጋገር፣ የኪነ ጥበብና የሥነ ጥበብ፣ ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ባህላዊና መንፈሳዊ ባህል ለማስፋፋት የሚደረግ የባሕል ወረራ እንደሆነ በማሰብ የተለያዩ ሀገራት ማንነታቸውንና ባሕላቸውን ለመጠበቅ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል **አካባቢያዊ ባሕልን ዓለም አቀፋዊ፣ ዓለም አቀፋዊ ባሕልን አካባቢያዊ** (localizing the globe or globalizing the local) የሚለውን መርሕ የሚያራምዱ ወገኖች የዓለም ሕዝብ ተመሳሳይ ባሕል እንዲኖረው ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው፡፡ ዓለማችን በዓለም አቀፋዊነት ሂደት ባሕላቸውን፣ ማንነታቸውና እምነታቸው ሳይለወጥ መቀጠል በሚፈልጉና ለሕዝቦች መቀራረብና ለዓለም አንድ መሆን ተመሳሳይ ባሕልና እምነት ያስፈልጋል በሚሉ ወገኖች እንቅስቃሴ ተወጥራለች፡፡

### የዓለም አቀፋዊነት ውጤቶች

በተለያዩ ተቋማት እየተካሄዱ ያሉት የዓለም አቀፋዊነት መመሪያዎች ለደሀ ሀገሮች በጣም ጠቃሚ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ የደሀ ሀገሮች ምጣኔ ሀብትና ኢንዱስትሪ ያላደገ በመሆኑ በበለፀጉት ሀገሮች ምጣኔ ሀብትና ኢንዱስትሪዎች በቀላሉ ሊዋጡ ይችላሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በግልጽ የሚያሳየው በኢንዱስትሪ የበለፀጉ ሀገሮች የኢንዱስትሪ ምርቶችና የባሕል ውጤት በደሀ ሀገሮች በብዛት መገኘታቸውን ነው፡፡ እ.አ.አ ከ1955 ዓ.ም. ወዲህ በዓለም አቀፍ ንግድ ላይ ከፋብሪካ ተመርተው የሚወጡ ቁሳቁሶች መጠን ከመቶ እጥፍ በላይ ጨምሯል፡፡ እ.አ.አ ከ2000 ዓ.ም. እስከ 2007 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ብቻ ቻይና ከአፍሪካ ሀገሮች ጋር የምታደርገው የንግድ ልውውጥ በሰባት እጅ አድጓል፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች 4.3**

**ክንውን ለ**

***ሀ. በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎች***

- የዓለም አቀፋዊነትን ምንነት ግለጹ፡፡
- የዓለም አቀፋዊነትን መገለጫዎች ዘርዝሩ፡፡
- የዓለም አቀፍ ገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክን ዓላማዎች አብራሩ፡፡
- የዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅቶች (ኩባንያዎች) ምሳሌዎችን ስጡ፡፡

***ለ.የሚሠሩ ተግባራት***

- በአካባቢያችሁ በስፋት የሚለበሱ አልባሳትን፣ የሚደመጡ ሙዚቃዎችን፣ የሆቴሎች ወይም የተለያዩ የንግድ ተቋማት ስያሜዎችን በማጥናት ከዓለም አቀፋዊነት ተጽእኖ ጋር ያለውን ግንኙነት አስመልክታችሁ አጭር ጽሑፍ በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማቅረብ በሰፊው ተወያዩበት፡፡

## ቁልፍ ቃላት

- መታቀብ፡- ከአልኮል መጠጦች፣ ፈንጠዝያዎች፣ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም ከሌሎች ተግባራት በግል ፍላጎት ያለማንም አስገዳጅነት ራስን መቆጠብ ወይንም ማግለል
- መገለል፡- በቆዳ ቀለም፣ በቋንቋ፣ በሙያ ወዘተ. በተገናኘ ከሌላው በተለየ መንገድ መመልከት
- ሥልጣን መስጠት፡- ኃላፊነት ወይም ሹመት መስጠት
- ሥርዓተ ጾታ፡- ጾታን መሠረት ያደረገ ለወንዶችና ለሴቶች የተሰጠ ማኅበረሰባዊ የሥራ ወይም የሚና ክፍፍል
- አድሎ፡- ሰዎችን በእኩል አይን አለማየት ወይም እኩል መብት ያለመስጠት
- ኩባንያ፡- እንደ አንድ ግለሰብ ለመሥራት ሥልጣን የተሰጠው ቡድን
- የወጣት ጥፋተኝነት፡- ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች በሆኑ ወጣቶች የሚፈጸሙ የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶችን ያመለክታል።
- ድምፅን በድምፅ መሻር፡- አንድን ውሳኔ ውድቅ የማድረግ ወይም የመከላከል ሕጋዊ መብት
- ዓለም አቀፋዊነት፡- በግለሰቦች፣ በሕዝቦችና በሀገሮች መካከል እያደገ በመጣው ግንኙነት አማካኝነት አስደናቂ የመረጃ፣ የባሕል፣ የምጣኔ ሀብትና የቴክኖሎጂ ልውውጥና መጋራት

## ማጠቃለያ

- ተማሪዎች የኤች. አይ. ቪ. ቫይረስ በደማቸው ላለባቸው ወይም በኤድስ ለታመሙ ወገኖች ድጋፍና እንክብካቤ በመስጠት እንዲሁም በወገኖቻችን ላይ የሚያስከትለውን ማኅበረሰባዊ፣ አካላዊ፣ ሥነ አእምሮአዊ ጫና፣ የአድሎና የማግለል ተግባራት ለመቅረፍ ብርቱ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- በዓለምና በኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት መጠን በፍጥነት እያደገ ይገኛል፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት ሀገራት የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ለማውጣት ተገደዋል፡፡ በኢትዮጵያ የወጣው ብሔራዊ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲም በሕዝብ ብዛትና በተፈጥሮ ሀብት መካከል አወንታዊ ግንኙነቶች ለመፍጠርና ዘላቂ ምጣኔ ሀብታዊና አካባቢያዊ ልማትን መሠረት አድርጎ ተዘጋጅቷል፡፡
- ሥርዓተ ጾታን መሠረት ያደረገ የልማት እንቅስቃሴ ለሀገር ዕድገት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ የሥርዓተ ጾታ ጥያቄ የመብት ጥያቄ እንጂ የችሮታ ጥያቄ ባለመሆኑ ሁሉም ዜጎች ለሥርዓተ ጾታ እኩልነት ሊታገሉ ይገባል፡፡ ሴቶች ለልማትና ለዕድገት የሚያደርጉት የላቀ አስተዋጽኦን ለማሳደግ ሴቶችን ማብቃት አስፈላጊ ነው፡፡
- ወጣት ጥፋተኛነት በወጣቶች የሚፈጸም የወንጀል ተግባር ነው፡፡ በብዛት የሚታየው በከተማ አካባቢ ነው፡፡ የወጣት ጥፋተኛነት መነሻ ምክንያቶች መልካም ያልሆነ ቤተሰባዊ ግንኙነትና የአካባቢ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ለወጣት ጥፋተኞች ኅብረተሰቡና ወላጆች፣ ትምህርት ቤቶችና የሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ክበብ አባላት፣ የምክርና የአመራር አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች በጋራና በቅንጅት የሚሰጡት ድጋፍ ወጣት ጥፋተኝነትን ለመከላከል ጠቃሚ ናቸው፡፡
- የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተመሠረተው ዓለም አቀፍ ሰላምና ፀጥታን ለማስከበር፣ በመንግሥታት መካከል የወዳጅነት ግንኙት ለማሳደግ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባሕላዊና ሰብአዊ ችግሮችን ለማቃለልና ዓለም አቀፍ ትብብርን ለማረጋገጥ ነው፡፡ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ፣ የፀጥታው ምክር ቤት፣ ዋናው ጽሕፈት ቤት የምጣኔ ሀብትና ማኅበራዊ ምክር ቤት፣ የሞግዚት አስተዳደር ምክር ቤትና ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት የተባሉ ስድስት አካላት አሉት፡፡ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጽሕፈት ቤት የሚገኘው በኒውዮርክ ከተማ ነው፡፡
- ዓለም አቀፋዊነት በሀገሮችና በግለሰቦች መካከል የሚደረግ የመረጃ፣ የባሕል፣ የተፈጥሮ ሀብትና ቴክኖሎጂ ወዘተ ልውውጦችንና መጋራትን ይመለከታል፡፡ በቴክኖሎጂና በኮሙኒኬሽን ዕድገት ምክንያት ዓለም ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ አንድ መንደር መጥታለች፡፡ በዓለም አቀፋዊነት ተጽእኖ አንድ ሀገር ባሕሉን፣ እምነቱንና ማንነቱን በሌላው ላይ ሊጭን ወይም ሊያጣ ይችላል፡፡ ይህ ለውጥ ደግሞ በምጣኔ ሀብታዊ፣ በፖለቲካዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ይንጸባረቃል፡፡

# ምዕራፍ አራት
# የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች «እውነት» ወይም «ሐሰት» በማለት መልሱ፡፡**

1. በኢትዮጵያ ውስጥ ለእናቶች ሞት ዋነኛው ምክንያት ያለ ዕድሜ ማርገዝና መውለድ ነው፡፡
2. በኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ለልጃገረዶች ለጋብቻ የሚፈቀደው ዝቅተኛ ዕድሜ 18 ዓመት ነው፡፡
3. የፀጥታው ምክር ቤት አባላት በሙሉ ድምፅን በድምፅ የመሻር ሥልጣን አላቸው፡፡
4. ወጣቶች ራሳቸውንና ሌሎችን ከኤች. አይ.ቪ/ኤድስ የመከላከል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**ለ. አዛመዱ**

*በ "ሀ" ረድፍ የተዘረዘሩትን ሐረግ በ "ለ" ሥር ከቀረቡት ጋር አዛምዱ፡፡*

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ________ 1. የፀጥታ ምክር ቤት | ሀ. ኒው ዮርክ |
| ________ 2. የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መቀመጫ | ለ. የምጣኔ ሀብትና ማኅበራዊ ምክር ቤት |
| ________ 3. የተዘጋ የተመድ አካል | ሐ. የሞግዚት አስተዳደር ምክር ቤት |
| ________ 4. የተመድ ጽሕፈት ቤት | መ. ሄግ |
| | ሠ. ቬና |
| | ረ. ብራስልስ |
| | ሸ. ግጭቶችን እንዲያጠና ሥልጣን የተሰጠው አካል |
| | ቀ. የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎችን አስፈጻሚ አካል |

**ሐ. ምርጫ**

*ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ መርጣችሁ ጻፉ፡፡*

1. ከሚከተሉት አንዱ በኢትዮጵያ የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ስልት አልተካተተም፡፡
   ሀ. ለቤተሰብ ትምህርት መስጠት
   ለ. የልጃገረዶችን ዝቅተኛ የጋብቻ እድሜ ከ15 ዓመት ወደ 18 ዓመት ማሳደግ
   ሐ. የልጆች ቁጥር በቤተሰቡ ፍላጎት እንዲወሰን ማድረግ
   መ. በሥነተዋልዶ ጤና ላይ የምርምር መርሐ ግብር እንዲበለጽግ ማመቻቸት

2. ከሚከተሉት መካከል የሴቶች መብት ያልሆነውን ምረጡ
   ሀ. ከወንዶች እኩል መብት ማግኘት
   ለ. እኩል የትምህርት ዕድል
   ሐ. ከ18 በታች ባለ ዕድሜ ማግባት
   መ. ሀብትንና ንብረትን የመውረስና የማውረስ መብት

3. ኤች አይ. ቪ/ ኤድስን ለመዋጋት ውጤታማ ምላሽ የሆነውን አውጡ።
   ሀ. በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ምርመራ ማካሄድ
   ለ. ኮንዶምን ማስተዋወቅና ማቅረብ
   ሐ. አድሎና መግለልን ማስወገድ
   መ. ሁሉም መልስ ነው

4. የዘመኑ (እ.ኢ.ት.አ 2004 ዓ.ም.) የተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ ማን ናቸው?
   ሀ. ኮፊ አናን                ሐ. ባንኪ ሙን
   ለ. አማራ ኢሴይ               መ. ትሪጊቭ ላይ

5. ከሚከተሉት አንዱ በኢትዮጵያ በገጠር የሚኖሩ ሴቶችን ይገልጻል።
   ሀ. ሴቶች ከወንዶች ያነሰ የሥራ ሰዓት ይሠራሉ።
   ለ. ሴቶች ከወንዶች የበለጠ የትምህርት ዕድል አላቸው።
   ሐ. ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ለረጅም ሰዓት ይሠራሉ።
   መ. ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ገቢ ያገኛሉ።

**መ. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ሙሉ።**

***የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተስማሚ ቃላት ወይም ሐረጋት ሙሉ።***

1. በግለሰቦችና በሀገሮች መካከል እያደገ የመጣውን የእርስ በእርስ ግንኙነቶች የሚያሳየውን ዓለም-አቀፋዊ ትስስር ______________ ይባላል።
2. በዓለም የሚገኙ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችን የመንከባከብ ኃላፊነት የተሰጠው ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላት ____________ ይባላል።
3. በተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች የሚሳተፉ ወጣቶች __________ ይባላሉ።

**ሠ. የአጭር መልስ ጥያቄዎች**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።***

1. ወጣት ጥፋተኝነት ምንድን ነው?
2. ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ዘዴዎችን ግለጹ።
3. አድሎና ማግለልን ግለጹ።
4. በአካባቢያችሁ የሚታይ የዓለም አቀፋዊነት ተጽእኖ መገለጫዎችን ዘርዝሩ።

**ፍተሻ**

*ልታከናውኗቸው የምትችሉአቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን ምልክት (✓) በሳጥኑ ውስጥ አስፍሩ*

1. ኤች አይ.ቪ/ኤድስን ለመዋጋት የሚያስችል የሕይወት ክህሎት አዳብራለሁ። ☐
2. የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ያለ ወገኖችን የሚንከባከቡ ግለሰቦች አርአያ አድርጌ እከተላለሁ። ☐
3. የሕዝብ ዕድገትን ሁኔታ በኢትዮጵያ እተነትናለሁ። ☐
4. የሕዝብ ዕድገትን ለመግታት የተነደፉ ስልቶችን እለያለሁ። ☐
5. የኢትዮጵያን የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ጠቀሜታንና የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂን እደግፋለሁ። ☐
6. በጾታና በሥርዓተ ጾታ መካከል ያለውን ልዩነት እገልጻለሁ።
7. የጾታ እኩልነትን ገጽታዎች እለያለሁ። ☐
8. ወጣቶች የጾታ እኩልነትን በማስፋፋት ዘንድ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ አደንቃለሁ። ☐
9. በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በምሳሌ በማቅረብ እወያያለሁ። ☐
10. የሴቶችን ተሳትፎ በማሳደግና በጋራ በመሥራት ድህነትን የመቀነስ ጠቀሜታ አረጋግጣለሁ። ☐
11. የወጣት ጥፋተኝነትን በምሳሌ እገልጻለሁ። ☐
12. ወጣት ጥፋተኝነትን እንዴት መከላከል እንደሚቻል እገልጻለሁ። ☐
13. በአካባቢያችን ስላለው የወጣት ጥፋተኝነት ማስታወሻ እጽፋለሁ። ☐
14. የተመድን ጠቀሜታና መተዳደሪያ ደንቦች አብራራለሁ። ☐
15. የተመድን ዋና ዋና አካላትና ሥራቸውን እለያለሁ። ☐
16. የዓለም አቀፋዊነት ትስስር ሐሳብን አስረዳላሁ። ☐
17. ለንግድ፣ ለባህልና መረጃ የተፈጠሩ ጥሩ አጋጣሚዎችንና የተደቀኑ ችግሮችን እገልጻለሁ። ☐